ማውጫ

ተ.ቁ ---------- 1-2

1. ማውጫ ---------- 1-2

2. የዝግጅቱ መግቢያ ---------- 3

አሪት ዘፍጥረት

3. የዘፍጥረት መግቢያ ---------- 5

4. አሪት ዘፍጥረት ---------- 6-24

5. ስለ ፈጣሪና ፍጥረት ---------- 9

6. ስለ ፈጣሪና ፍጥረት ---------- 9-14

7. ስለ መላእክትና ሰው ተፈጥሮ ---------- 14-16

8. ትንቢትና ቅዱስ መጽሐፍ ---------- 17-22

9. የምዕራፍ አንድ የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 23

10. ማጠቃለያ ---------- 23

ምዕራፍ ሁለት

11. መግቢያ ---------- 24

12. ምድራዊው የአዳምን ሔዋን ህልውና ---------- 24-31

13. ዓለማውያን ዓድቃን ---------- 31-36

14. ደገኛው አብርሃም ---------- 36-41

15. የምዕራፍ ሁለት የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 42

16. ማጠቃለያ ---------- 42

ምዕራፍ ሦስት

17. መግቢያ ---------- 43

18. የዋሁ ዮሴፍ ---------- 43-45

19. ተፈላጊ ትርጓሜዎችና የዘፍጥረት ማጠቃለያ ---------- 46-51

20. ዘመነ-አሪት የዘመነ-መሳፍንት ሁለተኛ ክፍል ---------- 51-54

21. የምዕራፍ ሦስት የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 54

22. ማጠቃለያ ---------- 54

ምዕራፍ አራት

23. መግቢያ ---------- 55
24. ሙሴ ---------- 55-61
25. ካህኑ አሮን ---------- 61-66
26. ኢያሱ ---------- 66-70
27. የምዕራፍ አራት የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 70
28. ማጠቃለያ ---------- 70

ምዕራፍ አምስት

29.መግቢያ ---------- 71
30. ደግኛይቱ ዲቦራ ---------- 71-75
31. ደግኛዋ ሐና የሳሙኤል እናት ---------- 76-82
32. ከዘፀዓት እስከ ሳሙኤል ---------- 82-88
33. የምዕራፍ አምስት የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 88
34. ማጠቃለያ ---------- 88

ምዕራፍ ስድስት

35. መግቢያ ---------- 89
36. ቃል ኪዳን በቅዱስ መጽሐፍ ---------- 89-96
37. መስዋዕተ ኦሪት ከየት እስከየት ---------- 96-102
38. ሰው ማልቀስ ያለበት ለየትኛው ሰው ነው ---------- 102-105
39. ክርስቲያን በማኅበራዊ ኑሮ ---------- 105-111
40. የምዕራፍ ስድስት የሙከራ ጥያቄዎች ---------- 111-112
41. ማጠቃለያ ---------- 112

የዝግጅቱ መግቢያ

ውድ በርቀት ያለኸው ደቀመዝሙሬ በክፍተኛ መንፈሳዊ ተቋም ደረጃ የሚሰጠውን የብሉይ ኪዳን ትምህርት ከመጀመርህ አስቀድሞ ቤተክርስቲያንን በስብከቱ ያሸበረቃት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱሳት መጻህፍትን ምስጢር ትርጉም ማጥናት ያለውን ጉልህ ጠቀሜታ ሲገልጽ ፡-

“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል 2ኛ- ጢሞ. 3፡-16-18”

በማለት ባስተላለፈው የተቀደሰ መልዕክት መሠረት በዓለም ካሉ ሀገሮች ሁሉ ከእስራኤል ቀጥላ በቀደምትነት በአምልኮተ እግዚአብሔር የምታተወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ ተርጉማ እስካሁን ጥንታዊነቱን እንደጠበቀ መኖሩን አብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ምሁራን ያረጋግጣሉ፡፡

በሩቅ ያለኸውደቀመዝሙሬ እንደምን ሰነበትህ ይህ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ የትምህርት ዝግጅት ስታጠናቅቅ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ያለህን ዕውቀት በማሳደግ ወደ ከፍተኛ ማስተዋል ትሸጋገራለህ፡፡

በዚህ የክፍል አንድ የብሉይ ኪዳን የርቀት ትምህርት ዝግጅት ውስጥም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ሥርዓትና ጥንታዊው የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት አስተምህሮን በመከተል ሰፊ ዕውቀት የምታገኝበትና ራስህን ከተሳሳተ ትምህርት የምትጠብቅበት የብሉይ ኪዳን ትምህርት ሰፊ ትንታኔና ማብራርያ ይዞ ስለቀረበ በማስተዋል ተመልከተው፡፡

በክፍል አንድ የብሉይ ኪዳን ትምህርት ዝግጅት ውስጥም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ኢሳይያስ ያለው የብሉይ ኪዳን ትምህርት በመንፈሳዊ የትምህርት ተቋም ደረጃ አንድ መንፈሳዊ ደቀመዝሙር ሊገነዘበው በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በሁሉም ዝግጅቶች ዙሪያ የመጽሐፉ ሥም አሠያየም ፡- የመጽሐፉ ጸሐፊ፡ በጠቅላላው የመጽሐፉ አከፋፈል በተጨማሪም የማገናዘቢያ ጥያቄዎችና ማጠቃላያ ነጥቦች ተካተውበት ቀርቦአል፡፡

<u>ይህን የብሉይ ኪዳን ክፍል አንድ የርቀት ትምህርት ካጠናቀቅህ በኋላ</u>

- ትክክለኛውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ታሪክና ትርጉም ትገነዘባለህ፡-
- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ታሪካቸውንና ትርጉማቸውን ተረድተህ ለሌሎች ታስረዳለህ፡-
- በጠቅላላው እግዚአብሔር በየዘመናቱ ለሕዝቡ ያለውን የተቀደሰ ዓላማ ተረድተህ አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር ለማድረግ ሰፊ ትምህርት ታገኝበታለህ፡፡

የዘፍጥረት መግቢያ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀመዝሙሬ በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የምታገኛቸው ጥልቅ ትንታኔ ያላቸው ትምህርቶች፡-

- የዘፍጥረት መጽሐፍ ስያሜ /ሥሙ/
- የዘፍጥረት መጽሐፍ ፀሐፊን በተመለከተ፡-
- የስነ-ፍጥረትን ታሪክ ማን ጻፈው?
- የዘፍጥረት መጽሐፍ ዓላማው፡-
- የፍጥረት ተረክቦን በተመለከተ፡-
- የፍጥረት አፈጣተርን በተመለከተ፡-
- የፍጥረት ዜና መዋዕልን በተመለከተ፡-
- ስለ ቀኑ ትርጉም በተመለከተ፡-
- ስለ ሰው ውድቀት፡-
- ስለ ሰው ውድቀት በየሀገሩ የሚነገሩ የተለያዩ ትውፊቶች፡-
- የማየ አይኅ ታሪክ በተለያዩ ዓለማት፡-
- ከተለያዩ ዓለማት የተገኙ የማየ አይኅ የተለያዩ ትውፊቶች፡-
- ስለ ባቢል ጥቅመ ሰናያር /የሰናያር ግንብ/
- ስለ አበው /ፓትርኬይ/፡-
- ቅድመ ማየ አይኅ የነበሩ አበው፡-
- ድኅረ ማየ አይኅ የነበሩ አበው፡-
- ስለ አርዕስተ አበው ፡-
- ስለ ዘፍጥረትመጽሐፍ አከፋፈል ከፊደል ሀ እሰከ ፊደል መ ድረስ

በዝርዝር ታገኛለህ እጅግ ሰፊ የሆነ ግንዛቤ ታገኝበታለህ በማስተዋል ተመልከተው፡፡

መልካም ንባብ!

ኦሪት ዘፍጥረት

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

በአይሁድ አጠራር “በረሺት” ይባላል። ቃሉም ዕብራይስጥ ነው። ይህም በቀዳሚ ወይም “በመጀመሪያ” ማለት ነው። ስያሜው የተወሰደው በመጽሐፉ አንደኛ ምዕራፍ መጀመሪያ ቁጥር ላይ ካለው መነሻ ቃል ነው። በታልሙድም መጽሐፈ ፍጥረተ ዓለም” ተብሎ ይጠራል።

ሰብዓው ሊቃናት ግን፣ ጂኔሲስ” የሚል ርእስ ለዚሁ መጽሐፍ ሰጥተዋል። ትርጓሜውም ዘልደት ዘፍጥረት ወይም መጀመሪያ ምንጭ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደማንኛውም ቋንቋ የተረጐሙ ሊቃውንት ሁሉ ይህን የሰብዓው ሊቃናትን ስያሜ ተከትለዋል። ጂኔሲስ ወይም ልደት በዕብራይስጡ ተወልዶተ ነው ይኸውም ቃል በዚሁ መጽሐፍ 11 ጊዜ ርእስ ነገር በመሆን ተጠቅሶ ይገኛል፣ 2፥4። 5፥1። 6፥9። 10፥1። 11፥10። 27፥25፡12፣19። 36፥1፣9። 37፥2/ በዚህም መነሻነት ሰብዓው ሊቃናት ለመጽሐፉ ርእስ ወይም መጠሪያ ሊያደርጉት ችለዋል። ሠለስቱ ምዕት ለመጻሕፍት ሁሉ ርዕስ ሲሰጡ ለዚህም ዘፍጥረት ብለው ርዕስ ሰጥተዋል።

የቤተ ክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ግን “ዘፍጥረት” ወይም “ዘልደት” የሚለውን ርእስ ሠለስቱ ምእት እንደሰጡ አድርገው ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ” ... እስከዚህ አርእስት ሰጥተዋል፡- እርሱ ግን ነገሩን በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ብሎ ያመጣዋል” ይላል ይሁን እንጂ ይህ አባባል በብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ከሠለስቱ ምእት አስቀድሞ የብሉይ ኪዳን መጀመሪያው መጽሐፈ ልደት ወይም ዘፍጥረት /ጂኔሲስ/ እየተባለ ይጠራ ነበርና።

ጸሐፊው

የፍጥረት ጸሐፊ ማን እንደሆነ ግልጥ ማስረጃ በውስጡ ባይገኝም ሙሴ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ እንደ ጻፈው ከጥንት ጀምሮ በአይሁድና በክርስቲያኖች ዘንድ ትውፊት አለ። ከዚህም ጋር የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት የዘፍጥረት ጸሐፊ ሙሴ ለመሆኑ የውስጥ ማስረጃ ለማቅረብ የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣሉ። ለምሳሌ ግዝረት በ8ኛው ቀን መሆን እንደሚገባው በዘፍጥረት 17፥12። ዘጸአት 12፥48 እና ዘሌዋውያን 12፥3 የተነገረው ቃል በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በወንጌለ ዮሐንስ 7፥21-23 ላይ ሲጠቀስ ጉዳዩ ከኦሪተ ሙሴ ጋር ተያይዞ መነገሩ ሙሴ የኦሪት ዘፍጥረት ጸሐፊ መሆኑን ያስረዳል

እንደዚሁም በዘፍጥረት ውስጥ የተነገረው የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ተስፋ በሌሎቹ ሙሴ እንደጻፋቸው የውስጥ ማስረጃ በተገኘላቸው በአራቱ መጻሕፍተ ኦሪት በተመሳሳይ ቃል መደገማቸው የጸሐፊውን አንድነት ያረጋግጣል፡፡

አንዳንድ የኦሪት ዘፍጥረት ምንጮች በሙሴ ዘመን የተፈጸሙ አለመሆናቸው የተረጋገጠ ነው፡፡ ለምሳሌ ከአብርሃም እስከ ልደተ ሙሴ ያለው ክፍል ሙሴ ከመወለዱ በፊት በአጭሩ የ300 ዓመት ዕድሜ አለው፡፡ ታዲያ ሙሴ ከራሱ በፊት በነበረው ክፍለ ዘመን የተፈጸሙ ድርጊቶችን እንዴት ጻፈ? ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው መልስ ሙሴ በአስተርእዮተ እግዚአብሔር ልዩ መመሪያ ከእግዚአብሔር በማግኘት ጽፎታል የሚል ነው፡፡ /አሞጽ 3፥7/ ይህን የማይቀበሉ አንዳንድ ሊቃውንት ግን ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ መዝገበ ታሪክ አግኝቶ ጽፎታል ይላሉ፡፡ ለዚህም የሚከተለውን ማስረጃ ያቀርባሉ በያመቱ በግብጽና በከነዓን የቄፋሮ ምርምር ይደረጋል፡፡ በምርመራውም መሠረት በሙሴ ዘመን የነበረ የጽሑፍ ማስረጃ በአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ የተመዘገበው ታሪካዊ እውነት ተገኝቶአል፡፡ ከዚህም ጋር ሙሴ በፈርያን ቤተ መንግሥት የሠለጠነና የግብጻውያንን ጥበብ ሁሉ የተማረ ነበረ /የሐዋ 7፥22/፡፡ የሥነ ጽሑፍም ሰው ነበር /ዘጸአት 34፥27 ዘኁልቁ 17፥2 ዘዳግም 6፥9፡፡ 24፥1-3፡፡ ኢያሱ 8፥32/ በመሆኑም ታሪክን ሰብስቦ ሊጽፍ ችሎአል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ማስረጃ የሙሴን ዐዋቂነትና ሥልጣኔ ከማረጋገጡ በቀር አስተርእዮተ እግዚአብሔርን አይቃወምም፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለጠቢባን አይገልጥም አልተባለምና፡፡ በቄፋሮ የተገኙ ማስረጃዎችም ሁሉ የእግዚአብሔርን ለሰዎች መገለጥ አልሰወሩምና ወይም አላስተባበሉምና፡፡

<u>የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ማን ጻፈ?</u>

ስለ ሥነ ፍጥረት ታሪክ አጻጻፍ ሁለት አይነት የሊቃውንት አስተያየት አለ፡፡

1ኛው፡- ሙሴ በልዩ አስተርእዮተ እግዚአብሔር ወይም በአለብዎተ መንፈስ ቅዱስ /By inspiration to God/ ጻፈው የሚል ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ይህን ዓለም እንዴት እንደፈጠረ በዘፈቀደ ተገልጦ ለሙሴ ነገረው፣ ሙሴም ከእግዚአብሔር የሰማውን ሁሉ ጻፈው ማለት ነው፡፡

2ኛው አስተያየት ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ከሙሴ በፊት ከብዙ ዘመናት ጀምሮ የፍጥረት ታሪክ ተጽፎ ነበር፡፡ ምናልባት በአብርሃም ወይም በኖህ ወይም በሄኖክ ተጽፎ ይሆናል፡፡ ከዚህም ጋር ሥነ ጽሕፈት ቅድመ ዘመነ አብርሃም የታወቀና የተለመደ ነበር፡፡

በኡር በሌሎችም እንደ ባቢሎን ባሉ ታላላቅ ከተማዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መጻሕፍት መዛግብት ቃላት ሰዋስው፣ የጥቅስ ሥራዎች መድበለ ታሪክ/ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የሂሳብ ሥራዎች የከዋክብት ጥናቶች የመልክአ ምድር፣ የሃይማኖትና የፖለቲካ ጽሑፎች ወዘተርፈ ያለባቸው አብያተ መጻሕፍት ነበሩ አብርሃም ስለ ፍጥረትና ስለ ሰው ውድቀት ስለ ጥፋት ውኃም/ ማየ አይኅ/ ከሴም ትውፊትን፣ ወይም መዝገቦችን ተቀብሎአል። አብርሃም ሥነ ጽሑፍ በታወቀበት ቤተ መጻሕፍት በነበረው ጎብረተሰብ መካከል ይኖር ስለነበር በትውፊት ያገኘውን፣ እግዚአብሔርም ተገልጦ የነገረውን ሁሉ በጥንቃቄ ይዞአል። በሸክላ። ጽላትም ላይ በክዩኒፎርም ጽሕፈት ጽፎ ለትውልደ ትውልድ አስተላልፎታል።

ይህ ሁለተኛው አስተያየት በዘመናውያን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት የተደገፈ ነው። ይሁን እንጂ በአይሁድና በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዛሬዎችም ብዙዎች ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት ያለው አስተያየት የመጀመሪያ ነው። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የፍጥረት ታሪክ ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ በመጀመሪያው መጽሐፉ /የጥንት ጽሑፍ አንቲኩቲ/ በሰፊው ያብራራል/።

ዓላማው

ኦሪት ዘፍጥረት ከእግዚአብሔር በቀር የሁሉን አጀማመርና አመጣጥ ይናገራል። ከመጀመሪያ ጀምሮ እስራኤላውያን ወደ ግብጽ እስከ ገቡበት ድረስ ስለ መለኮታዊ አስተርእዮ ታሪክ አጭር አገላለጥ ይሰጣል።

በዚህ መጀመሪያ መጽሐፍ ውስጥ፡-

1. የእግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ መታወቅ /1፥1/
2. የዓለም አጀማመር /1፥1-25/
3. የሰው ዘርእ መጀመሪያ /1፥26-30/። /2፥7/
4. በመጀመሪያ ጊዜ የኃጢአት ወደ ዓለም መግባት /3፥1-7/
5. የድኅነት ተስፋ አጀማመመር /3፥8-24/
6. የቤተሰብ ሕይወት /የጋብቻ አጀማመር /2፥22/
7. የመሥዋዕት አጀማመር /4፥1-15/
8. የሰው ሠራሽ ሥልጣኔ አጀማመር /4፥16፣ 9፥29/
9. ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ሕዝብ በነገድ መከፋፈል /ምዕ 10፥11/
10. የዕብራውያን ነገድ አጀማመር /ምዕራፍ 12፥50/

11. በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የቃል ኪዳን አጀማመር ተገልጠዋል። ኦሪት ዘፍጥረት በጠቅላላ ስለ ማናቸውም ነገር መጀመሪያ ይናገራል። ስለዚህም ሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ምንጭ መሠረትና መቅድም ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ የሚናገረው ስለ ዘርአ አብርሃም ከዚያም በእርሱ በኩል ስለሚመጣው መሢህ ነው። ይህም በዘፍጥረት ተነግሮአል።

የኦሪት ዘፍጥረት ምንጮች /ማቴሪያሎች/

የብሉይ ኪዳን መጀመሪያው መጽሐፍ ኦሪት ዘፍጥረት ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ከጸሐፊው በፊት በተፈፀሙ ድርጊቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

1. ፍጥረት

የሙሴ መጀመሪያው መጽሐፍ ስሙ እንደሚመለከተው ስለ ሥነ ፍጥረት አመጣጥ በመተረክ ይጀምራል። ስለ ፍጥረታት ፈጣሪ ግን "በመጀመሪያ እግዚአብሔር" ከማለት በቀር ምንም አይነት ዝርዝር ሁኔታ አይሰጥም። ምክንያቱም የኦሪት ዘፍጥረት ፀሐፊ /ሙሴ/ እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም የነበረ መሆኑን በማመን ስለ ሥራው ብቻ ለመግለጥ ስለፈለገ ነው።

የፍጥረት ተረክቦ

የዚህ ዓለምና የሕይወት መገኘት ድንገተኛ አይደለም። አጋጣሚ ወይም ቀስ በቀስ አይደለም። ፈጣሪ፣ አምላክ አለው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ "እንዲል /ዘፍ 1÷1/ ፈጣሪ /አምላክ/ ይህን ዓለም በውስጡም ያለውን በጠቅላላ የሚታየውንና የማይታየውን ካለመኖር ወደ መኖር አስገኘ። እስመ ውእቱ ይቤ፣ ወኮነ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ ... እርሱ ይሁኑ አለ ሆኑ። እርሱ አዘዘ፣ በትእዛዙም ተፈጠሩ /መዝ 148÷5/። እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ከፍተኛ ክብር ያለው ሰው ነው። ከሌላው ፍጥረት ሁሉ በሁለት አቅጣጫዎች ይለያል። 1ኛ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ እርሱ ብቻ ነው። 2ኛ በፍጥረታት ሁሉ ላይ ሥልጣን የተሰጠው እርሱ ብቻ ነው።

ፍጥረት በመጀመሪያ በራሱ ከነበረው ማቴሪያል አልተፈጠረም። ራሱም በራሱ አልመጣም ግን በቃለ እግዚአብሔር፣ በኃይለ እግዚአብሔር የተገኘ ነው። /ዕብ 11÷3/ ይሁን እንጂ ፍጥረት ከኢምንት ወይም እምኀበ አልቦ ተገኘ ማለት ነውና ይላሉ። ይህንም ማለታቸው ፍጥረት ሁሉ የተገኘበት አንድ ግዙፍ /ማተር/ አስቀድሞ ነበር ለማለት ስለፈለጉ ነው። ነገር ግን ግዙፍ አካል /ማተር/ ያለ አንድ ኃይል በራሱ ህላዌነት እንደነበረ

ለማወቅና ለመረዳት የሚያስችል ዕውቀት የለም። ስለዚህም ከ "አልቦ የሚገኘው አልቦ ነው" የሚለው አስተሳሰብ ምክንያተ ፍጥረትን አይቃወምም ምክንያቱም ፍጥረት የተገኘው በራሱ ህላዌነት ከነበረውና ከሚኖረው እግዚአብሔረ ነው እንጂ ከአልቦ አይደለምና።

በብሉይ ኪዳን ከተጻፈው ታሪክ ጋር የሚመሳሰል አንዳንድ ጊዜም የሚቃረን ስለፍጥረት የሚናገር ታሪክ በመካከለኛው ምሥራቅ ጥንታውያን ከተሞች ተገኝቶአል። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት መጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ካለው የፍጥረት ታሪክ ጋር የሚመሳሰሉ ከአብርሃም ዘመን በፊት የተቀረፁ ስለ ፍጥረት የሚገልጡ ግጥሞች ያሉባቸው የሸክላ ሥሌዳቸው በባቢሎን በነነዌ፣ በኒፑርና በአሹር በቅርብ ጊዜ ተገኝተዋል።

<u>የፍጥረት አፈጣጠር</u>

ፍጥረት በሁለት ዓይነት አፈጣጠር ተፈጥረዋል።

1. <u>ቀዳማይ ፍጥረት፡-</u>

በመጀመሪያ /እምኅበ አልቦ ኀበቦ ባለመኖር ወደ መኖር የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ቀዳማይ ፍጥረት ይባላል። ለምሳሌ ሰማይና ምድር ቀዳማውያን ፍጥረታት ናቸው። በቃለ እግዚአብሔር እምኅበ አልቦ መጡ እንጂ በራሱ ኀላዌነት ከነበረ ግዙፍ ነገር አልተገኙምና።

2. <u>ካልዕ ፍጥረት፡-</u>

ከግብር የተገኘው ግብር ሁሉ ካልእ ፍጥረት ይባላል። ለምሳሌ ሰው፣ አራዊት አዕዋፍ ወዘተርፈ ካልአን ፍጥረታት ናቸው። አስቀድሞ ከተፈጠረው /ከተገኘው ከመሬት ተፈጥረዋልና/ ዘፍ 2፥7፣ 2፥19/።

የቀዳማውያንና የካልእን አፈጣጠር በቃልም ይለያል። በዕብራይስጡ ፈጠረ ለማለት "ባርአ" ይላል። ትርጓሜው ያልነበረውን ካልነበረ ማምጣት ማስገኘት፣ ያልሆነውን መሆን ማለት ነው። ስለዚህ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ "የሚለው ዐረፍተ ነገር በዕብራይስጡ" በረሺት ባርኤሎሂም ሀሸማይም ወሀኤረድ ነው። እንደዚሁም ከመጀመሪያው ፍጥረት ላይ ሌላው /ካልእ/ ፍጥረት እንዴት እንደተገኘ ሲገልጥ ዕብራይስጡ "እሳህ" ይላል። ትርጉሙም "አበጀ" ከነበረው ላይ ወሰደ ሠራ አደራጀ ማለት ነው። ስለዚህም ግእዙ ግንበር ስብአ "የሚለውን ቃል ዕብራይስጡ ንእሳህ ሀአዳም" ይለዋል። ሰውን እንሥራ ወይም በግእዙ ንልሐኩ ማለት ነው። /ዘፍ 1፥26/

<u>የፍጥረት ዜና መዋዕል</u>

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ በ6 ቀናት ፈጥሮ እንደፈጸመ ኦሪት ዘፍጥረት ያስረዳል፣ በዚህም ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር 8 የመፍጠር ትእዛዛትን /ትእዛዘተ ፈጢር/ ሰጥቶአል፣ በእነዚህም ቀናትና ትእዛዛት የተፈጸሙትን ድርጊቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

የመፍጠር ትእዛዛት /እግዚአብሔር አለ/ ዘፍጥረት ምእ.1/	ቀን	ፍጥረታት
1. ቁጥር 3	1	ብርሃን
2. ቁጥር 6	2	ጠፈር
3. ቁጥር 9	2	አብሕርት
4. ቁጥር 11	3	የብስና ተክል
5. ቁጥር 14	4	ብርሃናት
6. ቁጥር 20	5	አእዋፍ ዓሣት
7. ቁጥር 24	6	እንስሳት

<u>የቀኑ ትርጉም</u>

በመፍሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለቀን አያሌ ትርጉም አለው፡፡

ሀ. መጀመሪያውና የተለመደው ትርጉም

12 ሰዓት መዓልትና 12 ሰዓት ሌሊት በድምሩ 24 ሰዓታት አንድ ቀን የሚለው ነው፡፡ /ዮሐ. 9÷14፣ 11÷9/፡፡

ለ. የተለየ ጊዜ፣ ለምሳሌ ዕለተ እግዚአብሔር /ኢሳ. 2÷12፣ ዘካ 14÷1/፡፡ ይህ ያልታወቀ ክፍለ ዘመንን ያመለክታል፡፡

ሐ. ረኸርም ክፍለ ዘመን /መዝ. 89÷4፣ 2ጴጥ. 3÷8/ ስለ ቀን ሌላም አስተያየትና ትርጉም ሊኖር ይችላል፡፡ እንግዲህ ቀን የተባለ 24 ሰዓት ብቻ ከሆነ እግዚአብሔር ይህን ዓለም ፈጥሮ ያከናወነው /የፈጸመው/ በ6 ቀናት ውስጥ /በ144 ሰዓታት፣ መሆኑ ነው፡፡ ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ይህን አስተያየት ቃል በቃል ይቀበላሉ፡፡ “እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና” እንኳንስ በ6 ቀናት በ6 ሴኮንድም ቢሆን ፍጥረትን ሁሉ ሊፈጥር ይችላልና፡፡ ይህም ቃል በቃል /ሊተራል/ ትርጓሜ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ፍጥረትን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ ለሚለው አነጋገር ተስማሚ ነው፡፡

ምክንያቱም አንድ ቀን ማለት አንድ ሺህ ዓመት ከሆነ እግዚአብሔር ለአንድ ሺህ ዓመት ያለ ሥራ በዕረፍት ኖረ ማለት ይሆናል።

አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ቀን የተባለ አንድ ረዥም ክፍለ ዘመን ነው የሚለውን ሀሳብ በማጽናት ፍጥረት የተከናወነው በ24 ሰዓት ርዝማኔ ተለክቶ በተቆጠረው በ6 ቀን ሳይሆን በረዥም ዘመናት ነው ይላሉ። ወይም አንዱን ቀን እንደ አንድ ሺህ በመቁጠር በ6000 ዓመታት ይህ ዓለም ተፈጥሮአል በማለት ሀሳባቸውን ያጸናሉ። ይህም አስተያየት ፍጥረት ቀስ በቀስ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ የሚለውን የሳይንስ ሊቃውንት አስተያየት ይመስላልና ከመጀመሪያው ጋር ይቃረናል። በጠቅላላ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ይለውጣል።

ሌሎች አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ስድስት ቀን የተባለው እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥርት ሁሉ ለሙሴ በስድስት ቀን መግለጡን የሚያሳይ ነው። እንጂ ፍጥረት በስድስት ቀን ጊዜ ውስጥ መፈጠሩን የሚያመለክት አይደለም ይላሉ። የእኛም ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት፣ ሙሴ በእግዚአብሔር ተጠርቶ ወደ ደብረሲና ከወጣ በኋላ ለ40 ቀናት በርእስ ደብር ቆየ ይሉና፡- ስድስቱን ቀን በስድስት ዕለታት የተፈጠሩ ሀያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረታት በልቡናው ሲስልበት ሰንብቷል ሠላሳ አራቱን ቀናት "ወነበቦ፣ ወነበቦ" ያለውን ቃል ሲነግረው ሰንብቷል በማለት ይተርካሉ።

ይህ አስተያየት እግዚአብሔር በ6 ቀንም ይሁን፣ በ6000 ዓመት የፈጠረውን ፍጥረት ለሙሴ በስድስት ቀን እንደገለጸለት ያስረዳል። ይሁን እንጂ በጥንታውያን የቤተ አይሁድና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ የሚታመነው፡- በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ውስጥ "ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን ..." ተብሎ በተመለከተው መሠረት ፍጥረት ሁሉ በስድስት ቀን እንደተከናወነ ነው። ዛሬም ቢሆን ይህኑ አስተያየት የሚከተሉ ብዙዎች ናቸው።

2. <u>ውድቀት</u>

የመጀመሪያ የሙሴ መጽሐፍ ከፍጥረት ቀጥሎ የሚተርከው ስለ ታላቁ ፍጥረት ስለ ሰው ውድቀት ነው።

ሰው በኃጢአት ሊወድቅ የቻለው በእባብ ተንኮልና ክፋት ነበር። እባብ ለጊዜው ራሱ እንደሚናገር ሆኖ ተገልጦአል። ነገር ግን በኋላ ሰይጣን በእባቡ አድሮ የሚናገር ወይም እባቡ የሰይጣን መሣሪያ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተጠቅሶአል። /2ቆሮ. 11፥3-14፣ ራእይ 12፥9፣ 20፥2/። ከዚህም ጋር መጽሐፈ ሄኖክ በምዕራፍ 19፥19

ላይ ሰይጣን ራሱ ገልጦ ይናገራ፣ ጋድርኤል ዝውእቱ ዘአርአየ ኩሎ ዝብጠታተ ሞት ለውሉደ ሰብእ፣ ወውእቱ ዘአስሐታ ለሔዋን" ጋድርኤል የሞት ግድያን ለሰው ልጆች ያሳየ ነው። ሔዋንንም ያሳታት እርሱ ነው። ሰለሞንም በመጽሐፈ ጥበብ 2÷24 ላይ ወበቅንአተ ዲያብሎስ ቦዓ ሞት ውስተ ዓለም በዲያብሎስ ቅንዐት ሞት ወደ ዓለም ገባ በማለት የሰው ልጅ ውድቀት የመጣው በእባብ መሣሪያነት በሰይጣን አማካኝነት መሆኑን ያስረዳል።

በመሠረቱ እባብ ቆሞ የሚሄድ በጣም ውብ እንደነበረ ይነገራል። ይህም ለሰይጣን መሣሪያነት ተስማሚ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም በዘፍጥረት 3÷14 ላይ በሆድህ ትሄዳለህ የሚለውን ቃል በመመልከት ከመረገሙ በፊት አራት እግሮች ነበሩት በማለት የሚተርኩ አሉ። የእኛም ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት "አምሳለ ዕንለ ገመል" የግመል ወሳብሬ ያህል ነበር ብለው ይተርካሉ። ይሁን እንጂ በኦሪት ዘፍጥረት 3÷14 ያለው ቃል እግር እንደነበረው በግልጥ የሚያሳይ አይደለም።

ሰው ለሰይጣን ታዛዥ በመሆኑ ለእግዚአብሔር አልታዘዘም። የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተቃወመ። በራሱ መንገድ ለመሄድ መረጠ። ራሱ አምላክ ለመሆን ተመኘ። የዚህም ውጤት የሚከተለው ሆነ። የመጀመሪያው ሰው ከገነት ወጣ ወዲያውኑ መንፈሳዊ ሞት ሞተ ማለት ከእግዚአብሔር ተለየ። ሕይወቱ በሥቃይ በሕማምና በድካም ሆነ። ሥጋዊ ሞትንም ከእርግማን በኋላ እንዲሞት ሆነ ይሁን እንጂ ሰው እግዚአብሔርን ቢተው እግዚአብሔር ሰውን አልተወውም። ቢጠፋ ፈለገው /ዘፍጥረት 3÷8-9/ የድኅነት ተስፋም ሰጠው /3÷15/ ቢራቆትም አለበሰው /3÷21/።

እግዚአብሔር ሰውን ኃጢአት እንዲሠራ አድርጐ ለምን ፈጠረው?

ይህ ሁልጊዜ በሕጻናት ሳይቀር የሚቀርብ ጥያቄ ነው። እግዚአብሔር ሰውን እንደሚመራ እንደ እንስሳ አድርጐ ካልፈጠረው ሌላ መንገድ ሊኖር ይችላልን? ያለ ምርጫ ኃይልስ ሞራላዊ ፍጡር ሊሆን ይችላል?

ነፃነት ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ታላቅ ስጦታ ነው ነፃነት ለማሰብ ነፃነት ለመምረጥ፣ ነፃነት ለመፍቀድ፣ ነፃነት በራሱ መንገድ ወይም በሌላ መንገድ ለመሄድ ለሰው ተሰጠው ስለዚህም ሰው ለፈጣሪው ላለመታዘዝ ወይም የፈጣሪውን ትእዛዝ ለማቃለል በነፃነት ተጠቅሞአል።

ስለዚህ የሰው ውድቀት ከነፃ ፈቃድ የመነጨ ነው። የእግዚአብሔርም ጣልቃ ገብነት ፈጽሞ የለበትም።

ስለ ሰው ውድቀት በየሀገሩ የሚነገሩ የተለያዩ ትውፊቶች

1. **ባቢሎን፡-** ሰው በእባብ አካል በተሰወረው መንፈስ በመታለሉ ከዕፀ ሕይወት መባረሩን፣ ወደዚያም እንዳይመለስ በኪሩብ መጠበቁን የሚጠቅሱ ጽሑፎች በባቢሎን ተገኝተዋል፡፡ ከእነዚህም ጽሑፎች ለሰው ዘርእ ሁሉ አባት የሆነው አዳም የሰማይ ጠቢባን አማልክትን አስቀየመ ስለዚህም መዋቲ ሆነ፡፡ ምግበ ሕይወትን እንዳይበላ ተከለከለ፡፡ /ሕማምን/ ሥቃይን በሕዝብ ላይ አመጣ፡፡ አማልክትም "ዕረፍት አይኑርህ" አሉት "ልብሰ ኀዘን አለበሱት" የሚሉት ታሪኮች በሸክላ ላይ ተቀርፀው ተገኝተዋል፡፡
2. **ፋርስ፡-** ፋርሳውያን ንጹሐን ደጋጎች እና ደስተኞች የነበሩ ወላጆቻችን ክፉ መንፈሰ /ሰይጣን/ በእባብ መልክ እስከታየበት ጊዜ የሕይወት ዛፍ ባለበት ገነት ውስጥ ይኖሩ ነበር የሚል ትውፊት አላቸው፡፡ ፈሪሳውያን ይህን ትውፊት ከአባታቸው ከያፌት ወርሰውት ይሆናል፡፡ ዕብራውያን የራሳቸውን ትውፊት ከሴም እንዳገኙ ፈሪሳውያንም ይህን ትውፊት ከያፌት አግኝተዋል፡፡
3. **ሂንዱ፡-** በመጀመሪያ ጊዜ ሰው ከክፋትና ከሕመም ነጻ ነበር፡፡ የራሱን ፍላጐት እየፈጸመ ለረኀቡም ጊዜ ይኖር ነበር፡፡
4. **ግሪክ፡-** የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በወርቃማው ዘመን ከክፋትና ከችግር ነፃ ነበሩ ደስተኞች ነበሩ ከአማልክት ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ምድርም ያለዝግጅት /ሳትታረስ/ ፍሬዋን ትሰጥ ነበር፡፡
5. **ቻናውያን፡-** የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የተትረፈረፈ ምግብ፣ የሰላም ኑሮም እንደነበራቸው ይተርካሉ፡፡
6. **መንጐላውያንና ቲቤታውያን በርበራውያንም፡-** ስለ ሰው ውድቀት ይህን የመሰለ ትውፊት አላቸው፡፡

3. ማየ አይን /ማዕበል/

ኦሪት ዘፍጥረት ከተመሠረተባቸው ምንጮች አንዱ የማየ አይህ ታሪክ ነው፡፡ የማየ አይኅ ምክንያት የሰው ልጅ ክፋት በምድር ላይ መብዛት መሆኑ በምዕራፍ 6፡5-8 ላይ ተብራርቶአል፡፡ ስለዚህም፡- እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሁሉ ለመቅጣት በሰውም ኃጢአት ምክንያት ሰው የሚጠቀምባቸውን እንስሳትን በጠቅላላ ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ፍጥረትን ሁሉ ለመደምሰስ ማየ አይህ በምድር ላይ እንዳዘነመ በምዕራፍ ስድስትና ሰባት ላይ ተተርኮአል፡፡

ማየ አይኅንም በምድር ላይ በሆነ ጊዜ ከሰማይ በታች ያሉ ተራሮች ሁሉ ተሸፈኑ። በምድር ላይ የሚንቀሳቀስ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሞተ /ዘፍ. 7፥19-21/ ይላል። ይህ ሴም ለልጆቹና ለልጅ ልጆቹ ያስተላለፈው ትውፊት ነው። ሴም ማየ አይኅ እንዳየ ተናግሮአል።

ይሁን እንጂ ዛሬ ይህን አነጋገር ሴም እንደሚያውቀው መልክዐ ምድር ልንተረጉመው እንችላለን? ወይስ እንደዛሬው መልክዐ ምድር እንደ አሪት ዘፍጥረት የታሪክ አቀራረብ ከኖህና ከቤተሰቡ በቀር የሰው ዘርእ ሁሉ በሙሉ ተደምስሶ ነበር። የተደመሰሰውም በማየ አይኅ ነበር። አሪት ዘፍጥረት ስለ ሰው ዘርእ የሚተረከውን ስንመለከት ከመጀመሪያው ሰው /ከአዳም/ ጀምሮ እስከ ኖህ እስከ ማየ አይኅ /ዐሥር ትውልድ ነበር። እንግዲህ በዐሥር ትውልድ ውስጥ የአንድ ቤተሰብእ ዘርእ በዚህ ዘመን የኤሊ ጉዞ ዓይነት ዛሬ የሰው ልጅ ያለበትን ምድር ሁሉ እንዴት ሊሞላ ይችላል? ይህም ጥያቄ ማየ አይኅ ዓለም አቀፍ ወይም አገር አቀፍ ነበር? የሚል ሌላ ጥያቄን ያስከትላል።

አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት "ማየ አይኅ ዓለም አቀፍ ነበር" ይሉና ዓለም አቀፍነቱን በሚከተለው መንገድ ይተረጉማሉ።

"በኖህ ዘመን የሰው ዘርእ እንደ ዛሬው ሳይበዛና በዛሬው ዓለም ሳይመላ በኤፍራጥስና በጤግሮስ ዙሪያ ብቻ ይኖር ነበር። ለኖህና ለልጆቹም ዓለም ሆኖ ይታወቅ የነበረው ያው ብቻ ነበር። የማይ አይኅም ዓላማ ኃጢአተኛውን ሰው ከገጸ ምድር ለማጥፋት ነበር። ስለዚህ ማየ አይኅ ዓለም አቀፍ /ዩኑቨርሳል/ ነበር በማለት በዚያ ዘመን የሰው ልጅ በሚኖርበት በኤፍራጥስና በጤግሮስ ዙሪያ ዘነመ ማለት ነው። እነዚህ ሊቃውንት፡- ለዚህ አተረጓጎማቸው ድጋፍ ወይም ማስረጃ ለመስጠት አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 41፥56-57 እና የሐዋርያት ሥራ 2፥5 ይጠቅሳሉ።

ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ደግሞ በምዕራፍ 9 ቁጥር 17 ላይ ያለውን ቃል ፊደል በፊደል በመተርጎም ማየ አይኅ በዛሬው የዓለም መልክዐ ምድር መሠረት ዓለም አቀፍ ነበር የሚለውን ሀሳብ ያጸናሉ። ለዚህም አተረጓጎማቸው ማቴ 24፥38-39 በመጥቀስ እንደዚህ ይላሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአቱን በኖህ ዘመን ከሆነው ማየ አይኅ ጋር አነጻጽሮ ተናግሮአል። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በዓለም ሁሉ እንደሚታይ ከላይ በተጠቀሰው ወንጌል ተገልጦአል። እንግዲያውስ ምሳሌው የሆነ ማየ አይኅም ዓለም አቀፍ እንደነበር በዚህ ማስተዋል ይቻላል። የቤተ ክርስቲያናችንም የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት አመለካከት ይህ ነው።

የማየ አይኅ ታሪክ በተለያዩ ዓለማት

በተለያዩ ዓለማት በብዙዎች ቋንቋዎች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የማየ አይኅ ትውፊት አለ። በተለይም በባቢሎን /በሱሜራያንና በአካጽያን/ ስለ ማየ አየኅ የሚተረከው በኦሪት ዘፍጥረት ከተተረከው ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት አለው።

ይሁን እንጂ ሁለቱም ኦሪት ዘፍጥረትና የባቢሎን ትውፊት በተመሳሳይ አካባቢ የተፈጸመውን የማየ አይኅን ታሪክ ቢያወሱም የኦሪት ዘፍጥረት ጸሐፊ የማየ አይኅን ታሪክ ከባቢሎን ማየ አይኅ የታሪክ ምንጭ አግኝቶ ጻፈ ማለት አስፈላጊ አይመስልም ምክንያቱም ሙሴ የጻፈ "በአለብዎተ መንፈስ ቅዱስ እንጂ መዛግብተ ታሪክን በመመርመር አይደለምና።

ከተለያዩ ዓለማት የተገኘ የማይ አይኅ ትውፊቶች

1. **<u>የባቢሎናውያን ትውፊት</u>**

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ300 ዓመት ቢሮስዩስ እንደጻፈው በባቢሎን በነበረው በማርዱክ ቤተ መቅደስ ቤተ መዛግብት የሚከተለው ታሪክ ተገኝቶአል።

ሂስትሮስ የተባለው ንጉሥ መርከብ እንዲሠራ፣ ወዳጆቹንና ዘመዶቹን፣ እንስሳትንም በያይነቱ ከበቂ ምግብ ጋር ይዞ ወደ መርከቡ እንዲገባ ከአማልክት አንዱ አስጠነቀቀው። ወዲያውም በአርማንያ ተራራ ላይ አርፎ ይታይ የነበረውን ታላቅ መርከብ ሠራ። ከማየ አይኅ ሕፀት በኋላ ሂስትሮስ ወፎችን ሦስት ጊዜ ከመርከብዋ ውጭ ልኮ። በ3ኛው ጊዜ ወፎቹ ሳይመለሱ ቀሩ። አለመመለሳቸውንም ባየ ጊዜ ራሱ ከመርከቡ ወጣና ምሥዋዕ ሠራ። መሥዋዕትም አቀረበ። ሌሎችም ስለማየ አይኅ የሚናገሩ ትውፊቶች በ1872 ዓ.ም /እ.ኤ.አ/ በጆርጅ እስሚዝ በነነዌ ከተማ ተገኝተዋል።

2. **<u>የግብጻውያን ትውፊት</u>፡-**

አማልክት አንድ ጊዜ ምድርን በማየ አይኅ አጸዱ። በዚያ ጊዜም ጥቂት እረኞች ብቻ በተራራ ላይ ወጥተው አመለጡ።

3. **<u>የግሪክ ትውፊት</u>፡-** ዲዮካሊዎን አማልክት ስለኃጢአቱ ብዛት በምድር ላይ ማየ አይኅን እንደሚያመጡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር። እርሱም በአርናስስ አርፎ የነበረውን መርከብ ሠራ። ሁለት ጊዜ ርግብን ላከ። በ3ኛው ጊዜ አለመመለስዋን አይቶ እርሱ ወጣ።

4. **<u>የሒንዱ ትውፊት</u>፡-** ማኑ ፍጥረትን ሁሉ ከጣፋው ከማየ አይኅ ብቻውን የሚድንበትን መርከብ እንዲሠራ ማስጠንቀቂያ ደርሶት ነበር፡፡

5. **<u>የቻይና ትውፊት</u>፡-** የቻይና ሥልጣኔ ጀማሪ የነበረው ፋሂ ከሦስት ወንዶች ልጆቹና ከሦስት ሴቶች ጋር ሰው በሰማይ ላይ በማመጹ ምክንያት ከመጣው ማየ አይኅ ዳነ፡፡

6. **<u>ኢንግላንድ</u>፡-** እንግሊዞች፡- ዓለም ሰውን ሁሉ በኃጢአቱ ምክንያት ለማጥፋት ከሁሉ በላይ ከሆነው አምላክ ከተላከው ማየ አይኅ ከዳነው ጻድቅ ፓትርያርክ /ታላቅ አባት/ እንደገና በሕዝብ ተመላች፡፡

7. **<u>የሜክሲኮ ትውፊት</u>፡-** በምድር ላይ ከዘነመው ማየ አይኅ አንድ ሰው ሚስቱና ልጆቹ በመርከብ ዳኑ፡፡

8. **<u>የአሜሪካ ሕንዶች</u>፡-** አሜሪካውያን ሕንዶች የተለያዩ አፈ ታሪኮች አሉአቸው፡፡ አንዱ፣ ሦስት ወይም ስምንት ሰዎች በጀልባ ውስጥ በከፍተኛ ተራራ ላይ ሆነው ከማየ አይኅ ዳኑ ይላሉ፡፡

9. **<u>የግሪንላንድ ትውፊት</u>፡-** አንድ ጊዜ ምድር ተናውጦ ነበር፡፡ ምድርን እንደገና ከሞሉአት ከአንድ ወንድና ከአንዲት ሴት በቀር ሰዎች ሁሉ ተደምስሰው ነበር፡፡

10. **<u>ፐርሻውያን</u>**፡- አንድ ሰውና ሚስቱ በሳጥን ውስጥ ሆነው ከማየ አይኅ ዳኑ፡፡

ስለ ማየ አይኅ በተለያዩ ሀገሮች የተለያዩ ሌላም ትወፊት ሊኖር ይችላል ሁሉም ትውፊት የሚያመለክተው የማየ አይኅን እርግጠኛ ታሪክ ነው፡፡ በሌላም በኩል ዓለም አቀፍነቱን ያረጋግጣል፡፡

4. <u>ባቢል /ጥቅመ ሰናያር</u>

ከማየ አይኅ በኋላ ዓለም፡- አዲስ ኑሮ ጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ለኖህ በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት /9፥1-3/ የሰው ዘር መብዛት መባዛት ቀጠለ፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ በመሄድ ፈንታ እግዚአብሔርን ለመከላከል ታላቅ ግንብ ይሠሩ ጀመር፡፡ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ የሆነ ሰፊ መንግሥት ማቋቋም እንዳለባቸው አሰቡ፡፡ ለስማቸውም ማስጠሪያ ይሆን ዘንድ ግንብ ለመሥራት ተነሡ፡፡

እግዚአብሔር ይህን አሳባቸውን ተመልክቶ ቋንቋቸውን ደባለቀ፡፡ በየሀገሩም በተናቸው /ምዕ 11፥1-9/፡፡ ይህም የሆነው ከማየ አይኅ በኋላ በ4ኛው ትውልድ በመዋዕለ ፋሌቅ በ11 ዓመት /ዜና 10፥25/ ከአብርሃም መጠራት በፊት በ326 ዓመት /ዘፍ 10፥26/

ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ የሰው ዘር በሦስቱ የኖህ ልጆች በሴም በካምና በያፌት አማካኝነት የተለያየ ቋንቋ በመናገር በነገድ ተከፈለ፡፡ ደቂቀ ሴም በዓረብያና በስተምስራቅ ሰፈሩ ደቂቀ ያፌት በአውሮጳ ሰፈሩ ደቂቅ ካም በአፍሪካ ሰፈሩ ታላቁ የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ጥቅመ ሰናያር የተገነባው ሕዝቡ ለእግዚአብሔር መገዛትን /አንቲኩቲ 2/የእግዚአብሔር ዓላማ ሰው እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰው ራሱን በራሱ ለማክበር ሞከረ፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታታይ ውድቀት /1 በአዳም 2 በኖህ 3 ከኖህ በኋላ በዝርወተ ባቢሎን ጊዜ ደረሱበት፡፡

5. <u>አበው /አባት ፓትርኬይ/</u>

የኦሪት ዘፍጥረት አብዛኛው ክፍል የተመሠረተ በአበው ታሪክ ላይ ነው፡፡

በዕብራይስጡ አቦት የሚለው ቃል እንደ ግእዙ አሻሚ ነው፡፡ ለሁሉም ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ የሕዝበ እስራኤል ቅድመ አያቶች ሁሉ አቦት ተብለው ይጠራሉ፡፡ ይህም በነቢያት ብዙ ጊዜ ተነግሮአል /ኤር 7፥14-22-26፣ 11፥7-10-13 ሕዝ. 20፥1-8/ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብም መጠሪያ ነው ጦቢት 4፥12 4ኛው መቃብያን 7፥19፣16-25፣ ዕብ. 7፥14/ አሥራ ሁለቱ ደቂቀ ያዕቆብም በዚሁ ስም ተጠርተው ይገኛሉ፡፡ /የሐዋ. 7፥8-9/

ነገር ግን በግሪኩ ፓትርያርኬይ የሚለው ሥም የሚያመለክተው በተለይ ሦስቱን አብርሃም ይስሐቅን ያዕቆብንና አሥራ ሁለቱን ነገደ እሥራኤልን ብቻ እንጂ እንደ ዕብራይስጡ አቦትና እንደ ግእዙ አበው ሕዝበ እስራኤልን ሁሉ አያመለክትም፡፡ ፓትርያርኬይ ማለት አርእስተ አበው ማለት ነው፡፡

ከእስራኤል ሕዝብ መመረጥ በፊት አበው ወይም አርእስተ አበው የሚባሉ ሦስቱ አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ሲሆኑ ከዚያ በፊት የዓለም ሕዝብ ሁሉ አባቶች ተብለው የሚጠሩ ሌሎች ናቸው፡፡ እነዚህም ቅድመ ማየ አይኅና ድኅረ ማየ አይኅ የነበሩ አበው ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

1. <u>ቅድመ ማየ አይኅ የነበሩ አበው</u>

ኦሪት ዘፍጥረት ቅድመ ማየ አይኅ ስለነበሩት አበው ሁለት ሐረገ ትውልድ ያመለክታል፡፡ አንደኛው በቃየን መስመር የወረደው ሐረገ ትውልድ ነው፡፡ ይህም በምዕራፍ 4፥16-18 ተገልጧል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በአቤል ፈንታ በተወለደው በሴት መስመር ያለው ሐረገ ትውልድ ሲሆን በምዕራፍ 5፥6-27 ተገልጧአል፡፡ ሁለቱም ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ተመሳሳይ ስሞችን ይዘረዝራሉ፡፡ የስም አጠራራቸው ቅደም

ተከተል አንድ ነው። ሁለቱም በላሜህ ይደመድማሉ። ሁለቱም ከላሜህ በኋላ ባለው ትውልድ የተጀመረውን የሰው ልጅ ሥልጣኔ ይገልጣሉ። በእነዚህ ሁለት ሐረጎች በኩል 14 አበው ይገኛሉ። ከእነዚህም ስድስቱ የቃየን ዘር፣ ስምንቱ የሴት ዘር አባቶች /አበው ናቸው።

2. ድኅረ ማየ አይኅ የነበሩ አበው

ከማየ አይኅ በኋላ ከአብርሃም ጥሪና ምርጫ አስቀድሞ የነበሩት አበው ከኖህ እስከ አብርሃም ያሉት ናቸው። እነዚህም በሴም ሐረግ ትውልድ የወረዱ ሲሆኑ ቍጥራቸውም ዐሥር ነው። /ዘፍ. 11÷10-26/ አብርሃም ከተጠራና የዕብራውያን ነገድ ከተመረጠ በኋላ ግን አበው በመባል የሚታወቁት አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ናቸው። አበውነታቸውም ለዕብራውያን ነገድ ለተመረጠው ሕዝብ /ብቻ ነው። እነዚህ ሦስት አበው መባል ብቻ ሳይሆን የግሪኩ ቃል ፓትርያርኬይ እንደሚያመለክተው አርእስተ አበውም ይባላሉ።

አርእስተ አበው

አርእስተ አበው የነበሩበት ዘመን ከመቸ እስከ መቼ እንደነበረ በትክክል ለማወቅ ቢያስቸግርም ከ1900 ቅ.ል.ክ እስከ 1500 ቅ.ል.ክ እንደነበረ ሊቃውንት ገምተዋል።

አርእስተ አበው፡- እንደ ዘላን ከሀገር ሀገር በመዘዋወር ከመሴጴጦምያ እስከ ግብጽ ይኖሩ ነበር። በመዘዋወር ከኖሩባቸው ሀገሮች ወይም ከተሞች አንዳንዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰዋል። እነርሱም፡- ዑር /ዘፍ 11÷28፣ 31÷15፣7/ ካራን /ዘፍ. 11÷31–32፣ 12÷4-5 27÷43፣ 28÷10፡ 29÷4/ ሴኬም /ዘፍ. 12÷6፣ 33÷18/ ሳሌም /ኢየሩሳሌም /ዘፍ. 14÷18/ ጌራራ /ዘፍ 20÷1-6/ ዶታይን /ዘፍ 37÷17/ ኬብሮን /ዘፍ 13÷18፣ 23÷2-29፣ 35÷27/ ቤቴል /ዘፍ. 12÷8/ በአርእስተ አበው ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ሁሉ ከሀገር ወደ ሀገር በመዘዋወር መኖራቸው በታሪክ ተረጋግጦአል።

ከዚህም ሌላ፡- አርኬዎሎጂስቶች እላይ በተጠቀሱት ቦታዎች የቍፋሮ /የአርኪዎሎጂ/ ጥናት ባደረጉ ጊዜ የእነ አብርሃም ታሪክ ተገኝቶአል። በ1935 ዓ.ም እ.ኤ.አ በኤፍራጥስ አካባቢ ማሬ በተባለው /ቴል ሀሪር/ ከ20.000 በላይ የሆኑ የጡብ ሠሌዳዎች በአርኬዎሎጂስቶች ተገኝተዋል። እነዚህም ከ2.000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፉ እንደነበሩ በአርኬዎሎጂስቶች ፍለጋ ተደርሶበታል። እነዚህ ሠሌዳዎች መጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤላውያን ቅድመ አያቶች ከምድረ ካራን እንደመጡ የሚናገረውን ታሪክ አረጋግጠዋል።

በማሬ በተገኘው በሸክላ ሠሌዳ ላይ በክዬኒፎርም አጻጻፍ የተጻፉት ናክሁር፣ ታራክሂ፣ ሰፋሂ እና ፋሌቃ የተባሉት ስሞች በአብርሃም ዘመዶች ከናኮር፣ ከታራ፣ ከሴፋግና ከፋሌቅ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው።።

በዘፍጥረት 14፥6 ላይ የተጠቀሱት ሐራውያን፡- ኑዙ /ዩርጋንቲፖ/ በተባለች ከተማ ይኖሩ እንደነበር አርኪዎሎጂስቶች አረጋግጠዋል።። በዚችም ከተማ ከ1925-1931ዓ.ም /እ.ኤ.አ የአርኪዎሎጂ ጥናት ብዙ የሸክላ ሠሌዳዎች ሊገኙ ችለዋል።። በሠሌዳዎችም ላይ የኑዙን ነዋሪዎች ባህል፣ ልማድና ሥርዐት የሚያመለክት ጽሑፍ ተጽፎአል።። ይህም ጽሑፍ በአሪት ዘፍጥረት ስለ አርአስተ አበው የተነገሩትን አንዳንድ ታሪኮች በትክክል ይመስላል።። ለምሳሌ፡-

1. በኑዙ አንድ ልጅ የሌላቸው መካኖች በሕይወታቸው የሚያገለግላቸው፣ ሲሞቱ የሚያለቅስላቸውና የሚቀብራቸው የሞጋሳ /የጡት/ ልጅ የመያዝ ልማድ ነበር።። የሞጋሳው ልጅ የውርስ መብት ነበረው።። ነገር ግን መካኖች ቆየተው ልጅ ቢወልዱ የማደጐው ልጅ ለእውነተኛው ልጅ መብቱን ሁሉ ይለቃል።። /ዘፍ. 15፥1-4/።።
2. ሚስትየዋ መካን ብትሆን ለመካንዋ ሚስት በቤት ውስጥ ገረድ ብትኖራት ገረድዋን ለባልዋ አሳውቃ ልጅ እንድትወልድለት የማድረግ ልማድ በኑዙ ነዋሪዎች ዘንድ ነበር።። /ዘፍ. 16፥2/ እነዚህ ከኑዙ ከተማ ባድማ ላይ በቁፋሮ የተገኙ መረጃዎች ሁሉ በአብርሃምና በሣራ ላይ የተፈጸሙትን ደርጊቶች የሚያረጋግጡ መሆናቸው አያጠራጥርም።። በሌላ በኩል ደግሞ፡- “አብርሃም አምሳላዊ የድራማ ሰው አንጂ በዚህ ዓለም የነበረ አማናዊ ሰው አይደለም” በማለት የተቹትን የእንጂልየስ ዌልሀውሴን አስተያየትን ያፈርሳል።። ይህ ብቻ አይደለም።። አብርሃም በቤተ አይሁድም ሆነ በቤተ ክርስቲያን፣ እንደዚሁም በዓለም የታሪክ ዐምድ ታሪካዊ ሰው መሆኑ በትክክል ይታመናል።። ስለ እርሱም በዘፍጥረት የተነገረው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ምሥክርነት ተረጋግጦአል።።
3. በኑዙ ከተማ ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች መካከል ቶቤል የተባለው አንድ ሰው የብኩርና መብቱን ሁሉ በ3 በጎች ለወንድሙ ኩርፖዛ መሸጡ በኑዙ ከተማ ፍርስራሽ ላይ አርኪዎሎጂ ምርመራ ከተገኙት ሠሌዳዎች በአንዱ ላይ ተጽፎ ተገኝቶአል።። ይህም፡- ኤሣው ለወንድሙ ለያዕቆብ ብኩርናውን በምስር ወጥ ከመሸጡ ጋር ይመሳሰላል።።

4. በኑዙ ከተገኙት የጡብ ሠሌዳዎች መካከል ሌላው ሠሌዳ ደግሞ የሚከተለውን ይተርካል፡፡ ከኑዙ ነዋሪዎች አንዱ ናሽዋ የተባለው ሰው ውሉ የተባለ አንድን ልጅ በማደጐ አሳደገ፡፡ ናሽዊ ሴት ልጁን ለውሉ ዳረ፡፡ ናሽዊ በሚሞትበት ጊዜ ውሉ በኑዙ ልማድ መሠረት የናሽዊ ሊሆን ነው፡፡ ናሽዊ ወንድ ልጁ ቢወልድም ውሉ ከሌሎች ወራሾች ጋር ተካፋይ ሊሆን ግድ ነው፡፡ ዋናው ወይም እውነተኛው ልጅ ግን የናሽዊን አማልክት ይወርሳል፡፡ አማልክቱንም መውሰድ የቤተሰቡ የበላይነቱን ያመለክታል፡፡

ከአርስተ አበው የአንዱ የያዕቆብ ሚስት ራሄል የአባትዋን የላባን ተራፊም መውሰድም /ዘፍ. 31፥19-35/ ከኑዙ ነዋሪዎች ታሪክ ጋር ይነጻጸራል፡፡

የአርእስተ አበው ባህል ልማድና ሥርዐት በዘመናቸው ከነበረው ጎብረተሰብ ባሕል ልማድና ሥርዐት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን ስሞቻቸውም በአርኪዎሎጂ ከተገኙት ስሞች ጋር ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ካራን /ዘፍ. 11፥34፣ 12፥4/ በአብርሃም ዘመን የአሞራውያን ማዕከላዊ ቦታ እንደነበር ታውቋል፡፡ አብርሃም የሚለውም ስም በአሞራውያን አጠራር አብአሞራን ያዕቆብ የተባለውም ስም ያቆበኤል ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ብንያምም በአሞራውያን ዘንድ የአንድ ነገድ ስም ነበር፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው፡- በአርኪዎሎጂ የተገኙት መረጃዎች ሁሉ በዘፍጥረት የተጻፈውን ታሪክ ከማረጋገጣቸውም በላይ የአርእስተ አበው አማናዊና ታሪካዊ ሕልውና ያስረዳሉ፡፡

<u>አከፋፈሉ</u>

ኦሪት ዘፍጥረት ከታሪኩ ቅደም ተከተል መስተካከል የተነሣ ለአከፋፈል አያስቸግርም፡፡ ስለዚህም ባጭሩ በአራት ዐበይት ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን፡፡

ሀ. <u>ቅድመ ታሪክ ምዕራፍ 1፥1-11-32</u>

1. ምዕራፍ 1፥2 የዓለምና የሰው ዘር ታሪክ
2. ” 2፥4-25 የወንድና የሴት ተፈጥሮ
3. ” 3፥1-24 ውድቀት
4. ” 4፥1-16 ቃየንና አቤል
5. ” 4፥17-26 ትውልደ ቃየን
6. ” 5፥1-32 ትውልድ ከአዳም እስከ ኖህ
7. ” 6፥1-22 ስለማየ አይኅ መቅድም

8. ” 7፥1-8፣22 ማየ አይኅ /የጥፋት ውኃ/

9. ” 9፥1-17 ኪዳነ ኖህ

10. ” 9፥18-27 ደቂቀ ኖህ

11. ” 10፥1-32 የምድር እንደገና በሕዝብ መሞላት

12. ” 11፥1-9 ጥቅመ ባቢል /ሰናዖር/

13. ” 11፥10-26 ትውልደ ሴም

14. ” 11፥27-32 ትውልደ ታራ /የትውልድ መደምደሚያ/

ለ. ርእሰ አበው /ፓትርያርክ/ አብርሃም/ ምዕራፍ 12፥1-25፣18

1. ምዕራፍ 12፥1-9 የአብርሃም ጥሪ

2. ” 12፥10-20 አብርሃምና ሣራ በግብጽ

3. ” 13፥1-18 የአብርሃምና ሎጥ መለያየት

4. ” 14፥1-24 አብርሃምና 4 ነገሥታት

5. ” 15፥1-20 የተስፋዎች እንደገና መታደስ

6. ” 16፥1-32 የአጋር መሰደድ /መባረር/

7. ” 17፥1-27 በግዝረት ምልክትነት የተሰጠ ኪዳን

8. ” 18፥1-9፣38 አብርሃም ልጅ እንደሚያገኝ የተሰጠው ተስፋ ሰዶምና ገሞራ

9. ” 20፥1-18 አብርሃምና ሣራ በጌራራ

10. ” 21፥1-21 ይስሐቅና እስማኤል

11. ” 21፥22-34 አብርሃምና አቤሚሊክ

12. ” 22፥1-24 የይስሐቅ መሥዋዕትነት

13. ” 23፥1-20 የአብርሃም መካነ መቃብር መግዛት

14. ” 24፥1-67 የይስሐቅ ሚስት

15. ” 25፥1-18 ትውልደ እስማኤል

ሐ. አርእስተ አበው ይስሐቅና ያዕቆብ ምዕራፍ 25፥19-36፣43

1. ” 34፥1-31 የዲና መጠለፍ

2. ” 35፥1-29 ያዕቆብ በቤቴል

3. ” 36፥1-43 ትውልደ ኤሣው

መ. የዮሴፍ ታሪክ /ምዕራፍ 37፥1-50፣26/

1. ምዕራፍ 37፥1-36 የዮሴፍ ልጅነትና ወደ ግብጽ መሸጡ
2. ” 38፥1-30 ይሁዳና ትእማር
3. ” 39፥1-23 የዮሴፍ ፈተናዎች
4. ” 40፥1-23 ዮሴፍ የእስረኞችን ሕልሞች መተርጐም
5. ” 41፥1-57 ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልሞች መተርጐሙ
6. ” 42፥1-38 ዮሴፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር መገናኘቱ
7. ” 43፥1-34 ሁለተኛው የግብጽ ጉዞ
8. ” 44፥1-34 ይሁዳ ስለብንያም ያደረገው ተማሕጽኖ
9. ” 45፥1-28 ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ መግለጡ /ማሳወቁ/
10. ” 46፥1-34 ወደ ግብጽ የያዕቆብ ጉዞ
11. ” 47፥1-31 ዕብራውያን በግብጽ
12. ” 48፥1-22 ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ኤፍሬምና ምናሴን እንደራሱ ልጆች መቍጠር
13. ” 49፥1-33 የያዕቆብ በረከቶች
14. ” 50፥1-26 የያዕቆብ ወደ መቃብር መውረድ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ፊጽሞ ይቅርታ ማድረጉና የመጨረሻ ተግባሩ፡፡

ማጠቃለያ

- ለቅዱሳት መጻሕፍት የመጀመሪያ ለሆነው የኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ሥያሜ የተወሰደው በመጽሐፉ አንደኛ ምዕራፍ መጀመሪያ ቁጥር ካለው መነሻ ቃል ነው፡፡
- የሥነ ፍጥረት ታሪክ ፀሐፊ ሙሴ መሆኑን በአይሁድና በጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዛሬዎቹም ብዙ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡
- ኦሪት ዘፍጥረት ስለማናቸውም ነገር መጀመሪያ ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ የዘፍጥረት መጽሐፍ ሥለ ስነ ፍጥረት በመተረክ ቢጀምርም ስለ ፍጥረታት፣ ፈጣሪ ግን በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከማለት በቀር ምንም ዓይነት ዝርዝር ሁኔታ አይሰጥም፡፡
- የኦሪት ዘፍረት አብዛኛው ክፍል የተመሠረተው በአበው ታሪክ ላይ ነው፡፡

የኦሪት ዘፍጥረት የሙከራ ጥያቄዎች

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ ከኦሪት ዘፍጥረት አንብበህ በተረዳኸው መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር የፅሑፍ መልስ ስጥ

1. የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው መጽሐፍ ሥያሜ የተወሰደው ከየት ነው?
2. የኦሪት ዘፍጥረት ፀሐፊ ሙሴ መሆኑን የሚያስረዱ ነጥቦችን አብራራ?
3. የዘፍጥረት መጽሐፍ የማይናገረው አጀማመር ስለማን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው የሚናገው ስለማንነው?
5. እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ከፍተኛ ክብር ያለው ሰው ነው ለምን ተባለ?
6. የፍጥረት አፈጣጠር እንዴት እንደሆነ ግለጽ?
7. የሰው ውድቀት የመነጨው ከየት ነው?
8. በዓለም በሚኖሩ የተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ታሪክና ትውፊት ስለማየ አይጎ የተፃፈው ታሪክ የሚያስረዳው ምንድነው?
9. በሰው ልጅ ላይ ተከታታይ ውድቀት ለምን ደረሰ?
10. የዕብራውያን ነገድ ከመመረጡ በፊትና ከተመረጠ በኋላ አበው በመባል ሥለሚታወቁት ግለጽ?
11. የኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ በስንት ይከፈላል?

ኦሪት ዘጸአት

መግቢያ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ በዚህ በኦሪት ዘፀዓት መጽሐፍ ያለው ታሪክ ምንባብ በውስጡ ያለው ምሥጢርና ትርጉም ከዚህ በታች በተዘጋጀው መሠረት ቀርቦልሃል ተመልከተው፡-

- ስለ መጽሐፍ ሥምና ሥያሜ፣
- ስለ መጽሐፍ ፀሐፊ፣
- በኦሪት ዘፀዓት የሚገኙ ጎብረ አምሳላት /ታይፖሎጂዊ/፣
- ስለ ፀዓተ ግብፅ፣
- ከግብፅ የተገኙ መረጃዎች፣
- ከአዳምና ከሞዓብ የተገኘ መረጃ፣
- ከከነዓን የተገኘ መረጃ
- ስለ ሙሴ
- የእግዚአብሔር ሥም ስለመገለጥ፣
- ለሙሴ የተገለጠው ምን ነበር?
- ስለ አስሩ መቅሰፍቶች፣
- ስለ ፋሲካና ዝግጅቱ አፈጻፀም፣
- ስ ለቃል ኪዳን /መጽሐፍ ኪዳን/
- ስለ ዐሥርቱ ትዕዛዛት አቆጣጠር፣
  - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር፣
  - የዮሴፍ ወልደ ኮርዮን /የአይሁድ አቆጣጠር/፣
  - የአውግስጢኖስ /የካቶሊክ/ አቆጣጠር፣
- ዐሥርቱ ትዕዛዛት በሁለት ይከፈላሉ፣
- ከዐሥርቱ ትዕዛዛት ቀጥሎ ስላሉት ሌሎች ሕጐችና ይዘት፣
- ስለ ደብተራ ኦሪት፣
- ስለ ደብተራ ኦሪት የተለያየ አሠራር፣
- የደብተራ ኦሪት ክፍሎችና በውስጧ ያሉ የተለያዩ ንዋያት፣
- በቅድስተ ቅዱሳን ወስጥ ስለሚቀመጡ ንዋያት፣

- ስለ ኦሪት ዘፀዓት መጽሐፍ አከፋፈል ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ድረስ፣

ግልጥ በሆነ መንገድ ተብራርቶ ቀርቧል ተመልከተው ብዙ ማስተዋልን ታተርፍበታለህ፡፡

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

ሁለተኛው የመሴ መጽሐፍ በዕብራይስጥ “ወኤሌህ ሼሞት” ወይም በአጭሩ “ሸሞት” ይባላል፡፡ ይኸውም “ወአለ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ቦኡ ብሔረ ግብጽ” ከሚለው ከመጽሐፉ መጀመሪያ ምዕራፍ ከቍጥር አንድ ላይ የተወሰደ ነው፡፡ ሰባው ሊቃናት ግን ጠቅላላ የታሪኩን ይዘት በመመልከት “ኤክሶዶስ” ብለውታል፡፡ ይህም መውጣት ማለት ነው ከዚህ በኋላ ማንኛውም የብሉይ ኪዳንን ትርጉም ስያሜ ተከትሎአል፡፡ በእኛም ትውፊት የግእዙም ሆነ የአማርኛው የብሉይ ኪዳን ትርጉማችን የሰብዓው ሊቃናትን ስያሜ በመከተል “ዘጸአት” ይላል፣ ይኸውም የአወጣጥ፣ ወይም የመውጣት መጽሐፍ ለማለት ነው፡፡ ዘጸአት በዘፍጥረት ለተነገረው ታሪክ ተከታታይ መጽሐፍ ቢሆንም ለሕጉ ግን የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው፡፡

ጸሐፊው

የኦሪት ዘጸአት ጸሐፊ፡- በአይሁድም ሆነ በክርስቲያኖች ትውፊት ሙሴ ነው /ጥበበ ሲራ 45፥1-7/፡፡ ከዚህም ጋር በውስጡ የሚገኙ ማስረጃዎች በዚህ መጽሐፍ ያለውን ታሪክ ሁሉ ሙሴ እንደጻፈው ያረጋግጣሉ፡፡ /ዘጸ. 17፥14-24፣4፥34፣27/ ነገር ግን በኦሪት ዘጸአት መግቢያ ላይ ያለው የሙሴ የልደቱና የአስተዳደጉ ታሪክ /ዘጸ. 2፥1-10/ በዘሌዋውያን ደግሞ የክህነትና የመሥዋዕት ወይም የሃይማኖት ሕግ ተዘርዝሮ ተገልጦአል፡፡ በደብረ ሲና የተነገረው ታሪክ ሁሉ የተጻፈው በሁለቱ በዘጸአትና በዘሌዋውያን ስለሆነ በአንድ የተጀመረው በሁለተኛው ተፈጽሞአል፡፡

በኦሪት ዘጸአት የሚገኙ ጎብረ አምሳላት /ታይፖሎጂዊ/

በኦሪት ዘጸአት የተተረኩት ታሪኮች ሁሉ ብዙ ጎብረ አምሳልነት አላቸው ይህም ጎብረ አምሳል የክርስቶስን የአድኅኖት ሥራ ይገልጣል፡፡ ለምሳሌ የእስራኤል ከግብጽ መውጣትና ከፈርዖን አገዛዝ መላቀቅ ነፍሳት ከሲኦል የመውጣታቸውና ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ የመሆናቸው አምሳል ነው፡፡ በደብረ ሲና በተሰጠው ቃል ኪዳን እስራኤል ዘሥጋ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ እንደተባሉ፡- በክርስቶስ ደም በተሰጠው ሐዲስ ኪዳንም እስራኤል ዘነፍስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ሆነዋል፡፡ ነቢዩ ሆሴዕ የእስራኤል

ልጆች በምድረ ግብጽ በስደት ኖረው መመለሳቸውን በመመልከት የተናገረውን ቃል፡- ቅዱስ ማቴዎስ ክርስቶስ በግብጽ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በስደት ቆይቶ ለመመለሱ ምሳሌና ትንቢት አድርጐ ጠቅሶታል /ሆሴ. 11፥1፣ ማቴ 2፥15/፡፡ እስራኤል ቀይ ባሕርን ተሻግረው ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ መኖራቸውን ክርስቶስ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ በገዳም ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት ለመቆየቱ ምሳሌ አድርገው የተረጐሙ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አበው አሉ፡፡

እስራኤል ከሞተ በኩር በዳኑበት በግዕ ፋሲካ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደውን ነዋ በግው ለእግዚአብሔር የተባለውን ክርስቶስን ያመለክታል /ዘጸ. 12 ዮሐ. 1፥29/

እስራኤል ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ የተመገቡት መና የጠጡት ውኃ ለክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ነበር /ዮሐ. 6፥47-58 ራእ. 21፥17/፡፡ እስራኤል ይጠጡት የነበረው ውኃ የፈለቀላቸው ከአንድ ዐለት ነበር፡፡ ያም ዐለት የክርስቶስ ምሳሌ ነበር /ዘጸ. 17፥6 1ቆሮ. 10፥4/ በቀን ከፀሐይ ይከልላቸው ከጠላት ይሰውራቸው የነበረው ዐምደ ደመና በሌሊት ያበራላቸው የነበረው ዐምደ እሳት የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፡፡ /ዘፀ 13፥20-22/፡፡ ሙሴ እጆቹን ዘርግቶ ለእስራኤል አንድ ቀን ሙሉ መጸለዩ ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ ለድኅነተ ዓለም መሰቀሉን ያሳያል፡፡ /ዘዳ. 17፥8-13/ ሙሴ ራሱ በብዙ መንገድ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፡፡

ከዚህም ሌላ የቤተ ክርስቲያን አበው ደብተራ ኦሪትንና በውስጥዋ የሚገኙትን ንዋያት የድንግል ማርያምና የክርስቶስ አምሳላት አድርገው ተርጉመዋቸዋል፡፡ ከነዚህም ጥቂቶችን እንደሚከተለው በማስቀመጥ እንመለከታለን፡፡

የድንግል ማርያም	የክርስቶስ
ደብተራ	/ዘፀ. 25፥26/
መንጦላዕት	
ቅድስተ ቅዱሳን	
ታቦት	
መሶበ ወርቅ	ጽሌ
ተቅዋመ ወርቅ	ማኅቶት
ማዕጠንተ ወርቅ	ፍሕም
በትረ አሮን	ፍሬ
ኅሞር	መና

ጸዓተ ግብጽ

እስራኤላውያን ከግብጽ መቼ ወጡ? እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበትን ትክክለኛውን ጊዜ ለይቶ ለማወቅ ያስቸግር ይሆናል። ምክንያቱም የኦሪት ዘጸዓት ጸሐፊ ጊዜውን ለይቶ አልመዘገበውምና ነገር ግን ድርጊቱ የተፈጸመበትን ክፍለ ዘመን አካባቢ ለመገመት ተችሎአል። ለዚህም ዓይነት ማስረጃዎች አሉ።

1. ከኦሪት ዘጸአት የተገኘው ማስረጃ
2. በአርኬዎሎጂስቶች ምርመራ የተገኘው ማስረጃ

አርኪዎሎጂስቶች በጥንት ዘመን ሰዎች የተደረጉ ነገሮችን ሁሉ ይመረምራሉ የሕንጻዎችን፣ የሸክላዎችን፣ የሐውልቶችን፣ የቅርጻቅርጾችን፣ የጽሑፎችንና የሌሎችንም የጥንት ቅርሶች ቅሪት ወይም ፍርስራሾችን ያጠናሉ። በዚህም መሠረት በግብጽና በከነዓን ጥንታውያን ነገሮችን የሚቆፍሩ ሊቃውንት ሕዝበ እሥራኤል ከግብጽ መቼ እንደወጡ ለመወሰን የሚረዱ ብዙ መረጃዎችን አግኝተዋል።

ሀ. ከግብጽ የተገኙ መረጃዎች

በዘጸአት 1÷11 ላይ የጠቀሰው የዳግማዊ ራምሴ ሕንፃ

የዚህ ሕንጻ ፍርስራሾች በ1930 /እ.ኤ.አ/ በተቈፈሩ ጊዜ የዳግማዊ ራምሴ ስም የተጻፈባቸው የሐውልታትና የአዕማድ ስብርባሪዎች ተገኝተዋል። አንድ የትምህርት ቤት ሰውም የራምሴ ከተማ ተወዳዳሪ የሌላት እጅግ በጣም ውብ እንደሆነች ገልጦ ለመምህሩ የጻፈውም ደብዳቤ በዚሁ በራምሴ ሕንጻ ፍራሽ ተገኝቶአል። በ1304 - 1280 ቅልክ ዳግማዊ ራምሴ ከተማውን ለማሠራት ያስገድዳቸው ከነበሩ ብዙ ሕዝቦች መካከል ዕብራውያን ነበሩ።

በ1220 ቅልክ ንጉሥ ሜርናፕታህ ሊብያን ድል እንዳደረገ የሚገልጠው ጽሑፍ በዚሁ ዘመን ዕብራውያን በከነዓን /በፍልስጥኤም/ እንደነበሩ ያሳያል።

እንግዲህ ከግብጽና ከኦሪት ዘጸአት በተገኘው መረጃ መሠረት ጸዓተ እስራኤል ከ1290 ቅልክ በኋላ ከ1220 ቅልክ በፊት መሆኑ ነው።

ለ. ከዔዶምና ከሞዓብ የተገኘ መረጃ

እስራኤላውያን ወደ ከነዓን በሚሄዱበት ጊዜ በነገሥቱ ዔዶምና በነገሥቱ ሞዓብ በተያዙ ሀገሮች በኩል አልፈው ነበር /ዘኍል. 21÷22/ የሞዓባውያንንና የዔዶማውያንን

የታሪክ ቅሪት ያጠኑ አርኪዎሎጂስቶች የዔዶምና የሞዓብ መንግሥታት እስከ 1300 ቅልክ እንዳልተመሠረቱ መርምረዋል፡፡ እስራኤላውያን ከ1300 ቅልክ ከግብጽ ከወጡ በዚያ አካባቢ የተቋቋሙ መንግሥታት ሊያገኙ አይችሉም ነበር፡፡

ስለዚህ ከዔዶምና ከሞዓብ የተገኘው መረጃ በዘኁልቁ ከተመለከተው ፍንጭ ጋር፡- ነገደ እስራኤል ከ1300 ቅልክ በኋላ ከግብጽ እንደወጡ ለመገመት ያስችላል፡፡

ሐ. ከከነዓን የተገኘ መረጃ

አርኬዎሎጂስቶች በከነዓን ብዙ ከተማዎችን ቁፍረዋል፣ በቍፋሮም በወጡት ሸክላዎች ሕንጻዎች አዕማድና ሐውልታት ላይ በተገኙት ጽሑፎች አማካኝነት ከተሞቹ መቼ እንደተሠሩና መቸ እንደተደመሰሱ አካባቢውን ዘመን ለመገመት ችለዋል፡፡

ከ1250-1220 ቅልክ ብዙ የከነዓን ከተማዎች በአደጋ ምክንያት እንደተደመሰሱ ብዙዎ መረጃዎችን አግኝተዋል ከእነዚህም ከተማዎች መካከል ቤቴል፣ ዳቤር፣ ላኪ ሻና፣ ሐዶር ይገኙባቸው ነበር መጽሐፈ ኢያሱ ደግሞ እሰራኤላውያን እነዚህን ከተማዎች መማረካቸውን ይጠቅሳል፡፡ ለምሳሌ፡- ኢያሱ 10፥38 በዳቤር ላይ የተጣለውን አደጋ ይናገራል፡፡ አርኬዎሎጂስቶች የዳቤርን ፍራሽ በቆፈሩ ጊዜ የከነዓናውያን ከተማ ቅርጸችን በአመድ ተሸፍነው አግኝተዋቸዋል፡፡ በዚህም፡- ከተማው በጠላት ተወርሮና በእሳት ተቃጥሎ እንደነበር የሚያሳይ መረጃ ተገኝቶአል፡፡ በተቃጠለውም ባድማ ላይ እስራኤላውያን ከትመው ሠፍረው እንደነበር አርኬዎሎጂስቶች መርምረው ደርሰውበታል፡፡

እንግዲህ ከመጽሐፈ ኢያሱ ጥቅስ ጋር ከከነዓን በተገኘው መረጃ መሠረት እስራኤላውያን ከ1250-1220 ቅልክ ባለው ዘመን ውስጥ ከነዓንን ወርረው እንደነበር ግልጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት በሲና ምድረ በዳ 40 ዓመት መቆየታቸው ተጽፎአል፡፡ /ዘኁ. 10፥11-12 ዘዳ. 2፥14 መዝ. 94፥10/ ይህ በእንዲህ እንዳለ የእስራኤል ወደ ከነዓን መግባት ከ1250-1240 ቅልክ ከሆነ ከ1290-1220 ቅልክ ባለው ጊዜ የእስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው /የጸዓት ግብጽ/ ዘመን አካባቢ ነው ተብሎ በብዙዎች ሊቃውንት ዘንድ ታምኖበታል፡፡

የኦሪት ዘጸዓት ምንጮች

ኦሪት ዘጸዓት በብዙ አስደናቂ ታሪኮችና ተአምራት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እስራኤላውያን ከግብጽ ለመውጣት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ከተነሡበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ ተአምራት ተደርገውላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ለእስራኤል መሪ ለሙሴ

ባደረገው ልዩ መገለጥ /አስተርእዮ ብዙ ድንቅ ሥራዎች ተፈጽመዋል፡፡ ልዩ ልዩ መመሪያ ሕጐችና ሥርዓቶች ተሰጥተዋል፡፡ ኦሪት ዘጸአት የተመሠረተው በእነዚህ ላይ ነው፡፡ እነዚህንም እንደሚከተሉት እንመለከታለን፡፡

1. <u>ሙሴ</u>

በኦሪት ዘጸአት መጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ አያሌ አርእስተ ታሪኮች ተጠቅሰዋል ከእነዚህም አንዱ ዮሴፍን የሚያውቀው ፈርዖን ነው፡፡ ዮሴፍ ከሞተ በኋላ በግብጽ የነበረው ዘርዓ መንግሥት ሂክሶስ ይባል ነበር፡፡ በምዕራፍ 1፥15-22 ላይ የተመለከተው በእስራኤል ልጆች ላይ ይፈጸም የነበረው ጭቆናና የሕጻናት ዕልቂት በግልሳዊ ተትሞስ ዘመነ መንግሥት /1500 ቅልክ/ ነበር፡፡ ሙሴ የተወለደው በግልሳዊ ተትሞስ ዘመን ሲሆን ያሳደገችውም የግልሳዊ ተትሞስ እኅት ሀትሼፕሱት ነበረች፡፡ ሙሴ የሚለውንም ስም ያወጣችለት ሀትሼፕሱት ናት፡፡ ሙሴ ማለት ዕጓለማይ ማለት ነው፡፡ /ዘጸ. 2፥10/ የጥንቱ የግብጽ ቋንቋ ሙሴ ማለት ልጅ ማለት ነውና ጐጃሜ ትንሽ ልጁ ሞሴ ሞሲት እንዲል በዕብራይስጡ እማይ ዘረከብክዎ ለማለት ሚን ሀማይም ሚሺቲሁ ይላል፡፡ ስለዚህ ሙሴ ማለት ያገኘሁት ወይም ያወጣሁት ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ሙሴ የተትሞት ከፊል ስም ነው፡፡ በግልሳዊ ተትሞስ ዘመነ መንግሥት ስለተወለደ የተትሞስ እኅት ስላሳደገችው ሞስ ወይም ሙሴ ተብሎአል፡፡

እንግዲህ ሙሴ የተወለደው በ1500 ቅልክ ከሆነ ዘጸዓት በዳግማዊ አሜን ሆቴጎ ዘመነ መንግሥት 1450-1420 ቅልክ እንደሆነ ለመገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ከሳልሳዊ ተትሞስ እስከ ዳግማዊ አሜን ሆቴጎ ያሉት ዓመታት ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባወጣበት ጊዜ የነበረውን ዕድሜ ያመለክታሉና፡፡

ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሊቃውንት ሙሴ በዳግማዊ ራምሴ ዘመነ መንግሥት /በ1300 ቅልክ/ እንደተወለደ ይተርካሉ፡፡ ያሳደገችውም የፈርኦን ራምሴ ዳግማዊ ልጅ ነበረች ይላሉ፡፡ በእኛ ትውፊት ተርሙት ወለተ ፈርኦን ትባላለች፡፡ ይህ ዳግማዊ ራምሴ በዘጸአት ምዕራፍ 1 ውስጥ የተጠቀሰው የእስራኤልን ልጆች ይጨቍን የነበረው ፈርዖን ነው በዚህ ታሪክ የእኛም የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ይስማማሉ፡፡ ሙሴ የተወለደ በዳግማዊ ራምሴ ዘመን /በ1300 ቅልክ/ ከሆነ ዘጸዓት በሜርናፕታሁ ዘመን /ከ1235-1220 ቅልክ/ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ከዳግማዊ ራምሴ እስከ ሜርናፕታህ ያሉት ዓመታት ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባወጣ ጊዜ የነበረውን ዕድሜ ያሳያሉና፡፡

<u>ሙሴ</u>

በኦሪት ዘጸዓአት ውስጥ ባይጠቀስም ሙሴ፡- የግብጻውያንን ትምህርት /ጥበብ/ እየተማረ ማደጉ እስጢፋኖስ በአይሁድ ፊት ባደረገው ንግግር ተገልጦአል፡፡ /የሐዋ. 7፥22/ በዚያ ዘመን በአዲሱ የግብጽ ሥርዐተ መንግሥት ለማንኛውም ንጉሣዊ ቤተሰብ ስለ አስተዳዳርና አመራር በመጠኑም በዘመኑ ስለነበረው ፍልስፍና የመማር ግዴታ ነበርና ሙሴም በቤተ ፈርኦን ሰለነበር ሊማር ችሎአል፡፡

2. ክሥተተ ስም ዘእግዚአብሔር

የእግዚአብሔር ስም መገለጫ

ዘሀለሞ ወይሄለ፡- ያለና የሚኖር /ያህዌ/ የሚለው ስም /ዘጸዓት 3፥14/ ለሙሴ ስለመገለጡ ሊቃውንት ሁሉ አስተያየቶች አሉአቸው፡፡

1. ለሙሴ የተገለጠው ምን ነበር?

ለሙሴ የተገለጠው አዲስ የእግዚአብሔር ስም ነበር የሚሉ ሊቃውንት አሉ፡፡ ይህን አስተያየት የሚደግፉ ሊቃውንት የሚከተለውን ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

ሀ. ያህዌ /ዘሀለሞ ወይሄለ፡- ያለና የሚኖር/ የሚለው ስም እስከ ዘመነ ሙሴ በእስራኤላውያን ዘንድ ፈጽሞ አይታወቅም ነበር፡፡

ለ. ይህ ስም /ያህዌ/ ሙሴ በእግዚአብሔር የተጠራ መሪ ሆኖ ተቀባይነት እንዲኖረው ለመጀመሪያ ጊዜ በደብረ ሲና ለሙሴ ተገለጠ፡፡

ሐ. በዘጸአት 3፥1-22 እንደምንመለከተው የታሪክ መልክ ኦርጅናል ወይም መጀመሪያ አይደለም፡፡ ጸሐፊው ያህዌ የሚለው ስም ከመገለጡ በፊት በዚሁ ስም ተጠቅሞአልና /ዘጸአ 3፥2፣4፥7/

መ. በዘፍጥረትና በዘጸአት ውስጥ የሚገኘው በአብዛኛው ታሪክ ዘንድ ያህዌ የሚለው ስም አጠቃቀም /ዘጸአት 3፥2-7/ በጥንት እስራኤላውያን ዘንድ በቀላሉ የተለያዩ ሁለት ዓይነት ታሪክ ተራኪዎችና ጸሐፊዎች እንደነበሩ ያሳያል፡፡

ሀ. 1ኛው የታሪክ ተራኪዎችና ጸሐፊዎች ግሩኘ አብርሃም ያህዌ የሚለውን ስም እንደሚያውቅና ያህዌ የሚለውም ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠውና የታወቀው ለሙሴ እንደሆነ ሲያምን፡-

ለ. 2ኛው የታሪክ ተራኪዎችና ጸሐፊዎች ግሩኘ ደግሞ ያህዌ የሚለው ስም ለአብርሃምና ከአብርሃም በፊት ለነበሩት ሁሉ አበው የተገለጠና የታወቀ እንደነበረ ያምናል /ዘፍ. 2፥4፣ ዘፍ. 4፥1/ ዘፍ. 4፥26፣ 14፥22/ በእኛም ትውፊት ይህ ሁለተኛው አስተያየት ተቀባይነት ያለው ይመስላል፣ ምክንያቱም “ወሥምየ እግዚኣ

/ያህዌ/ እያዳዳዕክዎሙ በማለት ፈንታ "ወሥምየ እግዚኣ አይዳዕክዎሙ" ይላልና /ዘጸዓት 6፥2-3/ አሥመራ ማኅበረ ሐዋርያት ያሳተመውን ብለይ ኪዳን ተመልከት።

2. <u>ለሙሴ የተገለጠው ምን ነበር?</u>

ለሙሴ የተገለጠው የስሙ ትርጓሜ ነበር የሚለ ሊቃውንት አለ። በብለይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ሥፍራ እንደምንረዳው የአንድ ሰው ስም ሁልጊዜ ግፉንና ጠባዩን ይገልጣል። ራሱ እግዚአብሔር "ስሜ እግዚአ /ያህዌ/ አልተገለጠላቸውም" ዘጸአ 6፥2-3/ ማለቱ የእግዚአብሔር ስም ከእነ ሙሴ በፊት የታወቀ ሲሆን ነገር ግን መለኮተዊ ኃይሉን አለማወቃቸውንና አለመረዳታቸውን ለመግለጥ ነበር። ለምሳሌ ደቂቀ ኤሊ እግዚአብሔርን በስም ብቻ ያውቁት ነበር እንጂ ፊታሒነቱን ታዳጊነቱንና ረዳኢነቱን ቃል ኪዳኑንም ለዘለዓለም የሚጠብቅ መሆኑን፣ የነበረ፣ ያለና የሚኖር መሆኑን አያውቁም ነበር። /1ሳሙ. 2፥12/ እንግዲህ ዘጸዓት 6፥2-3 የሚያስረዳን በቀድሞው ዘመን እነአብርሃም የእግዚአብሔርን የስም ትርጉም አለመረዳታቸውን አሁን ግን ለሙሴ የስሙ ትርጓሜ መገለጡን ነው። ከኤርምያስ 16፥21 ጋር አመዛዝን። ይህን ሀሳብ የሚከተሉ ሊቃውንት የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣሉ።

ሀ. እስራኤላውያን በግብጽ ሳሉ ይፈልጉት የነበረው ለእግዚአብሔር አዲስ ሥም ሳይሆን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንዲሆንና ከግብጽም እንዲያወጣቸው አጽናኝ ተስፋ እንዲሰጣቸው /ዘጸ. 3፥16/

ለ. ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል አዲስና ያልታወቀ ሥም አብሥሮ ወይም ይዞ የቀረበ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔርን አምላካቸው አድርገው ለመቀበል ምክንያት ባልኖራቸውም ነበር።

ሐ. አብርሃምና ዘሮቹ ስለ እግዚአብሔር ሁለት ሥሞችን በሚጠቀሙ በሁለት ግሩፖች እንደሚከፈሉ የሚተርኩ የጸሐፊዎችና የታሪክ ተራኪዎች /ነጋሪዎች/ አሳብ ሁሉ ልክ አይደለም።

እንግዲህ ሊቃውንት የሚመላለሱባቸው ስለ ክስተት ስም ዘእግዚአብሔር ያሉት ሁለት አስተያየቶች እነዚህ ናቸው። ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው ሊቃውንት ሳይስማሙ ሲቀሩ የትኛውን ለመከተል የሚችገሩ ደቀ መዛሙርት መሆናቸው ግልጥ ነው። ዐበይት ነጌያት ሲታገሉ የሚጐዳው ሣሩ ነው። እንደሚባለው ሊቃውንት ሲከራከሩ ፈዝዞ የሚቀረው፣ በጥርጥር ላይ የሚወድቀውና ሁሉንስ ብተወው ወደማለት የሚደርሰው የነገሩን እወኑተኛነትና ርዕስ ለማወቅ በመከታተል ላይ ያለ ደቀ መዝሙር ነው። ስለዚህ

የእግዚአብሔር ሥም እግዚእ አስቀድሞ የታወቀ ነበር ግን ለሙሴ የተገለጠው ትርጓሜው ነው በሚለው ትውፊት ላይ ሀሳባችንን እናጸናለን፡፡

ዐሥሩ መቅሠፍቶች

በግብጻውያን ላይ የወረዱት ዐሥሩ መቅሠፍቶች የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫዎች ነበሩ /ዘፀ. 9፥16/ በግብጽ የስህተት ሃይማኖቶችና አማልክት ላይ የእውነተኛውን የእስራኤልን አምላክ ኃይል ይገልጣሉ፡፡ ግብጻውያን ዐባይንና ሌሎችንም ነገሮች እንደ አማልክት አድርገው ያመልኩ ነበር፡፡ ነገር ግን የእግዚአበሔር መቅሠፍት በወንዙና በሌሎችም ነገሮች አማካኝነት በወረደ ጊዜ አንዳንድ ግብጻውያን የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያውቁ አድርጎአቸዋል፡፡ /ዘጸ. 8፥19፣ 9፥20/

ፈርዖን የእስራኤል አምላክ ኮናኔ ሰማይ ወምድር እንደሆነ ለወዳጆቹም ጠላቶቻቸውን የሚቀበል ኃያል አምላክ እንደሆነ እንዲያውቁ /ዐሥሩ መቅሰፍታት በግብጽ ላይ ወርደዋል፡፡ /ዘጸ. 9፥14-16/ ፈርዖን ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም ብሎአልና /ዘጸ. 5፥2/፡፡ የዐሥሩ መቅሠፍታት መውረድ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚገልጡት በፈርዖንና በግብጻውያን ላይ ብቻ ሳይሆን በእስራኤልም ላይ ነው፡፡ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ኃይል ሳይሆን በራሳቸው ኃይል ነጻ ለመውጣት ያስቡ ነበርና /ዘፀ. 2፥11-15/፡፡ ሁሉም መቅሠፍቶች የተደረጉት ግብጻውያን በሚያውቋቸው ነገሮች በጓጉንቸሮች በዝንቦችና በትንኞች፣ በዐባይ ወንዝ አማካኝነት ነው፡፡ ተአምራትነታቸው በመለኮታዊ ኃይል ገጸ ባሕርያቸውን መለወጣቸው ነው፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ተአምራቱን የሚገልጠው በሚታየውና በሚታወቀው ነገር ላይ ነውና፡፡

ዐሥሩ መቅሠፍታት በዝርዝር የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ደም 7፥14-25
2. ጓጉንቸር 8፥1-15
3. ቅማል 8፥16-19
4. ዝምብ 8፥20-23
5. ቸነፈር 9፥1-7
6. ቍስል 9፥8-12
7. በረዶ 9፥13-35
8. አንበጣ 10፥1-20
9. ጨለማ 10፥21-27
10. ሞተ በኩር 11፥1-10

ከእነዚህ ከዐሥሩ መካከል ሰባቱ መቅሠፍታት ደም፣ ጓጉንቸር፣ ዝምብ፣ ቸነፈር፣ በረዶ፣ አንበጣ፣ ሞተ በኩር፣ ከመሆናቸው በፊት እንደሚሆኑ አስቀድሞ ለፈርዖን በዐዋጅ ተነግሮታል /ዘጸ. 7፥15-16፣ 8፥1-6፣ 9፥1-13፣ 10፥1-5፣ 11፥4-6/ የዝንብ መቅሠፍት

ዐዋጅ ለፈርዖን የተነገረው ጥዋት በገበዘ ተከዚ ሳለ ነው። የአምሰቱ መቅሠፍታት፣ የበረድ፣ የጓጉንቸር፣ የቸነፈር፣ የአንበጣና የሞተ በኩር ዐዋጅ ግን ፈርዖን በሰገነት ሳለ ተነግሮታል።

ሌሎቹ 3 መቅሠፍታት ቅማል፣ ቊስልና ጨለማ ግን ለፈርዖን ግልጥ ማስጠንቀቂየ ሳይደርሰው በሀገሩ ላይ አንዲወርዱ ሆነዋል። /8÷16፣ 9÷8፣ 10÷21/።

ይኸውም እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሳያስጠነቅቅ በነቢይ በካህን ሳያስመክር ሳያስተምር፣ የማይቀጣ መሆኑን ሲያሳይ ማስጠንቀቂያውን ተመልክተው ነቢያትንና ካህናትን ሰምተው በማይመለሱት ላይ ደግሞ በፈቀደ ጊዜ ፍርዱን የሚገልጥ መሆኑን ያመለክታል።

የግብጽ ሐረሳውያን /ጠንቋዮች/ የመጀመሪያዎቹን መቀሠፍታት ደምን ጓጉንቸርንና ቅማልን በምትሐት ለማድረግ ከሙሴ ጋር ተወዳድረዋል። ግን ሁለቱን ደምንና ጓጉንቸርን በምትሐት ለማድረግ ሲሞክሩ ሦስተኛውን ቅማልን ለማድረግ ካለመቻላቸውም በላይ "አጽባተ እግዚአብሔር ውእቱ ዝንቱሰ" ይህስ የእግዚአብሔር እጅ አለበት ብለዋል /8÷19/።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጠንቋዮቹ /ሐረሳውያን ሙሴንና አሮንን ለመወዳደር አልቀጠሉም። ሦስቱ መቅሠፍታት ደም፣ ጓጉንቸርና ቅማል በግብጻውያንና በእስራኤላውያን ላይ ያለ ምንም ልዩነት ሲወርድ ከአራተኛው መቅሠፍት ጀምሮ ወደ ላይ ያሉት ግን በግብጻውያን ላይ ብቻ ወርደው። /8÷23/ በተለይም በ6ኛው በ8ኛውና በ10ኛው መቅሠፍታት ላይ ልዩ ጥበቃ ወይም መከላከያ ተደርጐላቸዋል።

በሁለተኛውና በአራተኛው፣ እንዲሁም በ7ኛው በ8ኛውና በ9ኛው መቅሠፍታት ጊዜ፡- ፈርዖን ሙሴና አሮን እግዚአብሔርን እንዲማልዱለት መልእክተኛ ላከባቸው። ፈርዖን ከድንጋጤው የተነሣ ደጋግሞ በአስቸኳይ ለሙሴና ለአሮን ያቀረባቸው አምስት ልመናዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. "ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ ... ሕዝቡንም አለቅቃለሁ" /8÷8/
2. "ሂዱ ... ለአምላካችሁ ሠዉ ... ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ ትሰው ዘንድ እለቅቃችኋለሁ" /8÷25፣28/
3. "በድያለሁ፣ ... ይቅር በሉኝ ... እግዚአብሔርን ለምኑ" /10÷24/ ይሁን እንጂ ፈርዖን ይህን ሁሉ ኑዛዜ ቢያደርግ እውነተኛው አምላክ ላይ እውነተኛ እምነት ሳያደርግ ስለሆነ ምሕረትንና ይቅርታን አላገኘም።

የመጀመሪያዎቹ መቅሠፍታት፡- ደም፣ ጓጉንቸር እና ቅማል የወረዱት በበትረ አሮን መሣሪያነት ነው። 4ኛው፣ 5ኛው፣ 6ኛው፣ 10ኛው መቅሠፍታት ግን በበትረ አሮን ወይም ሌላ መሣሪያ መፈጸማቸው አልተጠቀሰም። ያለምንም መሣሪያ በኃይለ እግዚአብሔር ብቻ ሆነዋል። ሌሎች ሦስት በረድ አንበጣና ጨለማ ደግሞ በእደ ሙሴ ወይም በበትረ ሙሴ መፈጸማቸው ተገልጦአል። ይኸውም፡- እግዚአብሔር በካህን፣ በምእመን አድሮ ተአምራቱን የሚገልጥ መሆኑን ያመለክታል። እንደዚሁም በሙሴና በአሮን በትር ወይም እጅ መሣሪያነት ሳይጠቀም ተአምራቱን ማሳየቱ መለኮታዊ ሥራውን በሚሠራበት ጊዜ የማንና የምንንም እርዳታ /አጋዥነት/ የማይሻ መሆኑን ያሳያል።

5. ፋሲካ

መጨረሻውና 10ኛው መቅሠፍት ሞተ በኩር ከመሆኑ በፊት ልዩ መመሪያ ከእግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን ተሰጥቶ ነበር /ዘጸአ. 12፥1-51 አንብቡ/። 10ኛው መቅሠፍት ሞተ በኩር እግዚአብሔር በሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ወደተዘጋጁት እስራኤላውያን አልቀረበም።

የፋሲካው ዝግጅት አፈጻጸም

1. ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ጠቦት በሚያዝያ በ10ኛው ቀን ይመረጣል። ጠቦቱ በሚያዝያ በ14ኛው ቀን ይሠዋል። ደሙ በእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤት መቃንና መድረክ ላይ ይረጫል። ሥጋው እርሾ ካልገባበት ቂጣና ከሆምጣጤ ጋር ይበላል። ሥጋው በዕለቱ ይፈጸማል እንጂ ለነገ ተርፎ አያድርም። ስለዚህ እያንዳንዱ እስራኤላዊ የበጉን ሥጋ በዕለቱ ለመፈጸም እንዲችል ቤተሰቡን ሁሉ ሰብስቦ በጉን ያርዳል።

ሞተ በኩር የበጉ ደም የተረጨበትን ቤተ እስራኤልን እያለፈ ወደ ግብጻውያን ቤት ገባ በዚህም ምክንያት ፋሲካ የሚለው ስያሜ ሊወጣ ችሎአል። ፋሲካ /ፓሰካ/ ማለት በዕብራይስጥ ማለፍ መሻገር ወይም ማዕዶት ማለት ነውና።

እስራኤላውያን፡- በእያንዳንዱ ግብጻዊ ቤት ሞተ በኩር ከሆነ በኋላ ወዲያውኑ ግብጽን ለቅቀው ወጥተዋል። ጸዓተ ግብጽ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ታሪኮች ሁሉ ለእስራኤላውያን እጅግ ታላቅ ታሪክ ነው። ፈርዖን በእያንዳንዱ ግብጻዊ ቤት እንደሆነ ባስተዋለው ጊዜ የእስራኤልን ጸዓት ፈቀደ። ዛሬ የፋሲካ በዓል በየዓመቱ በእስራኤላውያን ዘንድ መጠበቅ /መከበሩ/ እግዚአብሔር ከግብጽ ባርነት እንዳወጣቸው ለማስታወስ ነው። እስራኤል ከግብጽ የወጡበትን ወር በመጀመሪያ አቢብ በኋላ ኒሳን በመባል ይጠራል። ይኸውም ሚያዝያ ነው አቢብ ተብሎ መጠራቱ ቅድመ ፄዋዌ በባቢሎናዊያን ቋንቋ ነው።

የፋሲካው በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በግል ቤት ነበር። ምክንያቱም ማእከላዊ መሰብሰቢያ ወይም ቤተ አምልኮት እንደዚሁም ሥርዓተ ክህነት ገና አልተመሠረተም ነበርና። ከሦስቱ ዐበይት ዓመታውያን በዓላት መካከል የፋሲካ በዓል ብቻ በግብጽ የተቋቋመ ነው። /ዘጸ. 23፥14-18/።

6. ቃል ኪዳን /መጽሐፈ ኪዳን/

ቀደም ሲል ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው ቃል ኪዳን /ዘፍ. 12፥፣ 15፣ 17/ ምዕራፎች ላይ በዘጸአት 19፥3-8 ላይ የልጅ ልጆቹ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ እንደገና በመነገር ታድሷል። እስራኤላውያን በእግረ ደብረ ሲና ሳሉ ከአሕዛብ ሁሉ የተለዩ፣ የተመረጡና የተቀደሱ ሕዝብ እንደሆኑ፣ ለፈቃደ እግዚአብሔር ፍፁም ታዛዥ እንዲሆኑ እርሱንም ብቻ መከተልና ማፍቀር እንደሚገባቸው ከእግዚአብሔር በሙሴ በኩል ተነገራቸው። ሕዝቡም አንድ አፍ ሆነው እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ አናደርጋለን ብለው መለሱ /ዘጸ. 19፥8/።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር በእነርሱ መካከል ስለሚመሠርተው ቃል ኪዳን የሦስት ቀናት ዝግጅት አደረጉ። እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ዐሥሩን ትእዛዛት /ዲካሎግ/ ሌሎችን ሕጐችና ቅዱሳት በዓላትን ስለማክበር የሚናገሩ መመሪያዎችን ነገራቸው።

በአሮንና በሁለት ልጆቹ በሰባው ሊቃናትም መሪነት ሕዝቡ፡- የሚቃጠልና የደኅንነት መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን አከበሩ። ሙሴ መጽሐፈ ኪዳኑን/ ቃል-ኪዳኑን/ ካነበበላቸው በኋላ ሕዝቡ "እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፣ እንታዘዛለንም አሉ "ለቃል ኪዳኑም ስምምነት እንደ ማኅተም ይሆን ዘንድ መሴ የመሥዋዕቱን ደም በመስዊያውና በሕዝቡ ላይ ረጨው በዚህም እስራኤላውያን ወደ ምድረ ርስት እንደሚገቡ አረጋገጡ /ዘጸ. 24፥1-11/ የዚህም ቃል ኪዳን ዋና ዓላማ የሕዝቡ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ነበር ይሁን እንጂ የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው በኪዳኑ በኩል የነበራቸውን መብት ሊያጡ ችለዋል። /ዘጸ. 32 ነገር ግን የፈረሰው ቃል ኪዳን በሙሴ ጸሎት /አማላጅነት/ በእግዚአብሔር ምሕረት እንደገና ታድሶ በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል የነበረው ግንኙነት ቀጠለ /ዘጸአት 34/። በተጨማሪም በደብረ ሲና ከተሰጠው ቃል ኪዳን ሌላ በሐቅለ ሞዓብ ደግሞ ተመሳሳይ ቃል ኪዳን ተሰጥቶአቸዋል /ዘዳግም 29/

እግዚአብሔር በደብረ ሲና ከእስራኤላውያን ጋር ያደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ በሙሴ የተነበበው የቃል ኪዳን መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል /ዘጸ. 20፥2-17/ ነው። አንዳንድ ሊቃውንት ግን የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ የሚሉት ዘጸአት 20የ22-23፣33 ያለውን

ነው ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ ሊቃውንት ዘንድ ደግሞ 20፥23-33 ያሉት ሦስቱ ምዕራፎች የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ይባላሉ፡፡ ተቀባይነት ያለውም ይህ ነው፡፡

ዐሥሩ ቃላት ወይም ዐሥሩ ትእዛዛት /ዲካሎግ/ የቃል ኪዳኑ መዋቅር ወይም መሠረት ናቸው፡፡ የዐሥሩ ትእዛዛት /ዲካሎግ/ አቆጣጠር በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የተለያየ ነው፡፡ ይህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

1. ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ 20፥2-6
2. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው
3. የሰንበትን ቀን አስብ
4. አባትና እናትህን አክብር
5. አትግደል
6. አታመንዝር
7. አትስረቅ
8. … በሀሰት አትመስክር
9. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ
10. ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ /ዘሌዋ. 19፥18/

2. <u>የዮሴፍ ወልደ ኮርዩን /የአይሁድን ይመለከታል</u>

1. ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ 20፥2-3
2. ሥዕልና ምስልን ለአንተ ከቶ አታድርግ 20፥4-6
3. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው፡፡
4. የሰንበትን ቀን አስብ
5. አባትህንና እናትህን አክብር
6. አትግደል
7. አታመንዝር
8. አትሥረቅ
9. በሀሰት አትመስክር
10. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ

3. የአውግስጢኖስ /የካቶሊክ አቆጣጠር

1. ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ 20፥2-6

2. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው
3. የሰንበትን ቀን አስብ
4. አባትህንና እናትህን አክብር
5. አትግደል
6. አታመንዝር
7. አትስረቅ
8. ... በሐሰት አትመስክር
9. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ
10. የባልንጀራህን ምሽት ሎሌውን ገረዱን፣ በሬውን አህያውን ማናቸውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ አትመኝ፡፡

የአይሁድ አቆጣጠር ከዮሴፍ ወልደ ኮርዮን አቆጣጠር ይለያል፡፡ ይኸውም ዘጸአት 20÷2 ላይ ያለው "አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል አንደኛ ትእዛዝ፣ ከቊጥር 3÷6 ያለውን ደግሞ እንደ ሁለተኛ ትእዛዝ አድርገው በመቊጠራቸው ነው፡፡

የዩሴፍና የአውግስጢኖስ ልዩነትም ከላይ እንዳስቀመጥነው ሁሉ ጆሴፉስ ኢታምልክን ለሁለት በመክፈሉ ሲሆን አውግስጢኖስ ደግሞ ኢትፍቱን ሁለት አድርጐ በመቈጠሩ ነው፡፡ የግሪክና የአብዛኛዎቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የዮሴፍን አቆጣጠር ሲከተሉ ሉተራውንያንና የሮም ቤተ ክርስቲያን የአውግስጢኖስን ይከተላሉ፡፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ አንዳንድ የካቶሊካዊ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር "አፍቅር ቢፀከ ከመ ነፍስከን" ዘሌዋ. 19÷18/ አሥረኛ አድርገው ቈጥረው ጽፈዋል፡፡ /ባለ ሥዕል ትምህርተ ክርስቲያን ገጽ/ ይህን የሮም ካቶሊካውያን ቤተ ክርስቲያን በምስራቁ ክፍል የምሥራቁን በምዕራብም የምዕራቡን ባህልና ሥርዐት ተከትላ ትኖራለች በሚለው መመሪያ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

ዐሥሩ ትእዛዛት በሁለት ክፍል ይከፈላሉ

1ኛው ፍቅረ እግዚአብሔር 2ኛው ፍቅረ ቢጽ ይባላል፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ ትእዛዛቱን ሲሰጠው አንደኛው ክፍል በአንደኛው ጽሌ ሁለተኛው ክፈል በሁለተኛው ጽሌ ጽፎ ሰጥቶታል፡፡ ስለዚህም በአንደኛው ጽሌ የተጻፈው ፍቅረ አግዚአብሔር ሲሆን ይኸውም እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና እንደ አውግስጢኖስ አቆጣጠር 3 ትእዛዛት ናቸው፡፡ እንደ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ግን በአንደኛው ጽሌ የተጻፉት

አራት ትእዛዛት ይሆናሉ፡፡ በሁለተኛው ጽሌ የተጻፈውም ፍቅረ ቢጽ ነው፡፡ በዚህም እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና እንደ አውግስጢኖስ አቆጣጠር ሰባት ትእዛዛት እንደ ዮሴፍም ስድስት ትእዛዛት ተጽፈውበታል፡፡ ፊሎ የተባለው አይሁዳዊ ሊቅ ግን ዐሥሩን ትእዛዛት በሁለት ሲከፍል አምስቱን በአንድ ወገን አምስቱን በሁለተኛው ወገን አድርጐ ከፍሎአቸዋል ይኸውም ስለ ፍቅረ ሰብእ ከሚናገሩት ትእዛዛት አንዱን የመጀመሪያውን ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር ጨምሮ በመቍጠር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ የሚስማሙ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አይገኙም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ትእዛዛት ሲናገር በሁለት ክፍል ማለት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ከፍሎ ተናግሮአል /ማቴ. 22፥34-40/

ከዐሥሩ ትእዛዛት /ዴካሎግ/ ቀጥለው ያሉት የሌሎች ሕጎች ይዘት እንደሚከተለው ነው

1. ጠቅላላ የእስራኤላውያን የአምልኮት መልክ /ዘጸአት 20፥22-26/
2. ሕዝባዊ ሕግ /Civil legissemon 21፥1-23፥13/፡፡
   ሀ. የአገልጋዮች መብት 21፥1-11
   ለ. ቅተለተ ነፍስን የሚመለከቱ ሕጐች /21፥12-17/
   ሐ. የአካል ጉዳትን የሚመለከቱ ሕጎች /21፥18-32/
   መ. ንብረትን የሚመለከቱ ሕጎች /21፥33-36/
   ሠ. ሥርዓትን የሚመለከቱ ሕጎች /22፥1-4/
   ረ. በንብረት ላይ ስለሚደርስ ጉዳት የሚናገሩ ሕጐች /22፥5-6/
   ሰ. የአደራ ንብረትን በመጠበቅ ሁኔታ አለመተማመንን የሚመለከቱ ሕጐች /22፥7-15/
   በ. ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታዎችን የሚመለከቱ ሕጎች /22፥18-31/
   ተ. የመብት ጥበቃ /23፥1-13/
3. ስለ ሦስቱ ዐበይት በዓላት የሚገለጠው ትምህርታዊ ሕግ /23፥14-19/
4. የቃል ኪዳን አምላክ ከሕዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት /23፥20-23/

7. ደብተራ ኦሪት

የዘጸዓት ዋናው ክፍል ማኅበረ አስራኤል ለአምልኮትና ከእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ዓይነት መመሪያ ለማግኘት ስለሚሰበሰቡበት ደብተራ ኦሪት አሠራር ዝግጅትና በውስጡም

ስለሚገኙት ንዋያት በዝርዝር ይናገራል /ዘጸአ. 25፥31/ ደብተራ ኦሪት በዘጸአት 23፥17-11 እንደ ተገለጠው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሕዝቡም ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ማዕከላዊ ቦታ ነበር፡፡ እሥራኤላውያን በምድረ በዳ በኖሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ተገልጦ የሃይማኖትና የአስተዳደር ሕግጋትን ከሰጠው በኋላ ጠቅላላ ሥርዐተ አምልኮት የሚፈጸምበት ይህ ተንቀሳቃሽ የሆነው ድንኳን ነበር፡፡

እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከገቡም በኋላ ድንኳኑ በአገልግሎት ላይ ነበር፡፡ በዘመነ መሳፍንት በሴሎ /ኢያ. 18፥1/ በሳያል ዘመነ መንግሥት በኖብ /1ሳሙ. 21፣ መቃ. 2፥25-26/ ቆይቶም በገባዖን /1ዜና. 16፥39/ ተተክሎ ነበር፡፡ በኋላ ግን ቤተ መቅደስ በተሠራ ጊዜ ሰሎሞን ድንኳኑን በቤተ መቅደስ ውስጥ አኖረው /1ነገሥት 8፥4/፡፡

ደብተራ ኦሪት በተለያዩ ስሞች ይጠራ ነበር

1. ደብተራ /ኦሄል/ ዘጸአት 33፥7/ የአማርኛው ድንኳን ይለዋል፡፡
2. ደብተራ ዘመርጡል /የመገናኛ ድንኳን/ ኦሄል - ሞዒድ/ ዘጸአ 33፥7 “ደብተራ ዘመርጡል” የሚለው የግእዙ ቃል ትክክለኛ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በዕብራይስጡ አሄል ሞዔድ ማለት ደብተራ ዘማኅበር፣ ወይም ዘጉባዔ ማለት ነውና፡፡ ስለዚህ የመገናኛው ድንኳን የሚለው የአማርኛው ትርጉም ከዕብራይስጡ ቃል ኦሄል - ሞዔድ ጋር ተስማሚ ነው፡፡
3. ደብተራ ስምዕ /አሄል - ዒዱት/ ዘኁል. 9፥15/ የምስክር ድንኳን ማለት ነው፡፡ የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ የመገናኛ ድንኳን ለማለትና የምስክር ድንኳን ለማለት የሚጠቀመው፡- ደብተራ ዘመርጡል የሚለውን ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ደብተራ ዘመርጡል የሚስማማው የምስክር ድንኳን ለሚለው ለአማርኛው ቃልና ደብተራ ስምዕ ለሚለው ለግእዙ ቃል ነው፡፡ መርጡል ወይም ማርተር የተባለው ቃል በቀጥታ የተወሰደው ከግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ምስክር ማለት ነውና ዒዱት የሚለው የዕብራይስጥ ቃልም ምስክር ትእዛዝ ማለት ነውና፡፡ ስለዚህ /በዘፀአት 33፥7/ ላይ ወተሰምየት ደብተራ ዘምርጡር “የሚለው ቃል ወተሰምየት ደብተራ ዘጉባኤ ወይም ዘማኅበር ተብሎ ቢታረም የቀና ይሆናል፡፡ አንዳንድ የግእዝ ሊቃውንት ግን በመርጡልና በመርጡር መካከል ልዩነት እንዳለ ይናገራሉ፡፡ መርጡል ጉባኤ ወይም ቤተ ጉባኤ ማለት ነው ይላሉ ይህ ከሆነ ደብተራ ዘመርጡል የሚለው ዘጉባኤ ወይም ዘማኅበር ማለት ይሆናል፡፡
4. ቤተ እግዚአብሔር /በይት ያህዌ/ ዘጸአ. 34፥26፣ ኢያሱ 6፥24/

የደብተራ ኦሪት ክፍሎችና በውስጧና ያሉ ንዋያት

1. ከደብተራ ውጭ ዙሪያውን 50 በመቶ ክንድ የሚሆን ሐሺር /አደባባይዋ/ አለ፡፡ ይህም አደባባይ እስራኤልን ለእግዚአብሔር እንደ ቅዱስ ሕዝብ አድርጐ ከአሕዛብ የሚለይና የሚጠብቅ ነው፡፡ ይህም ሥርዐት ከደብተራ ኦሪት በኋላ በተሠሩት በመቅደሰ ሰሎሞንና በመቅደሰ ሂሮድስ ተጠብቆ ይሠራበት ነበር፡፡
2. ደብተራ ኦሪት ራስዋ ዐሥር በ30 ክንድ የሆነች ሁለት ክፍል ማለት ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ በመጋረጃ የተከፈለች ነበረች፡፡
3. ከደብተራ ኦሪት በአፍአ በአደባባይ መጋረጃ አንጻር /መስቅ አንጠላዕት አፍአ/ ታላቅ ምሥዋዓ ብረት ቆሞአል፡፡ ይህም ለሚቃጠለው መሥዋዕት /ሚዝባሕ - ኦላህ/ ለእህል ቍርባን/ ሚንሐሕ/ ማቅረቢያ መሥዋዕት ማለት ነው፡፡
4. በመሥዋዕተ ብርቱና በመንጠላዕተ ግብዓት መካከል ካህናቱ ወደ ደብተራ ከመግባታቸው በፊት እጃቸውንና እግራቸውን የሚታጠቡባት ትልቅ ማእከከ ብረት /ኪዮር/ አለ፡፡ ይህም መንጽሔ ኃጢአት ለሆነው ለክርስቶስ ደም ምሳሌ ነው፡፡
5. ቅድስት /ቅዳሽ/ ስፋትዋ 20 በ10 ክንድ ነው፡፡ በዚህ ክፍል 3 ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ፡፡
   ሀ. በስተ ሰሜን ወይም በቀኝ በኩል ማዕደ ኅብስተ ገጽ ሽልሐት /ወለሔም ፊኒሞ/ ተዘርግቶአል፡፡ በማዕደ ሕብስተ ገጽም ላይ 12 ትኩስሀባውዝ /ኅብስቶች/ በየሳምንቱ ቅዳሜ ይቀመጣሉ ይህም ለጊዜው ዐሥራ ሁለት ነገደ እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት እንደ ሕያው መሥዋዕት ሆነው የሚቀርቡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ፍጻሜው ግን ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡
   ለ. በስተደቡብ ወይም በግራ በኩል ተቅዋመ ወርቅ /መኖራህ/ ተተክሎአል፡፡ ተቅወመ ወርቅ ባለ ሰባት መሐትወ ዘይት ነው፡፡ ይህም፡- በመንፈስ ቅዱስ ፍፁም ግብረ እግዚአብሔርን የሠራ ክርስቶስ ብርሃነ ዓለም ለመሆኑ አምሳል ነው፡፡ /ዘካ. 4/ ማርዬሎጂ አለበት፡፡
   ሐ. በስተምዕራብ በኩል ምሥዋዓ ዕጣን ዘወርቅ /ሚዝባሕ ሚቅታር ቆሟል፡፡ ምሥዋዑ ቅድስቲቱን ከቅድስተ ቅዱሳኑ በሚለየው በመንጠላዕት ውስጤ ፋሮኬት/ ፊት ለፊት ለሚቀርበው ማዕጠንት ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህም መሥዋዕተ ዕጣን ዘወርቅ ለዕርገተ ጸሎተ ቅዱሳን ምሳሌ ነው /ራእ. 8፥3/፡፡
6. <u>መንጠላዕተ ውሳጤ /ፋሮኬት/ ቅድስተ ቅዱሳን/</u>

ቅድስቱን የሚከፍል ነው። ይህም የክርስቶስ መንጦላዕተ ሥጋ ምሳሌ ነው። ክርስቶስ በተሰቀለበት ዕለት መንጦላዕተ ውስጥ ለሁለት ተከፍሎአል ማለት የአገልግሎት ሥርዓት አልፎአል። ዛሬ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚቻለው በክርስቶስ በሥጋው መጋረጃነት በኩል /ዕብ. 10፥20 ማቴ. 27፥54/

7. <u>ቅድስተ ቅዱሳን /ቀዲሽ ቀዲሽም/</u> የቅድስተ ቅዱሳን ስፋት 10 በ10 ክንድ ነው

<u>በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የሚቀመጡ ንዋያት ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።</u>

ሀ. ታቦተ ኪዳን /ታቦተ ሕግ አሮን ህብረት/ የታቦቱ መጠን 2.5 በ1.5 ክንድ ነበር፥1 በውስጥና በአፍአ በጥሩ ወርቅ ተለብጦአል ኪሩብም እንደሚናተፉ አውራ ዶሮዎች መስለው በመሥሀሉ ላይ ማለት በምክዳኑ ላይ ክንፎቻቸውን ዘርግተው ተስለዋል፣። በመሥሃሎ በዕብራይስጥ ካፎሮት ይባላል። ይህም ሥርዓት ወይም ይቅርታ ማለት ነው። የግእዝ ብሉይ ኪዳን ግን ተድባብ ይለዋል ቅርፁን እንጂ ተግባሩን አያመለክትም ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ በዕለተ በዐለ አስተሥርዮ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ የመሥዋዕት ኃጢአቱን ደም በምሥዋዑ ላይ ይረጫል። ይህም ክርስቶስ ሠራዬ ኃጢአት ለመሆኑ ምሳሌ ነው። /ዕብ. 9፥12/ ታቦቱ፡- እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንደሚገኝ ያመለክታል። ይኸውም ኪሩቤል ዙፋኖቹ ሲሆኑ ታቦት መክየደ እግሩ ነው ማለት ነው ዘጸአ. 25፥22 መዝ. 80፥1/።

ለ. ጐሞረ ወርቅ ወይም መሶበ ወርቅ ዘመና /ኃሜር/ በታቦቱ አንጻር ይቀመጥ ነበር። ይህም እስራኤል በምድረ በዳ ሳሉ ይበሉት ከነበረው መና ለመታሰቢያ ያስቀምጡበት የነበረው ዕቃ ነው ዘፀ. 16፥33/ በትረ አሮን በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ከሚቀመጡት ንዋያት አንዱዋ በትረ አሮን ነበረች። ይህች በትር በግብጽ ብዙ ተአምራት የተሠራበት በኋላም ሳይተክሉአት ለምልማ የተገኘችው ናት /ዘኁ. 17፥10/ በመሠረቱ መሰበወርቅና በትረ አሮን ለብቻቸው በአንጻረ ታቦት ይቀመጡ ነበር። በኋላ ግን በታቦቱ ውስጥ እንዲቀመጡ ሆነዋል። ይህም እስከ ሰሎሞን ጊዜ ነበር። በሰሎሞን ጊዜ በታቦቱ ውስጥ ከጽላተ ሕግ በቀር አንዳችም አልነበረም። /1ነገ. 8፥9/ በትረ አሮንና መሶበ ወርቅ የጠፉት በኤሊ ዘመን እንደነበር የሚተርኩ አሉ /1ሳሙ. 6፥19/ ነገር ግን ከዚያም በፊት መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለማናገኝ ቀደም ብለው ጠፍተው ሊሆን ይችላል። በሐዲስ ኪዳን ምሳሌነታቸው ለእመቤታችን ነው።

አከፋፈሉ

ኦሪት ዘጸዓት በሰባት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል፣

1. **ምዕራፍ 1፥1፣ 4፥31 እስራኤላውያን በግብጽ**
   - ሀ. ከዘፍጥረት የቀጠለ ታሪክ 1፥1-7
   - ለ. የሥቃዩ መጀመሪያ 1፥8-22
   - ሐ. የእግዚአብሔር ፍርዱና የማዳኑ መጀመሪያ ደረጃ የሙሴ ልደትና ጥሪ 2፥1-4-31፡፡
2. **ምዕራፍ 5፥11፣ 15፥21 የፍርድ ቅጣትና ነጻነት**
   - ሀ. በግብጻውያን ላይ የተደረጉ የመጀመሪየ ቅጣቶች እነዚህም ዐሥሩ መቅሠፍታት ናቸው 5፥1-11፥10
   - ለ. በግብጻውያን ላይ የተደረገው የመጨረሻ ቅጣት ፋሲካ፣ የባርነት ፍጻሜ ሰጥመተ ባሕር እስራኤላውያን ግብጽን መልቀቃቸውንና ቀይ ባሕርን መሻገራቸው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ቀን በዐምደ ደመና ሌሊት በዐምደ እሳት መምራት 12፥1-14፥31፡፡
   - ሐ. የነፃነት መዝሙር 15፥1-21
3. **ምዕራፍ 15፥22፣ 19፥2 ከቀይ ባሕር እስከ ሲና**
   - ሀ. የእስራኤላውያን ጉዞ ባማራ በኤሊም፣ በሲና ምድረ በዳና ቢራፊዲም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ከዐለት፣ መና ከደመና ሥጋም መመገቡ 15፥22-17፣17
   - ለ. እስራኤላውያን አማሌቃውያንን ድል ማድረጋቸው 17፥8-16
   - ሐ. የዩቶር ጉብኝትና ሙሴን የሚረዱ መሪዎች እንዲሾሙ ምክር መስጠቱ 18፥1-27፡፡
   - መ. እስራኤላውያን በአገር ደብረ ሲና መስፈራቸው 19፥1-2
4. **ምዕራፍ 19፥3-2፣18 የቃል ኪዳኑ መመሥርት**
   - ሀ. የእግዚአብሔር ዓላማ ለእስራኤል 19፥3-6
   - ለ. ሕዝቡ ሙሴ የነገራቸውን ትእዛዝ እግዚአብሔር መቀበላቸውና የጌታ ድምጽ ለመስማት መዘጋጀታቸው 19፥7-25
   - ሐ. ቃል ኪዳኑን የሚመለከቱ ሕግጋት 20፥1-23፥19
   - መ. የልዩ ልዩ ሥርዓቶች አስተዋጽኦ 23፥20-33

ሠ. የቃል ኪዳኑ መጽደቅ 24፥1-18

5. **<u>ምዕራፍ 25፥1-31፣18 የቃል ኪዳኑ፣ የማደሪያው ድንኳንና የካህናት ተቅዋሞች</u>**

   ሀ. ሕዝበ እስራኤል ለእግዚአብሔር ያቀረቡት ስጦታ፣ ዕብስተ ገጽ ተቅዋመ ወርቅና ደብተራ ስምዕ ከአሠራራቸው አይነት ጋር 25፥1-27፣21

   ለ. ሥርዐተ ክህነትና የቅድስና አገልግሎት 28፥1-29፥46

   ሐ. የድንኳኑ አሠራር ዓይነትና ሠራተኞች 30፥1-31፣11

   መ. ትእምርተ ሰንበትና ጽላት ሕግ 31፥12-18

6. ምዕራፍ 32፥1-34፣35 የቃል ኪዳኑ መፍረስና እንደገና መታደስ

   ሀ. እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ አቁመው ማምለካቸውና ቃል ኪዳኑን ማፍረሳቸው 32፥1-10

   ለ. የሙሴ አማላጅነትና የቃል ኪዳን አፍራሽዎች መቀጣት 32፥11-33፣23

   ሐ. የቃል ኪዳኑ እንደገና መታደስ 34፥1-35

7. ምዕራፍ 35፥1-40፣38 የድንኳኑ አሠራርና አተካከል

   ሀ. ሕዝቡ በፈቃዳቸው ባመጡት ስጦታ የድንኳኑ ሥራ በንድፉ መሠራት መከናወን 35፥1-39፣43

   ለ. የድንኳኑ መተከል፣ የእግዚአብሔር ክብር በድንኳኑ ላይ መገለጥ 40፥1-38

<u>ማጠቃለያ</u>

- ኦሪት ዘፀዓት በዘፍጥረት ለተነገረው ታሪክ ተከታታይ መጽሐፍ ቢሆንም በሕጉ ግን የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው።
- በደብረ ሲና የተነገረው ታሪክ ሁሉ የተፃፈው በሁለቱ በዘፀዓትና በዘሌዋውያን ስለሆነ በአንዱ የተጀመረው በሁለተኛው ተፈፅሞአል።
- በኦሪት ዘፀዓት መጽሐፍ የተተረኩት ታሪኮች ሁሉ ብዙ ጎብረ ምሳሌዎችን የያዙና የክርስቶስን የማዳን ሥራ የሚገልጡ ናቸው።
- የቤተ ክርስቲያን አበው ደብተራ ኦሪትንና በወስጥዋ የሚገኙትን ንዋያት የድንግል ማርያምና የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ አድርገው ተርጉመዋቸዋል።
- ከግብጽና ከኦሪት ዘፀዓት በተገኘ መረጃ መሠረት ፀዓተ እስራኤል ከ1235 ቅልክ 1220 ቅልክ መሆኑ ነው።

- የእግዚአብሔር ስም አስቀድሞ የታወቀ ነበር ለሙሴ የተገለጠው ግን የሥሙ ትርጉም ነበር፡፡
- ፀዓቱ ግብጽ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ታሪኮች ሁሉ ለእስራኤላውያን እጅግ ታላቅ ታሪክ ነው፡፡
- በዘፀዓት የቃል ኪዳን መጽሐፍ የሚባሉት ምዕራፎች 20-23 እና 33 ናቸው፡፡

የኦሪት ዘፀዓት የሙከራ ጥያቄዎች

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ ከኦሪት ዘፀዓት አንብበህ በተረዳኸው መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄወች የጽሑፍ መልስ ስጥ

1. በኦሪት ዘፀዓት መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ምሳሌ የሆኑ ስምንቱን ታሪኮች ግለጥ?
2. በግብፃውያን ላይ የወረዱት ዐሥሩ መቅሰፍቶች ምንን ያመለክታል?
3. ከሦስቱ ዐበየት የእስራኤላውያን በዓላት በግብፅ ምድር የተጀመረው የትኛው ነው?
4. እስራኤል በደብረ ሲና ከተሰጠው ቃል ኪዳን ሌላ ተመሳሳይ ቃል ኪዳን የተቀበሉት የት ነው?
5. እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሕዝቡም ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ማዕከላዊ ቦታ የት ነበር?

ዘሌዋውያን

መግቢያ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ ስለ ሌዋውያን የአገልግሎት ምርጫና ሥርዓት አፈፃፀም ከሚያስገነዝበው የዘሌዋውያን መጽሐፍ ደግሞ የምታገኛቸው ሀቅ ብዙ ጠቃሚ ዕውቀቶች በሚከተለው መልኩ ቀርቦልሃል፡፡

- ስለ መጽሐፉ ስምና ሥያሜ፣
- ስለ መጽሐፉ ፀሐፊ እና ዓላማው፣
- ስለ መጽሐፉ አከፋፈል፣
- ስለ ብሉይ ኪዳን መስዋዕት ዓይነቶች ከሀ እስከ ነ ተዘርዝረዋል፣

  ተመልከታቸው በውስጣቸው በሐዲስ ኪዳን ካለው አገልግሎት በጉልህ በውስጣቸው የያዙት ምሥጢር ሥላለ ተመልከታቸው፣

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

ሦስተኛው የሙሴ መጽሐፍ በአይሁድ አጠራር "ወይቅርዐ" በሚል ስያሜ ይጠራል ይህም በመጽሐፍ መጀመሪያ ቍጥር አንድ ላይ የሚገኝ ቃል ነው፡፡ በታልሙድ ደግሞ "ቶራሕ ኮሂኒም" ኦሪተ ካህናት በመባል ይጠራል፡፡ በሰብዓው ሊቃናት ትርጉም "ሊቪቲኮን" ይባላል፡፡ የሌዋውያን ማለት ነው፡፡ የግእዙም የሰብዓ ሊቃናትን በመከተል ዘሌዋውያን ይላል አንዳንድ ጊዜም ኦሪት ዘሌዋውያን የሚል የግእዝ ብሉይ ኪዳን ይገኛል፡፡ በዚህ የግእዙ ታልሙድን ተከትሎአል፡፡ በምሽና "ኦሪተ መሥዋዕታት" ተብሎ ይጠራል፡፡ ያም ይህ ስያሜው የሚያመለክተው ጠቅላላ የመጽሐፉን ይዘት ስለሆነ ሁሌም ተመሳሳይነት አለው፡፡

ሌዋውያን የሚባሉት ደቂቀ ሌዊ ሁሉ ናቸው፡፡ ከአሮን ቤተሰብ የተወለዱት ደግሞ ካህናት ይባላሉ፡፡ መጽሐፉ "ዘሌዋውያን" ተብሎ ይሰየም እንጂ ስለ ሌዋውያን ብቻ አይናገርም፡፡ ስለ ካህናትና ስለሕዝብም ይናገርል፡፡ /ዘጸ 28፥1-4፣ ዘኁል 18፥1-4/፡፡

ጸሐፊው

የ3ኛው መጽሐፈ ኦሪት ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ በሁሉም ዘንድ የታመነ ነው፡፡

ዓላማው

ዘሌዋውያን፡- ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤላውያን በሃይማኖታዊና በማኅበራዊ ሕይወት የሚመሩባቸውን ሕጐች ይዞአል፡፡

እስራኤላውያን በደብረ ሲና ሳሉ የሃይማኖትና አስተዳደር ሕግ ተሰጣቸው፡፡ የፈረሰው ቃል ኪዳንም ታደሰላቸው፡፡ የማደሪያው ድንኳን ተተከለላቸው፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር በመካከላቸው እንደሚያድር ተስፋ ሰጣቸው፡፡ ሕዝቡ ወደ ተስፋው ሀገር ጉዞአቸውን ከመቀጠላቸው በፊት በማደሪያው ውስጥ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ መመሪየ የሚሆኑአቸውን ሕጐች ማወቅ ለእነርሱ አስፈላጊ ነበር፡፡ ሕጐቹም በዘሌዋውያን የሚገኙት ናቸው፡፡

ዘሌዋውያን ራሱን የቻለ ክፍል ሲሆን በዘጸአት የተተረከው ታሪክና የተሰጠው ትእዛዝ በተግባር ላይ እንደዋሉ ለማስተዋል፣ በዝርዝር የሚያስረዳ ክፍል ነው፡፡ ዘሌዋውያን የዘጸአት ተከታይ ስለሆነ ወፀውየ በማለት በወ ይጀምራል፡፡ ከዚህም ሌላ በዊፄ መጀመሩ የዘጸአትና የዘሌዋውያን ጸሐፊ አንድ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዘሌዋውያን፡- ሕዝበ እስራኤል ርኩስ ከሆነው ነገር ሁሉ እንዲርቁ ያስጠነቅቃል፡- ተቋርጦ የነበረውም የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት እንደገና እንደቀጠለ ያስረዳል፡፡

<u>አከፋፈሉ</u>

ሀ. <u>1፥1-7፣38 ሕግ መሥዋዕት</u>

እግዚአብሔር በኦሪት ዘጸአት 25፥22 ላይ ለሙሴ በሰጠው ተስፋ መሠረት ከማደሪያው ድንኳን ሆኖ ሙሴን አነጋገረው፡፡ ይህም ኃጢአተኞቹን እስራኤላውያን ከርኩስ ነገር እንዲርቁና በንጽሕ እምነት ሆነዋ መሥዋዕት በመያዝ ወደርሱ መቅረብ እንዲችሉ ነበር፡፡ በዚህ በመጀመሪያው ክፍል አምስቱ የመሥዋዕት አይነቶች ተዘርዝረዋል፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የሚቃጠል መሥዋዕት
2. የእህል መሥዋዕት
3. የሰላም /የድኅነት/ መሥዋዕት
4. የኃጢአት መሥዋዕት
5. የበደል መሥዋዕት

እነዚህም በሚከተሉት ምዕራፎች ይገኛሉ፡፡

1. <u>ምዕራፍ 1 የሚቃጠል መሥዋዕት /አላህ/</u>

በዕብራይስጥ አጠቃላይ የመሥዋዕት ሥረይ/ተርም /ቍርባን የሚለው ቃል ነው። ይህ ስም የተለያየ መሥዋዕቶችን ሁሉ ያጠቃልላል። የቃል መሠረት ትርጉም በሥርዓተ አምልኮ ለእግዚአብሔር አንድ ነገርን ማቅረብን ያመለክታል።

2. **ምዕራፍ 2 የእህል ቍርባን /ሚንሐሕ/**

ቁጥር 1-3 ሳይጋገር የሚቀርበውን የእህል ቍርባን ይገልጣል። ከቍጥር 4-13 ተጋግሮ ስለሚቀርበው የእህል ቍርባን ያስረዳል። ቍጥር 14 የቀዳማያቱን ቍርባን ይናገርል።

3. **ምዕራፍ 3 የሰላም /የደኅንነት/ መሥዋዕት**

ዝባሕ /ሰልሚም/ ቍ 1-5 በዚህ መሥዋዕት ሦስት አይነት እንስሳት ይቀርባሉ። እነርሱም ላም፣ ቍ. 1-5 በግ ቍ. 6-11 ፍየል ቍ. 12-17 ናቸው። ምዕራፍ 3 ከምዕራፍ 7፥11-38 ጋር ተነጻጽሮ ሊጠና የሚገባው ክፍል ነው። ተመሳሳይነት አለው በሰላም መሥዋዕት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ስምምነትና ዕረቅ ያመለክታል።

4. **ምዕራፍ 1፥5-13 የኃጢአት መሥዋዕት**

ይህ መሥዋዕት ተለይቶ ላልታወቀ ወይም ባለማወቅ ለተሠራ ኃጢአት ማስተሥርያ ይሆ ዘንድ የሚቀርብ ነው። ከቍጥር 1-12 ካህኑ ስለራሱ ኃጢአት የሚያቀርበውን የመሥዋዕት ዓይነት ያስረዳል። ከቍጥር 13-21 የእስራኤል ማኅበር ባለማወቅ ኃጢአት ሲሠሩ ጉባኤው ሊያቀርበው የሚገባውን መሥዋዕት ይናገርል። ቍጥር 22-26 መኰንኑ፣ ከቍጥር 27-5፣13 ማንኛውም ሰው ስለሚያቀርበው የኃጢአት መሥዋዕት ይገልጣል።

5. **ምዕራፍ 5፥14-6፣7 የበደል መሥዋዕት /አሸም/**

ይህ መሥዋዕት ተለይቶ ሊቃወቅ ኃጢአት ማስተሥሪያ የሚቀርብ ነው።

6. **ምዕራፍ 6፥8-13 ስለሚቃጠል መሥዋዕት አቀራረብ**

ከቍጥር 24-30 ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አቀራረብ ይዘረዝራል።

7. **ምዕራፍ 7 የተለያዩ መሥዋዕቶች**

ቍጥር 1-7 ስለ በደል መሥዋዕት፣ ቍ 8-10 ስለ የሚቃጠል መሥዋዕት ቍ 11-18 ስለ ደኅንነት /የሰላም/ ስለ ምሥጋና፣ ስለ ስእለትና የፈቃድ መሥዋዕቶች አቀራረብ በድጋሚ ይናገራል። ቍ 19-27 ከመሥዋዕቱ የሚበላውንና የማይበላውን ክፍል ይዘረዝራል። ከቍ.28-34 የመወዝወዝና የማንሣት መሥዋዕት ሥነ ሥርዐትን ያብራራል። ከቍ 35-38 ስለ መሥዋዕቶች ሁሉ አይነትና አቀራረብ ማጠቃለያ ነው።

ከአንድ እስከ አምስት ያሉ ምዕራፎች ለእስራኤላውያን ሁለ የተነገሩ ሲሆኑ ስድስትና ሰባት ምዕራፎች ግን ለአሮንና ለልጆቹ ተነግረዋል። በእነዚህም በሁለቱ /6-7/ ምዕራፎች የተነገሩት ሕግጋት በአምስቱ ምዕራፎች ከተነገሩት የመሥዋዕት ሕግጋት ጥቂት ልዩነት ያሳያሉ። ይሁን እንጂ የጸሐፊን ልዩነት አያመለክትም።

ስድስት አይነት የደም መሥዋዕቶች

የደም መሥዋዕቶች /ዝባሐም/ ሥርዐት ሁሉ ስለ ኃጢአተኛው በሚሆን በንጽሐ ሕይወት ለውጥ ኃጢአትን ማስተሥረይ /ኪፑር/ ነው። አቅራቢው በተሠዋዒው ራስ ላይ እጁን ይጭናል። በዚህም ድርጊት ተሠዋዒው ኃጢአተኛውን መቅረብ ይወክላል። አቅራቢው ትክክለኛውን የሞት ቅጣት መቀበሉን ለማመልከት እንስሳውን ይሠዋል። ቀጥሎም ቀሪውን አገልግሎት እንዲፈጽም የታረደውን /የተሠዋውን/ እንስሳ ወደ ካህኑ ያቀርበዋል ካህኑም ደሙን በመሠዊያው ላይ ይረጫል ወይም ይቀባል።

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በተለያዩ የደም የመሥዋዕቶቹ ሁሉም በመጀመሪያዎቹ ሰባት ምዕራፉት ይገኛሉ።

1. <u>የሚቃጠል መሥዋዕት /ቅ-ርባን አላህ/ ዓላማው</u>

ተለይቶ የማይታወቀውን ኃጢአት ለማስተሥረይ በኃጢአተኛው ሰው ለቅዱስ አምላክ የሚቀርብ ነው። ራሱን መባዕ አድርጐ ለአምላክ መስጠትን ያሳያል።

<u>ተሠዋዒ</u>፡- ነውር የሌለበት ተባዕት በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ርግብ፣ ዋኖስ እንደ አቅራቡው ሀብት መጠን ነው።

<u>የአምላክ ድርሻ</u>፡- የቀረበው እንስሳት በሙሉ ይቃጠላል። መዓዛ ሠናይ ይሆናል።

<u>የካህኑ ድርሻ</u>፡- ከዚህ መሥዋዕት ለካህኑ የሚደርስ ክፈል የለም።

<u>የአቅራቢው ድርሻ</u>፡- ለአቅራቢውም ከዚህ መስዋት አይደርሰውም።

2. <u>የኃጢአት መሥዋዕት /ሐታአት/</u>

<u>ዓለማው</u>፡- ተለይቶ የማይታወቀውን ኃጢአት ለማስተሥረይ የሚቀርብ ነው።

<u>ተሠዋዒ</u>፡- ካህኑ ወይም ማኅበሩ በሬ፣ መኰንኑ ተባዕት ፍየል፣ ተራው ሕዝበ አንስት ፍየል ያቀርባል።

<u>የአምላክ ድርሻ</u>፡- ሰቡ፣ ሁለት ኪላሊቶች የጉበት መረብ ነው።

<u>የካህኑ ድርሻ</u>፡- ከስቡ በቀር ሌላው የቀረው ክፍል በመገናኛው ድንኳን ይባላል።

<u>የአቅራቢያው ድርሻ</u>፡- ለአቅራቢው የሚደርስ ነው።

3. የመተላለፍ /የበደል/ መሥዋዕት/ አሻም/

ዓላማው፡- ተለይቶ የታወቀውን ኃጢአት ለማስተሥረይ ነው፡፡

ተሠዋሚ፡- አውራ በግ ብቻ ነው፡፡

የአምላክ ድርሻ፡- ስቡ ሁለት ኪላሊቶች የጉበት መረብ ነው፡፡

የካህኑ ድርሻ፡- ከስቡ በቀር ሌላው የቀረበው ክፍል በመገናኛው ድንኳን ይባላል፡፡

የአቅራቢው ድርሻ፡- ከዚህ ለአቅራቢው የለም፡፡

4. የድኅንነት /የሰላም/ መሥዋዕት/ ዝባሕ ሸላሚም/

/የምሥጋና መሥዋዕት/ ተውዳህ/

ዓላማው፡- ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚቀርብ ነው፡፡ ያልተጠበቀ በረከትን ለመቀበል ወይም ለተደረገ ጸጋ ምሥጋና ለማቅረብ የሚሠዋ ነው፡፡

ተሠዋሚ፡- ነውር የሌለበት ተባዕት፣ ወይም እንሰት ላም በግ፣ ፍየል ነው፡፡

የአምላክ ድርሻ፡- የስቡ ክፍል

የካህኑ ድርሻ፡- 1. ከሚወዘወዘው ቍርባን ፍርምባው በሊቀ ካህናቱ ይሆናል፡፡

2. ከሚነሣው ቍርባን ቀኝ ወርቹ ለተረኛው /ለሰሞነኛው/ ካህን ይሆናል፡፡ ይህም በማንኛውም ንጹሕ ቦታ ይበላል፡፡

የአቅራቢው ድርሻ፡- ቀሪው ክፍል በአደባባይ በዕለቱ ይበላል፡፡

የስእለት መሥዋዕት /ነዳር/

ዓላማው፡- ለበከረከት ወይም በቅድሚያ ለሆነ ጸጋ የሚቀርብ ነው፡፡ የጠየቀው ርዳታ ሲሆንለት ለተደረገለት የሚያቀርበው ነው፡፡

ተሠዋሚ፡- ነውር የሌለበት ተባዕት ወይም እንሰት በሬ በግ፣ ፍየል

የአምላክ ድርሻ፡- የስቡ ክፍል

የካህኑ ድርሻ፡- 1. ከሚወዘወዘው ቁርባን ፍርምባ

ሊቀ ካህናቱ፡- 2. ከሚነሣው ቍርባን ቀኝ ወርቹ ለተረኛው ካህን ይሆናል፡፡ በማናቸውም ንጹሕ ቦታ ይባላል፡፡

የአቅራቢው ድርሻ፡- ቀሪው ክፍል በዕለቱ ወየም በማግሥቱ በአደባባይ ይባላል፡፡

6. የፈቃድ መሥዋዕት /ነደባሕ/

ዓላማው፡- ጠቅላላ አመሥጋኝነትን፣ ፍቅረ አምላክንና ልዩ በረከትን አለመጠየቅን ለመግለጥ ለሚቀርብ ነው፡፡

<u>ተሠዋሚ</u>፡- ተባዕት ወይም አንስት፣ በሬ፣ በግ ፍየል፡፡

<u>የአምላክ ድርሻ</u>፡- የስቡ ክፍል

<u>የካህኑ ድርሻ</u>፡- በአራተኛውና በአምስተኛው የመሥዋዕት አይነቶች እንደተነገረው ነው፡፡

<u>የአቅራቢው ድርሻ</u>፡- ቀሪው ክፍል በዕለቱ ወይም በማግሥት ለአደባባይ

ለ. <u>ለምዕራፍ 8፥1-10፣20 የካህናት መቀደስ</u>

በኦሪት ዘጸአት 29፥1-36 እና 40፥12-15 በተሰጠው መመሪያ መሠረት አሁን ሙሴ አሮንንና የአሮንን ልጆች ቅብዐ ክህነት ይቀባል፡፡

1. 8፥1-5 ስለ ሥርዓተ ክህነት ዝግጅት እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ትእዛዝ፡፡
2. 8፥6-13 ካህናት ከሥርዓተ ክህነት በፊት ሊያደርጉት የሚገባ ሥርዓት፡- ይኸውም ሕጽበት፣ የልብስ ተክህኖ አለባበስና የቅብዓ ክህነት አፈጻጸም ነው፡፡
3. 8፥14-30 የተክህኖው ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ የሚቀርብ መሥዋዕት፡፡ ከቁጥ 31፥36 ሥርዓተ ክህነቱና ሥርዓተ መሥዋዕቱ ከተከናወነ በኋላ ካህናቱ ለሰባቱ ቀናት በመገናኛው ድንኳን እንዲቆዩና የተረፈው መሥዋዕት ምን መሆን እንደሚገባው የተሰጠውን ትእዛዝ ያብራራል፡፡
4. 9፥1-7 አሮን አገልግሎቱን እንዲጀምር ሙሴ መመሪያ ትእዛዝ ይሰጠዋል፡፡
5. 9የ8-21 አሮንና ልጆቹ አገልግሎታቸውን ይጀምራሉ፡፡
6. 9የ22-24 አሮን በካህንነቱ ሕዝቡን ይባርካል፡፡ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፡፡
7. 10፥1-3 ናዳብና አብድዩ ባልተፈቀደው እሳት ማዕጠንት በማቀረባቸው ከተቀጡ በኋላ ከሠፈር ውጭ መጣላቸው፡፡
8. 10፥4-7 ናዳብና አብድዩ ባልተፈቀደው እሳት ማዕጠንት በማቅረባቸው ከተቀጡ በኋላ ውጭ መጣላቸው
9. 10፥8-11 ካህናት ወይም በመጠጣት እንዳይሳከሩ የተሰጠ ትእዛዝ፡፡
10. ቅዱሳን ተራፊ መስዋዕት ስለመከላት የተሠጠ ትእዛዝ

በምዕራፍ 9 ቁጥር 11 እና 15 ላይ ያለው ሀሳብና በምዕራፍ 10፥16-20 ያለው ሃሳብ የተለያየ ወይም የተጋጨ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ልዩነትም ሆነ ግጭት ሊፈጠር አይችልም፡፡

በምዕራፍ 10፥16-20 የምዕራፍ 9፥15 እርማት ወይም ማስተካከያ እንደ ሆነ መናገርም ልክ አይደለም፡- መቃጠል የሚገባው በመጀመሪያው ደሙ ወደ መገናኛው ድንኳን ተወስዶ በዕጣኑ መሠዊያ ላይ የሚረጨው የኃጢአት መሥዋዕት ሥጋ ብቻ ነበር፡፡

የዚህም ሕግ በምዕራፍ 4፥1-21 ተገልጦአል፡፡ በምዕራፍ 9 ከቁጥር 8 ጀምሮ ያለው ግን ልዩ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም ካህናት ወደ አገልግሎት ሲገቡ የሚፈጽሙት ሥርዓት ነው፡፡ የዚህም ዓላማው ተለይቶ የታወቀ የአሮንን ኃጢአት ለማስተሥረይ ሳይሆን አሮንን ከግብረ ክህነት የማከላከል ተለይቶ ያልታወቀ ነገር ቢኖር እርሱን ለማስወገድ ስለሆነ ደሙ ወደ መገናኛው ድንኳን አይወስድም፡፡ ግን በኃጢአት መሠዋዕት መሠዊያ ቀንዶች /በአቅርንተ መሥዋዕ ዘመሥዋዕት ኃጢአት/ ይረባል፡፡

በዚህ ክፍል እንደ ተመለከትነው በመሥዊያው አጠገብ ማገልገል የተፈቀደቸው የአሮን ቤተሰብ ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎች ግን እንዲቀርቡ አልተፈቀደም ነበር፡፡ ደፍሮ የሚቀርብ ቢኖር ይሞታል /ዘኁ 18፥7/ ማንም እስራኤላዊ መሥዋዕት ማቅረብ ይችል ነበር፡፡ ግን በራሱ መብት ሥነ ሥርዓቱን መፈጸም አይችልም ነበር፡፡ ሌ ለዕከላዊ ያስፈልገው ነበር፡፡ ይህም ካህኑ ነው /ዘኁ 16፥5/ ማንም ሰው እንደ ካህን ሆኖ መሥዋዕት እንዲያቀርብ አለመፈቀዱ የእግዚአብሔርን ቅዱስነትና የሰውን ኃጢአተኛነት ያመለክታል፡፡ ካህናት በክህነት የማያገለግሉ ከመሆናቸውም ሌላ መምህራን ስለሆኑ ከአስጸያፊ ነገር ሁሉ ራሳቸውን እንዲለዩ /10፥1/ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ /ምዕ 21፥22/፡፡

ሐ. ምዕራፍ 11፥1-15፥33

1. ምዕራፍ 11 ራጹሐንና ርኩሳን እንስሳት

ይህ ምዕራፍ ስለ ምንጻት ሕጐች ሁሉ እንደ መግቢያ ነው፡፡ ስለ እንስሳት ተፈጥሮ የሰው አእምሮ የሚገመተውን የሚያስገነዝብ ምዕራፍ ነው፡፡ ምዕራፉን እንደሚከተለው ይከፍላል፡፡

ሀ. ከቁጥር 1-8 በየብስ ስላሉ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት

ለ. ከቍጥር 9-12 በባሕርና በወንዞች ውስጥ ስለሚገኙ እንስሳት

ሐ. ከቍጥር 13-28 ስለ አዕዋፍና ስለ ሌሎችም የሚበሩ፣ የሚሸከረከሩ እንስሳት፣

መ. ከቍጥር 29-40 በየብስ የሚኖሩ ተንቀሳቃሽ እንሰሳወችን መብላትም ሆነ በድናቸውን መንካት እንደማይገባ ያስረዳል፡፡

ሠ. ከቍጥር 41-45 በሆዳቸው የሚሳቡና ብዙ አገር ስላላቸው ትሎች ይናገራል፡፡

ረ. ከቍጥር 46-47 ማጠቃለያ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ከቍጥር 2-23 ያሉ ዝርዝሮች በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 14፥6-20 ተደግመዋል፡፡ ከዚህ ሕግ በፊት በሌላቸው ዓለም ስለ ቅዱሳት /ንጽሕ/ ርኩስ ነገር የወጣ

ሕግ እንደነበረ እምብዛም አይነገርም፡፡ ይህ አይነቱ ሥርዐት በዕብራውያንና በግልጻውያን ዘንድ ብዙ ነበር፡፡

2. **ምዕራፍ 12 ሴት ከወለደች በኋላ ስለ መነጻትዋ ወራት ይናገራል**
3. **ምዕራፍ 13 እና 14 ስለ ለምጽና ስለ የተለያዩ የቆዳ በሽታዎች የተሰጡ ሕጐች ይዘዋል፡፡**

እነዚህ ምዕራፎች በ4 ክፍሎች ከፍለን እንመለከታለን፡፡

1ኛ. 13፥1-46 በሰዎች ላይ የሚመጣ ለምጽ

2ኛ. 13፥47-59 በልብሶችና በምንጣፎች ላይ የሚመጣ ለምጽ

3ኛ. 14፥1-32 ከለምጽ የመንጻት ሥርዓት

4ኛ. 14፥33-53 በሴቶች ላይ የሚታይ ለምጽ

ከቍጥር 54-57 ማጠቃለያ ነው፡፡

4. **ምዕራፍ 15 ከአካል ስለሚወጣ ፈሳሽ ነገርና ከእርሱም ስለመንጻት ይናገራል፡፡**

ይህ ምዕራፍ በ4 ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1ኛ. ከቍጥር 1-15 ከወንዲ የሚመጣ ማንኛውም ፈሳሽ

2ኛ. ከቍጥር 16-18 ከአባላዘርእ የሚወጣ ፈሳሽ

3ኛ. ከቍጥር 19-24 ከሴት የሚወጣ ፈሳሽ /ትክቶ/

4ኛ. ከቍጥር 25-34 በበሽታ ምክንያት ከሴት አካል የሚወጣው ፈሳሽ ቁጥር 32 እና 33 መደምደሚያ ነው፡፡

መ. <u>ምዕራፍ 16 1-34 ዕለተ አስተሥርዬ</u>

ይህ ምዕራፍ ከቍጥር 1-28 የዐመቱን የሕዝቡን ኃጢአት የማስተሰርይ ሕጐች አጠቃልሎ የያዘ ነው፡፡ ከቍጥር 29-34 ስለ ዓመታዊው የበዓል አከባበር ዕለት በዓለል አስተሥርየ/ ይገልጣል፡፡

ሠ. <u>ምዕራፍ 17፥1-16 ለመሥዋዕት የተለየ ቦታና ሕርመተ ደም</u>

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሕጐች ሁሉ ከጥቂቶች በቀር ባለፉት ስለ መሥዋዕት በሚናገሩት ምዕራፎች ተነግረዋል፡፡ ቁጥር 1-9 መሥዋዕት ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ መቅረብ እንዳለበት ይናገራል፡፡ ቁጥር 10-14 ደምን መብላት ጎሩም መሆኑን ሲያስረዳ ቁጥር 15 እና 16 ደግሞ የአውሬ ትራፊ ርኩስ መሆኑን ይገልጣል፡፡

ረ. <u>ምዕራፍ 18፥1-20፣27 የሃይማኖት የግብረ ገብ ሕጐችና ቅጣቶች</u>

18 እና 19 ምዕራፎች የሃይማኖትና የግብረ ገብ ሕጐችን ይዘዋል፡፡

1. ምዕራፍ 18፥1-5 መግቢያ ነው “እኔ እግዚአብሔር” የሚለው ቃል እግዚአብሔር የሚፈልገውን ቅድስና ለማጽናት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ ተነግሮአል፡፡ /2፣4፣5፣6፣21፣30/
2. 18፥6-18 ተራክቦተ አዝማድን /አውስቦተ አዝማድን/ የሚከለክሉ ሕጐች፣
3. 18፥19-23 ሩካቤ ዘበሐሳርን የሚከለክል ሕግ፣
4. 18፥24-30 ቀጥተኛ ማስጠንቀቂያ ሕጐች ናቸው የዚህ ምዕራፍ መግቢውና መደምደሚያው አንድ ዓይነት ነው፡፡
5. 19፥1-8 በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ዋና ዓላማ ሕዝቡ ቅዱሳን እንዲሆኑ ነው፡፡ የተፈለገውንም ቅድስና ለማጠናከር “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” የሚለው ቃል 14 ጊዜ ያህል በዚህ ምዕራፍ ተጠቅሶአል፡፡ /3፣4፣10፣12፣14፣16፣18፣25፣28፣30፣31፣32፣34፣37/
6. 19፥9-18 ለባልንጀራ ሊደረግ የሚገባውን ነገር የሚያመለክቱ ሕጐች፣
7. 19፥19-37 ሃይማኖትን ግብረ ገብነትንና ማሕበራዊ ጉዳይን የሚመለከቱ ሕጐች፣

2. <u>ምዕራፍ 20 ቅጣቶች</u>

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ቅጣቶች ሁሉ በምዕራፍ 18-19 የተጠቀሱትን ወንጀሎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በምዕራፍ 18 ተጠቅሰው በምዕራፍ 20 ያልተደገሙ አራት ነገሮች ቢኖርም ቅጣት በሌላው በተመሳሳይ አንጻር ይሰጥ ይሆናል፡፡

ሰ. <u>ምዕራፍ 21፥1-22፣33 የካህናት ቅድስና</u>

ይህ ክፍል በሁለት ክፍሎች ይከፍላል፡፡

1. ምዕራፍ 21፥22፣16 የካህናትን ቅድስና ይናገራል፡፡
   ሀ. ከቁጥር 1-6 ካህናት በድን በመንካት መርከስ እንደማይገባቸው ይገልጣል፡፡
   ለ. ከቁጥር 7-15 የካህናት ጋብቻ
   ሐ. ከቁጥር 16-24 የካህናት የአካል ጉድለት
   መ. ምዕራፍ 22፥1-16 ለተቀደሱ ነገሮች የተሰጠ ክብር
2. 22፥17-33 የተቀደሰ የስዕለትና የፈቃድ መሥዋዕት

ይህ ክፍል በሌሎች ስለ መሥዋዕት በተነገሩት ሕጐች በደፈናው ነውር የሌለበት እንስሳት የሚለውን ምክንያት ያብራራል፡፡

ቀ. ምዕራፍ 23÷1-24፣23 ክብረ በዓላት

1. ምዕራፍ 23 ስለ ቅዱሳት በዓላት ይዘረዝራል፡፡

   ሀ. ቍጥር 1-3 ሰንበት

   ለ. ቍጥር 4 ዓመታዊያን በዓላትን 1 ፋሲካ ቍጥር 5-8/2/

ቀዳምያት እክል ቍጥር 9-14፣/3/ የመከር በዓል /በዓለ ሠዊት/

ቍጥር 15-22

   ሐ. ቍጥር 23-25 በዓለ ሃምሳ

   መ. ቍጥር 26-32 በዓለ አስተሥርዬ

   ሠ. ቍጥር 33-43 በዓለ ዳሕስ /መጸለት/

2. ምዕራፍ 24-23 በበዓላት አንቀጽ መካከል ጣልቃ የገባ ክፍል ነው፡፡ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ስለሚገኙት ንዋያትና በእግዚአብሔር ስም ላይ ጽርፈት በሚያደርጉ ሰዎች ላይ ስለተወሰነው ቅጣት ይናገራል፡፡

   ሀ. ቍጥር 1-4 ስለ ተቅዋመ ማሕቶች

   ለ. ቍጥር 5-9 ስለ ኅብስተ ገጽ

   ሐ. ቍጥር 10-23 ጽርፈተ ስመ እግዚአብሔር በሚያደርጉ ሰዎች ላይ ስለተዋሰነው ቅጣት ይገልጣል፡፡ ይህ ቅጣት የተመሠረተው በወልደ ሰሎሚት ላይ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በሕግነት ጸንቶ ተመሳሳይ ዕረፍት የሚያደረግ ሁሉ በዚሁ ቅጣት የሚቀጣ ሆኖአል፡፡

   በ. ምዕራፍ 25÷1-55 ዓመተ ኅድገትና ዓመተ ኢዮቤልዩ

ከምዕራፍ 23 ቀጥሎ መግባት የሚገባው ምዕራፍ ነው፡፡ የበዓላትን ነገር ይናገራልና ምዕራፉ በ3 ይከፈላል፡፡

1. ቍጥር 1 እና 2 መግቢያ ነው፡፡ በዚህ ላይ የመሴና የደብረ ሲና መጠቀስ ወደ ኋላ ዘጸአት ምዕራፍ 34 ቍጥር 32ን ያታውሳል፡፡
2. ቍጥር 3-7 ስለ ዓመተ ኅድገት ይናገርል፡፡
3. ቍጥር 8-55 ስለ ዓመተ ኢዮቤልዩ ያስረዳል፡፡ ይህ ሦስተኛው ክፍል አንደገና በ3 ይከፈላል፡፡
   1. ቍጥር 8-12 የዓመት ኢዮብልዩ አጠባበቅ
   2. ቍጥር 13-34 ሐብትን በሚመለከት ሁኔታ በዓል ኢዮቤልዩን /ዓመተ ኢዮቤልዩን/ አስመልክቶ የተነገረ/ የወጣ ሕግ፣

3. ቁጥር 34-55 የአንድ እስራኤላዊን የግል ነጻነት በሚመለከት ጉዳይ በኢዮቤልዩ በዓል ምክንያት የተወሰነ ሕግ፡፡

ሦስቱ ዐበይት የዕብራውያን የዓመት በዓላት

ዕብራውያን በልዩ አከባበር የሚያከብሩአቸው ሦስት ዐበይት የዓመት በዓላት አሉአቸው፡፡

እነዚህም፡- 1. በዓለ ፋሲካና በዓለ ናዕት

2. በዓለ ኀምሳ

3. በዓለ ዳሕስ፣ ናቸው

የእነዚህንም አከባበር ሥርዐት እንደሚከተለው እንለመለከታለን፡፡

1.1. በዓለ ፋሲካ /ፕሳሕ፣ ፍሥሕ/ ሚያዝያ/ አቢብ 14 ቀን ማታ ይከበራል /ዘሌ 23፥4-5/

ሀ. **ዓላማው**፡- እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣታቸውን ሞተ በኩር ግብጻውያንን ሲያጠፋ እነርሱን ማለፉን ለማስታወስ ነው፡፡

ለ. **አከባበሩ**፡- የበግ ጠቦት ይታረዳል፡፡ ደሙ በሂሶፕ መቃን መድረኩ ላይ ይረጫል /ይቀባል/ ሥጋው ይጠበሳል፡፡ ወዲያው አቅራቢው ባለቤቱ ከነ ቤተሰቡ ይፈጽመዋል እንጂ አያድርም፡፡ በዓለ ፋሲካ ለጊዜው በግብጽ ተጀምሮአል፡፡ በሲና ምድረ በዳም ሲከበር ቆይቶአል፡፡ ነገር ግን በዘዳግም 16፥5-6 እንደተገለጠው እግዚአብሔር ቅድስት ሀገር እየሩሳሌምን ከመረጠ በኋላ በዓለ ፋሲካ፣ በቅድስት ሀገር በቻ እንዲከበር ሆኖአል፡፡

ሐ. **ልዩ ምሳሌነቱ**፡- የክርስቶስን ስቅለት ያመለክታል /1ቆሮ 5፥7/

1.2. በዓለ ናዕት /ማያት/ ከሚያዝያ 15-22 ይከበራለ /ዘሌ 23፥6/

ሀ. **ዓላማው**፡- ከግብጽ በችኮላ መውጣታቸውን ለማዘከር ነው፡፡ የእርሻው መቅረት ለእግዚአብሔር መቀደስን ያመለክታል፡፡

ለ. **አከባበሩ**፡- ከፋሲካ ማግሥት /በሁለተኛው ቀን/ ሚያዝያ 16 ከግብጹ ቀዳምያት ነጻ ጋር የሚቃጠል መሥዋዕት ይቀርባል /ቁ. 7/ 15ኛውና 22ኛው ቀናት ሁለቱም እንደ ሰንበት ይቆጠራሉ፡፡ እንደገና የሚቃጠል መሠዋዕት ይጨመራል፡፡ 2 ወይፈኖች፣ 1 አውራ በግ 7 ጠቦቶች እንደዚሁም የኃጢአት መሥዋዕት አንደ ፍየል ይሠዋል፡፡ በዚሁ ዕለት ናዕት ብቻ ይበላል፡፡

ሐ. **ልዩ ምሳሌነቱ**፡- የክርስቶስን ትንሣኤ ያሳያል፡፡

2. በዓለ ኀምሳ ሽብያት ስሙናት ማለት ነው /በ3ኛው ወር በሊዋን/ ሰኔ 6 ይከበራል። ወይም በበዓላት ናዕት በ2ኛው ቀን ቍርባነ ቀዳማያተ በተደገ በ46ኛው ቀን፣ ፋሲካ በዋለ በ50ኛው ቀን ይውላል።

ሀ. **ዓላማው**፡- ከስንደው መከር ቀዳማያቱን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነው።

ለ. **አከባበር**፡- በዓሉ እንደ ቅዱስ ሰንበት ይቆጠራል። በዚህ በዓል ላይ ከስንዴ ዱቄት በእርሾ የተጋገሩ ሁለት ዳቦዎች ለመወዝወዝ ቍርባን ይቀርባሉ። የማቃጠል መሥዋዕት ሰባት የበግ ጠቦቶች አንደ ወይፈን፣ ሁለት አውራ በጎች፣ የኃጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት ፍየል እንደዚሁም የሰላም ወይም የድኅነት መስዋዕት ሁለት ተባዕት የበግ ጠቦቶች ይቀርባሉ። ተጨማሪ የሚቃጠልና የኃጢአት መሥዋዕት በዚህ በዓል ዕለት መቅረብ እንደሚገባ በዘኁልቁ 28፥27 ተገልጦአል።

ሐ. **ልዩ ምሳሌነቱ**፡- የርደተ መንፈስ ቅዱስ ነው። ምሳሌነቱ ክርስቶስ በብዙ ሕዝብ፣ በሕጻናትና በአዕሩግ ታጅቦ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱን ያሳያል። ከዳግም ምጽአቱም ጋር የሚያገናዝቡት ሊቃውንት አሉ።

3. በዓለ ዳሕስ፡- /ሱኬት/ ሐዲስ ኪዳን /የግእዙ/ በዓለ ናዕትን በዓለ መደሰት ብሎ ይጠራዋል /ማር 1፥14፣1፣ ሉቃ 22፥1/ በብሉይ ግን በዓለ መጸለት የሚለው በዓል ዳቆስ /ዳስ/ ነው /ዘሌ 23፥34-41/ በሰባተኛው ወር በተሻሪ /ጥቅምት/ ወር ከ15ኛው ቀን ጀምሮ አስከ 22ኛው ቀን ይውላል።

ሀ. **ዓላማው**

በምድረ በዳ የተደረገ መንክራትን ለማዘከርና በመከር ፍፃሜ እግዚአብሔር ለማመስገን፣ ደስታንም ለማድረግ ስንዴ የዛፎች ፍሬ፣ ወይን፣ በዚህ ወር ይደርሳሉ።

ለ. **አከባበሩ**

15ኛው 22ኛው ቀናት ሁለቱም እንደሰንበት ይቈጠራሉ። በሚቃጠል መሥዋዕት ከሰባት እስከ 13 ወይፈኖች በቀን በቀን ሁለት የበግ አውራዎች 14 የበግ ጠቦቶች ይታረዳሉ ለኃጢአቱ መስዋዕት አንድ ፍየል ይቀርባል። /ዘኁ 29/ የበዓሉ አክባሪዎች ለሰባት ቀናት በዳስ ውስጥ ይሰነብታሉ። በአንድ እጃቸው የዘንባባ የአኻያና የለመለመ ዛፍ ቅርንጫፍ በሌላው እጃቸው ፍሬያት ይዘው በዓሉን ያከብራሉ።

ሐ. **ምሳሌነቱ**

ክርስቶስ በብዙ ሕዝብ፣ በሕፃናትና በአዕሩግ ታጅቦ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱን ያሳያል። ከዳግም ምጽአቱም ጋር የሚያገናዝቡት ሊቃውንት አሉ።

የሰባቱ የዕብራውያን በዓላት ወቅት ወርና ቀን

ቁጥር	ስም	ወቅት	ወርና ቀን	ኑኅ በዓል	የሚገኝበት ጥቅስ
1	በዓለ ፋሲካ	መጸው በዕብራውያን	ኒሳን 14 ኒሳን 15	1	ዘፀ. 12፥1-13 ዘሌ. 23፥4-8 ዘኍ. 28፥16-25 ዘዳግ. 1፥6፣1-8
2	በዓለ ኀምሳ /ሸቡዖት/	ጥንተ ሐጋይ በዕብራውያን	ሲዋን 6 /ሰኔ/	1	ዘሌ. 23፥15-21 ዘኍል. 28፥26-31 ዘዳግ. 16፥9-12
3	በዓለ መጥቅዕ	ፀደይ በዕብራውያን	ቲሽር /ታሽሪ/ ጥቅምት	1	ዘሌ. 23፥24 ዘኍል. 29፥1-9
4	ዕለተ አስተሥርዬ ዮም ኪፑር	ጸደይ በዕብራውያን	ቲሽሪ 10	1	ዘሌ. 1፥6 ዘሌ. 23፥26-32 ዘኍ. 29፥7-11
5	በዓለ ዳሕስ /ስክት/ በዓለ መጸለት	ጸደይ በዕብራውያን	ቲሽሪ 15	8	ዘሌ. 23፥33-34 ዘኍ. 29፥12-40 ዘዳግ. 16፥13-15
6	የመታደስ በዓል / ሐኑካህ በዓለ ብርሃናት	ክረምት / በዕብራውያን	ካሴሉ ታኅሣሥ 25	8	1 መቃ. 4፥36-59
7	በዓለ ፍሪም	ጥንተ ሐጋይ /በዕብራውያን/	ዳር 14	1	አስቴር 9፥17-32

በሰንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሰው የወር ስምና የቀን አቈጣጠር እንደ ዕብራውያን የቀን አቆጣጠር ነው፡፡ የወሮች ስም ወደ ኢትዮጵያ የወር ስም ለውጠን እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

1. ኤሉል መሰከረም ነህምያ 6፥15
2. ቲሽሪ /ታሼሪ/ ጥቅምት
3. ማርክሺዋን ሕዳር

4. ካሴሉ ታኅሣሣ ነህመያ 1፥1 ዘካ. 7፥1
5. ጤቤት ጥር
6. ሽባት /ሰባጥ/ የካቲት ዘካ 1፥7
7. አዳር መጋቢት ሕዝ 6፥15 አስቴ 3፥7
8. ኒሳን ሚያዝያ ነህምያ 2፥1 አስቴ 3፥7
9. አ.ያር ግንቦት /ዜፍ/
10. ሲዋን ሰኔ አስቴር 8፥9
11. ተሙዝ ሐምሌ
12. ጥብ ነሐሴ

ማስታወሻ፡- ቅድመ ዔዋዊ እስራኤላውያን በከነዓናውያን የወር ስሞች ይጠቀሙ ነበር፡፡ ከ12 ወራት መካከል አራቱ በብሉይ ኪዳን ተጠቅሰዋል፡፡

1. አቢብ /ሚያዝያ/ ዘጸአት 13፥4፣ 23፥15 34፥18
2. ዚፍ /ግንቦት/ 1 ነገሥት 6፥1-37
3. ኤታኒም /ጥቅምት/ 1 ነገሥት 8፥2
4. ቡል /ሕዳር/ 1 ነገሥት 6፥38

የከነዓናውያን የዓመት መጀመሪያ መስከረም ነበር፡፡ እስራኤላውያንም ወደ ከነዓን ከገቡ በኋላ ይህን ተከትለዋል፡፡

ምዕራፍ 26፥1-46 ተስፋዎችና ከባድ ማስጠንቀቂያዎች

ዘሌዋውያን የቃል ኪዳን መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን በተስፋ ይደመድማል ከቃል ኪዳኑም እንዳይወጡ በጥብቅ ያስጠነቅቃል፡፡

/ዘጸአት 23፥20-33/ ይህ ምዕራፍ በ4 ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. ቍጥር 1 እና 2 መግቢያ ነው፡፡ የሕጉ ሁለ መንፈስ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ተጠቀልለአል፡፡ እነዚህም ሁለት ትእዛዛት ከጣዖት መራቅና እወነተኛውን አመላክ መከተል ናቸው፡፡
2. ቍጥር 3፥13 ሕጉን በመጠበቅ የሚገኝ በረከት
3. ቍጥር 14፥33 ሕጉን ባለመጠበቅ የሚመጣ መርገም ይህ ሦስተኛው ክፍል እንደገና በአራት ንኡሳት ክፍላት ይከፈላል፡፡
   ሀ. ቍጥር 18-20 ከቍጥር 14-17 በተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ሕዝቡ ባይመለሱ በሌላ ከባድ ቅጣት እንደሚቀጡ ያስጠነቅቃል፡፡

ለ. ቍጥር 21 እና 22 የሕዝቡን ተግባራዊ ዓመጽ ይገልጻል፡፡

ሐ. 23-26 ሕዝቡ በዓመጸኝነታቸው ቢፀኑ እግዚአብሔር ደግሞ ከቀደሙት ቅጣቶቱ በበለጠ ቅጣት እንደሚቀጣቸው ያስረዳል፡፡

መ. ቍጥር 27-33 ተከታታይ የሆነውን የሕዝቡን ዓመጽ ይዘረዝራል፡፡

4. ቍጥር 34-35 የእግዚአብሔር የፍርዱ ዓላማ ምን እንደሆነ ይገልጣል፣ ቍጥር 46 የምዕራፍ አጠቃላይ መደምደሚያ ነው፡፡

ነ. ምዕራፍ 27፥1-34 ስእለትና ዐሥራት

ስእለት ከፈቃድና ከግል ፍላጐት የተነሣ የሚፈጸም እንጂ በደብረ ሲና ከተሰጡት ሕጐች ክፍል አይደለም፡፡ ባለመሆኑም፡- የስእለት አሰጣጥ መመሪያ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ከቃል ኪዳኑ ሕግ መደምደሚያ በኋላ ተሰጥአል፡፡ 26፥46 ምዕራፍ በሰባት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. ቍጥር 1-8 የሰው ስእለት
2. ቍጥር 9-13 የእንስሳት ስእለት
3. ቍጥር 14-15 የቤት ስእለት
4. ቍጥር 16-25 የመሬት ስእለት
5. ቍጥር 26-27 የበኩራት ወይም ከእንስሳት በመጀመሪያ የተወለደውን ስእለት አድርጐ አስጠት፣
6. ቍጥር 28-29 በፈቃድና በስእለት ለእግዚአብሔር የተለዩ ነገሮች
7. ቍጥር 30-34 የመሬት ዐሥራት

ማጠቃለያ ዘሌዋውያን በሐዲስ ኪዳን ዘመን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸሙ ድርጊቶችን በግልጥ የሚያመለክት መጽሐፍ ነው፡፡ ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ በሰፊው የተዘረዘሩት ክህነትና መሠዋዕት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሊቀ ካህናትነቱንና መሥዋዕትነቱን በጉልህ ያሳያሉ፡፡

ማጠቃለያ

- የኦሪት ዘሌዋውያን የመጽሐፉ ሥያሜ የሚያሳየው ጠቅላላ የመጽሐፉን ይዘት ነው፡፡
- ኦሪት ዘሌዋውያን ተቋርጦ የነበረው የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት እንደገና እንደቀጠለ ያስረዳል፡፡

- የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ስለ መሥዋዕት ዓይነቶችና የአቀራረብ ሥርዓታቸውን ያስረዳል፡፡
- ማንም ሰው እንደ ካህን ሆኖ መሥዋዕት እንዲያቀርብ አለመፈቀድ የእግዚአብሔርን ቅዱስነትና የሰውን ኃጢአተኛነት ያመለክታል፡፡
- በመሥዋዕቱ መቅረብ በኩል የእግዚአብሔር ዓላማ ሕዝቡ ቅዱሳን እንዲሆኑ ነው፡፡

<u>የኦሪት ዘሌዋውያን የሙከራ ጥያቄዎች</u>

ውድ በርቀት ያለኸው ደቀ መዝሙሬ በኦሪት ዘሌዋውያን ካነበብከው ለሚከተሉት ጥያቄዎች የጽሑፍ መልስ ስጥ፡፡

1. የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ በዕብራይስጥ ምን ይባላል?
2. በኦሪት ዘሌዋውያን የሃይማኖትና የግብረገብ ሕጎችን የያዙት ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው?
3. ዕብራውያን ስንት በዓላትና ወራት አሉአቸው?
4. የስእለት አሰጣጥ መመሪያ /ሕግ/ የተሰጠው መቼ ነው?
5. በዘሌዋውያን መጽሐፍ በሰፊው የተዘረዘሩት ክህነትና መሥዋዕት ምንን ያሳያሉ?

ኦሪት ዘኍልቊ

መግቢያ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ በዚህ በአራተኛው የኦሪት ዘኍልቊ ደግሞ ያሉትን ጠቃሚ ነገሮች እንድትመለከታቸው እንደሚከተለው ቀርቦልሃል፡፡

- ስለ ኦሪት ዘኍልቊ መጽሐፍ ሥም አሠያየም፣
- ስለ መጽሐፉ ዓላማ፣
- ስለ ኦሪት ዘኍልቊ መጽሐፍ አከፋፈል፣

ከተራ ቊጥር 1 እስከ 12 ድረስ በዝርዝር ቀርቧል ብዙ ቁምነገር ታገኝበታለህ ተመልከተው፡፡

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

አራተኛው የሙሴ መጽሐፍ በአይሁድ አጠራር /በማሶሬቲክ ቴክስት/ በሚድባር ይባላል፡፡ ቃሉ የተወሰደው ከመጽፉ መጀመሪያ ምዕራፍ መጀመሪያ ቊጥር ላይ ነው፡፡ ትርጉሙም "በምድረ በዳ" ማለት ነው፡፡ ሰብዓ ሊቃናት ግን ኦሪትን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ በተረጐሙ ጊዜ ለአራተኛው የኦሪት /የሕግ/ መጽሐፍ "አሬስሞስ" የሚል ርእስ ሰጥተውታል፡፡ ይህም ቊጥር ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ብሉይ ኪዳንን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች የተረጐሙ ሊቃውንት ሁሉ፡- ሰብዓ ሊቃናት የሰጡትን ርእስ ተከትለዋል፡፡ ለምሳሌ የቩልጌቱ ትርጉም "ኑሜሪ" ይላል፡፡ በዚህ መሠረት የእንግሊዘኛው ትርጉም ነምበርስ ይላል፡፡ ቊጥረኛ ማለት ነው፡፡ የግእዙ ብሉይ ኪዳናችንም የሰብዓ ሊቃናትን ትርጉም በመከተል "ዘኍልቊ" ይላል የቊጥር ማለት ነው፡፡

መጽሐፉ ዘኍልቊ የተባለበት ምክንያት እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ ሳሉ ሁለት ጊዜ መቈጠራቸውን ስለሚተርክ ነው፡፡ ሁለት ጊዜ የተፈጸመው የሕዝብ ቆጠራ አንደኛ በሲና ሲሆን ሁለተኛው በሐቅለ ሞዓብ ነበር፡፡

ዓላማው

ኦሪት ዘኍልቊ፡- እስራኤላውያን ከሲና ተነሥተው እስከ ከነዓን ድንበር ያደረጉትን ጉዞ ይገልጣል፡፡ በምድረ በዳ ስለ ገጠማቸው ችግር ይዘረዝራል፡፡ በተጨማሪም

የሸማግሌዎችን ወደ ተስፋ ሀገር አለመግባትና ለ38 ዓመታት በምድረ በዳ እንዲንከራተቱ የተፈረደባቸውን ፍርድ ይናገራል። እንደዚሁም የተለያዩ ሕጐች ይገኙበታል።

አከፋፈሉ

ኦሪት ዘኁልቁ በ3 ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ. ሲናን ለመልቀቅ የተደረጉ ዝግጅቶች 1፥1-10፥10

ለ. ከሲና ወደ ሐቅለ ሞዓብ የተደረገ ግዞ 10፥11-21፥35

ሐ. በሐቅለ ሞዓብ የተፈጸሙ ድርጊቶች 22፥1-36፥13። እነዚህም 3 ክፍሎች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሀ. <u>1፥1-10፥10 ሲናን ለመልቀቅ የተደረጉ ዝርጅቶች</u>

ዝግጅቱ በዚሁ መጽሐፍ እንደተገለጠው ከጸአተ ግብጽ በኋላ በሁለተኛው ዓመት፣ በሁለተኛው ወር ከአንደኛው ቀን ጀምሮ እስከ 20ኛው ቀን ድረስ ሲሆን ለ19 ቀናት ወስዶአል። /ዘኁ 10፥11/ ይህ ክፍል በ4 ንኡስ ክፍል ይከፈላል።

1. <u>ከ1 እስከ 4 ያሉ ምዕራፎች የሕዝብ ቈጠራና አመዳደብ</u>

በምዕራፍ 1፥1-54 የተመዘገበው የሕዝብ ቈጠራ ከመገናኛው ድንኳን መተከል በኋላ አንድ ወር ፈጅቶአል። /ዘጸ. 40፥17/ ቈጠራው ከ20 ዓመት ጀምሮ ወደ ላይ ያሉ ለሰልፍ የሚወጡ ወንዶችን ብቻ ይመለከታል። 1፥2-3 የተቈጠሩትም ድምር 603550 ነበር /1፥46/ በምዕራፍ 2 ያለው አቈጣጠር ደግመ በመገናኛው ድንኳን ዙሪያ በየሥፍራቸውና በየዓላማቸው የሚሆነውን የ12 ነገድ ሥነ ሥርዓትን ይገልጣል። ከዚህም ሌላ የእያንዳንዱን ነገድ ከዘረዘረ በኋላ ይደምርና በመጨረሻ አጠቃላይ ድምሩን ይሰጣል /2፥23/።

በእነዚህ ምዕራፎች ላይ ሦስት አከራካሪ ነገሮች ከብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ተሰንዝረዋል።

ሀ. ለሰልፍ /ለጦርነት/ የሚወጡት ሰዎች ብቻ 600 000 ሲሆኑ የጠቅላላው ሕዝብ ድምር ሁለት ሚልዬን ሊሆን ይችላል። እንደዚህም ከሆነ 70 ቤተሰቦች በ400 ዓመት ውስጥ በባርነትና በጭቆና ሆነው ይህን ያህል ሊበዙ አይችሉም የሚሉ አንዳንድ ሊቃውንት አሉ። ነገር ግን ይህ የእብራውያን አበዛዝ ልዩ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ዘጸአ 1፥7/።

ለ. ሲና ይህን ያህል ትልቅ ብዛት ላለው ሕዝብ ለሰፈርና ለመሰማሪየ በቂ ቦታ የለውም። ስለዚህ የሕዝቡ ቍጥር እንደተባለው ላይሆን ይችላል የሚል ግምት የሰጡ ሊቃውንት

አልታጡም፡፡ ነገር ግን ሕዝበ እስራኤል በምድረ በዳ የኖሩት በተፈጥሮ ኃይል ሳይሆን በተአምራዊ ኃይል ነበር፡፡ መና ከደመና እየወረደላቸው ውኃ ከዓለት እየፈለቀላቸው ኖረዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ተአምር የቦታው ጥበት ብዛታቸውን አይቀንሰውም፡፡

ሐ. የሠልፍ ሥነ- ስርዓት በምዕራፍ 2 እና በምዕራፍ 10÷14-20 እንደተዘረዘረው ሊሆን የማይችል መሆኑን የተናገሩ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት አሉ፡፡ ነገር ግን የሕዝቡ ቍጥር ይህን ያህል ካልሆነ አንድ ጸሐፊ ያልሆነውን ነገር በዚህ ዓይነት አከፋፈልና ቅንብር ሊመድብ አይችልም፡፡

በምዕራፍ 3 የሌዋውያን ተግባር ተገልጠአል፡፡ ነገደ ሌዊ በ12 ነገደ እስራኤል የበኩር ልጆች ፈንታ የተመረጠ ነበር፡፡ ምርጫውም በክህነት አገልግሎት ጊዜ ካህናትን ለመርዳት ነበር፡፡

ምራፍ 4 የሦስቱ ደቂቀ ሌዊ ቍጥርና የሥራ መደብ ይናገራል፡፡ ይህም በአራት ይከፈላል፡፡

1. ቍጥር 1-20 ደቂቀ ቀዓትና ሥራቸው
2. ቍጥር 21-28 ደቂቀ ጌድሰን /ጌርሰን/ እና ሥራቸው
3. ቍጥር 29-33 ደቂቀ ሜራሪና ሥራቸው

ቍጥር 34-49 የሌዋውያንን ሥራ በአስተዋጽኦ ከማሳየት ጋር ድምራቸውን ይናገራል፡፡

2750 ቀዓታውያን፣ 2630 ጌድሰናውያን፣ 3200 ሜራሪያውያን በድምር 8580 ሲሆኑ ከጠቅላላው ከ22000 ሌዋውያን ለአገለግሎት የሠለጠኑ ናቸው /3÷39/፡፡

2. <u>ምዕራፍ 5 እና ምዕራፍ 6 ሥርዓተ ንጽሕናና ቃለ ቡራኬ</u>

ሀ. ምዕራፍ 5 ቍጥር 1-10 ለምጽና ፈሳሽ ነገርን የሚመለከቱ ሕጐች

ለ. ቍጥር 11-31 በዝሙት ስለሚያዙ ወይም ባልየው በቅንዓት ስለሚጠራጠራት ሴት የተደነገጉ ሕጐች

6 ምዕራፍ ቍጥር 1-21 ሕገ ናዝራውያን፣ ቍጥር 22-27 አሮንና ሕዝቡን የሚባርክበት ቃለ ቡራኬ፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ቃለ ቡራኬ ትምህርት ሥላሴን የያዘ ነው፡፡ ከ 2ቆሮ 3÷14 ጋር አመዛዝን፡፡

3. <u>ምዕራፍ 7÷1፣ 9÷14 ብስና የተደረጉ የመጨረሻ ታሪኮች</u>

ሀ. ምዕራፍ 7÷1-7-89 የ12 ነገዶች አለቆች የማደሪያው ድንኳን ፈጽሞ ከተተከለ በኋላ ለአገልግሎት ያቀረቡትን መባዕ ይዘረዝራል፡፡ አቅራረባቸውም በተራ ስለ ነበር 12

አለቆች በ12 ቀናት መባቸውን አስገብተዋል። ቊጥር 12፣ 18፣ 24፣ 30፣ 36፣ 42፣ 48፣ 54፣ 60፣ 66፣ 72፣ 78/

ለ. ምዕራፍ 8፥1-26 የሌዋውያን ተቀድሶ /መቅደስ/

ከቊጥር 1-4 ስለ ተቀዋመ ማሕቶት ሥርዐት ይናገራል። ከቊጥር 5-22 የሌዋውያንን ለአገልግሎት መለየት፣ በእስራኤል ልጆች በኩራት ሁለት ፋንታ ለእግዚአብሔር የተለዩ አገልጋዮች መሆናቸው ይገልጣል። ከቊጥር 23-26 የሌዋውያን የአገልግሎት ጊዜ መነሻና መድረሻ ተመዝግቦአል።

ሐ. ምዕራፍ 9፥1-14 በዓለ ፋሲካ በሲና

በዓለ ፋሲካ ለመጀመሪያ ጊዜ በግብጽ ከተከበረ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በደብረ ሲና ተከብሯል።

4. <u>ምዕራፍ 9፥15፣10፥10 በመገናኛው ድንኳን ላይ የወረደው ደመናና ለሰልፍ ዝግጅት የተደረጉ መለከቶች</u>

ይህ ደመና የእስራኤል የመንገድ መሪ ነበር፣ ደመናው ካልተነሣ አይጓዙም ነበር። በዚህም ለመጓዝም ሆነ ለመቀመጥ የእግዚአብሔረን ትእዛዝ ያስተውሉ ነበር። /9፥19-23/

መለከቶቹ ሁለት ሲሆኑ የሁለቱ ድምጽ በተሰማ ጊዜ ማኅበሩ ሁሉ ወደ ደብተራ ስምዕ፣ አንዲ ብቻ ሲነፉ አለቆቹ ወደ ሙሴ ይሰበሰባሉ። ከዚህም ሌላ በመለከቶቹ ድምጽ ስልት የተለያየ ሥርዐት ነበር። 10፥1-10

ለ. ምዕራፍ 10፥11-21፥35 ከግዳመ ሲና ወደ ሞዓብ የተደረገ ጉዞ

1. 10፥11-14፣45 ከግዳመ ሲና እስከ ቃዳሴ በረሐ የተደረገ ጉዞ

ሀ. የጉዞው ሰልፍ በይሁዳ ልጆች መሪነት ይጀመራል።

ሙሴ በጉዞው መነሻና መድረሻ ላይ ይጸልያል።

የጉዞው ምዕራፍ የሚወሰነው ወደ በመናው መነሳትና መቆም ነበር /10፥11-36/

ለ. ምዕራፍ 11፥1-35። በተቤራ /መካነ ውእየት/ በመቃብረ ፍትወት/ ቂብሮት ሐታባሕ/ የተፈጸመው የሕዝብ ማጉረምረም፣ መጐምጀት የድርጭት መውረድና የሰብዓው ሊቃናት ትንቢት መናገር።

ሐ. ምዕራፍ 9፥1-14 ማርያምና አሮን በሙሴ ላይ በታቃውሞ በመነሣታቸው ምክንያት የተሰጠ ፍርድ፣ የማርያም በለምጽ መቀጣትና እንደ ገና በሙሴ ጸሎት መዳንዋ።

መ. ምዕራፍ 13፥1-25 እስራኤላውያን ከግዳመ ሲና ተነሥተው በተቤራና በመቃብረ ፍትወት በኩል ተጉዘው ወደ አሳሮት ደረሱ። ከአሳሮት ተነሥተው በግዳመ ፋራን

ዘቃዳስ ሰፈሩ፡፡ በገዳመ ፋራን ሳለ ሙሴ 12 ሰብአ ዓይን ወደ ከንዓን ላከ፡፡ 13፥26-33 ሰብአ ዓይኑ የሀገሪቱን ዜና ለሙሴ ያቀርባሉ በካሌብ አፈ ጉባኤነት ኢያሱና ካሌብ ካቀረቡት ዜና በቀር ዐሥሩ ሰብአይን ያቀረቡት ዜና ሕዝቡን የሚያዳክም ነበር፡፡

ሠ. ምዕራፍ 14፥1-10 እነዚህ ቍጥሮች ከምዕራፍ 13፥26-33 የቀጠለውን ታሪክ ይዘዋል፡፡ ሕዝቡ ከዐሥሩ ሰብአ ዐይን አስደንጋጭ ዜና በመስማት ወደ ግብጽ ለመመለስ ተስማሙ፡፡ ካሌብና ኢያሱ ግን አስደንጋጩን ዜሃ ተቃወሙ፡፡ በምዕራፍ 13 ቁጥር 30 ካሌበ በቻ የዐሥሩን ሰብአ ዐይን ዜና ሲቃወም ሰምተን ነበር፡፡ በምዕራፍ 14፥6 ላይ ደግሞ ኢያሱ ሲተባበር ይታያል፡፡ በዚህም ምክነያት እነዚህ ሁለቱ ጀግኖች ወደ ከነዓን ሊገቡ ችለዋል፡፡

ረ. 14፥11-25 በዚህ ክፍል በዓመፀኛው ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር ሲቀጣ፣ ሙሴ ስለሕዝቡ ሲማልድ እንደመለከተለን፡፡ ቍጥር 24 ላይ ካሌብ ከኢያሱ ተለይቶ መጠቀሱ፣ ለተቃውሞው መሪ ከመሆኑም በላይ የመሪነት ሥልጣን ከተሰጠው ከነገደ የሁዳ ስለሆነ ነው፡፡

ሰ. 14፥26-38 እግዚአብሔር ከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያለ ሁሉ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ወደ ከነዓን እንዳማይገባ ወሰነ፡፡ አንድ ቀን አንድ ዓመት፣ አርባው ቀናት አርባ ዓመታት እንዲሆንባቸው ፈርዶ /ቍ. 34/

ቀ. 14፥39-45 ሙሴ የእግዚአብሔርን ውሳኔና ፍርድ ለሕዝቡ አስታወቀ፡፡ ሕዝቡ ከፍርድ በኋላ ተጸጸቱ፣ ግን አልጠቀማቸውም፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለተነሡ በሂርማ ድል ሆኑ፡፡

2. ምዕራፍ 15፥1-19፥22 በሠላሳ ሰባቱ የተአምራት ዓመታት ውስጥ የተፈጸሙ ድርጊቶች

ሀ. ምዕራፍ 15 የተለያዩ የመሥዋዕት ሕጐችን፣ ሰንበትን ሲሸር የተገኘ የአንድ ሰው የፍርድ ቅጣት /ቍ. 32-36/ እንደዚሁም ትእዛዘ እግዚአብሔርን ለማስታወስ ሕዝበ እስራኤል በልብሳቸው ጫፍ ዘርፍ /ዘፈር/ እንዲያደርጉ የተነገረውን ትእዛዝ ይዞአል፡፡ /ቍ. 37-41/

ለ. ምዕራፍ 16፥1-50 የቆሬ፣ የዳታን፣ የአቤሮንና የአንድ አንድ ዐመጹን የነሣሱት ከሌዊና ከሮቤል ነገዶች የተውጣጡ መሪዎች ናቸው፡፡ በቍጥር 1 ላይ እንደምንመለከተው የዐመጹ ቀስቃሾች በመጀመሪየ በሙሴ ላይ ዐምጸዋል፡፡ እንደገናም 250 ሰዎችን አሳድመው በሙሴና በአሮን ላይ ተነሥተዋል፡፡ /ቍ. 2-3/ ቍጥር 4-11 ሙሴ ከነገሩ አነሣሽ ከቆሬ ጋር ይነጋገራል፡፡

ቍጥር 12-15 ሙሴ ከዳታንና ከአቤሮን ጋር ለመነጋገር ፈልጐ ሳለ እምቢ አሉት፡፡ ቍጥር 16-19 ዐመፀኞች በቍጥራቸው ልክ ጥናዎቹን ይዘው ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ፡፡ ቍጥር 20-30 ሕዝቡ ከዐመፀኞች ሰፈር አካባቢ እንዲርቁ ማስጠንቀቂየ ተሰጣቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሴና አሮን ወደ እግዚአብሔር ማለዱ ግን /ሕዝቡ/ እነቆሬ ምሕረት የማይገባቸው ሆነው ተገኙ፡፡

ቍጥር 31-40 ዐመጸኞቹ ተቀሠፉ፡፡ ነገር ግን የደቂቀ ቆሬን ከአባታቸው ጋር መሬት አልዋጣቸውም፡፡

ዘኁል. 26፥9-11 ቍጥር 41-50 በተቀሠፉ ሰዎች ምክንያት ማጎበሩ ሁሉ በሙሴና በአሮን ላይ ተነሡ፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ቀሠፈ፡፡ ሆኖም መቅሠፍቱ ወደ ሁሉም ሳይተላለፍ አሮን ማለዳላቸው፡፡

ሐ. ምዕራፍ 17፥1-13 ክህነት ከቤተ አሮን እንዳይወጣ ሕዝቡም ለሁለተኛ ጊዜ በክህነት ምክንያት እንዳያጉረመርሙ እግዚአብሔር በአሮን በትር ላይ ምልክት አደረገ፡፡ ይህም ነገር ማርየም /ማሬዮሎጂ/ አለበት፡፡

መ. ምዕራፍ 18፥1-32 የካህናትና የሌዋውያን አገልግሎት፡፡ ቍጥር 1-7 የካህናትንና የሌዋውያንን የሥራ ድርሻ ይገልጣል፡፡ ቍጥር 8-19 ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ሌዋውያን ከሕዝቡ ጋር ርስት እንደሌላቸው ያስረዳል፡፡

ቍጥር 29-32 ሌዋውያን የዐሥራት ዐሥራት ማቅረብ እንዳለባቸው ያስጠነቅቃል

ሠ. ምዕራፍ 19፥1-22 ከሐመደ ዕጉልት ስለመንጻት ይናገራል፡፡

3. ምዕራፍ 20 እና 21 ከቃዴስ ወደ ሞዓብ የተደረገ ጉዞ

የማርያም ሞት 20፥1 በውኃ እጦት ምክንያት የሕዝቡ ማጉረምረም /20፥2-6/ ሙሴ ዓለቱን በመምታት ውኃ ማፍለቅ /20፥7-13/ በዚህ ጊዜ ሙሴና አሮን ወደ ተስፋ ሀገር እንደማይገቡ ተፈርዶባቸው፡፡ ቍጥር14-21 ሙሴ ወደ ኤዶምያስ ንጉሥ መልእክተኞች እንደላከና ንጉሥም ለእስራኤላውያን በሀገሩ ውስጥ ማለፊያ መንገድ እነደከለከለ እናገኛለን፡፡ ቍጥር 22-29 እስራኤላውያን ከቃዴስ ወደ ደብረ ሖር ተጓዙ፡፡ በደብረ ሖር ካህኑ አሮን ሞተና ልጁ አልአዛር በአባቱ ቦታ ተተካ፡፡ ምዕራፍ 21፥1-3 የአራጽ ዛቻና የእስራኤል ድል አድራጊነት ተገልጸአል፡፡ ቍጥር 4-9 ሕዝቡ ከደብረ ሖር ይጓዛሉ፡፡ ሕዝቡ በምድረ በዳ እንሞታለን ብለው በመገመት አጉረመረሙ፡፡ በዚህም ምክንያት መርዛም እባብ ተላከባቸው ነገር ግን ሙሴ ማለዳላቸው፡፡

ይህም ቍጥር 10-35 የጉዞውን ተከታታይ ታሪክ ከሴዎንና ከዐግ ጋር የተደረገውን ጦርነት ይናገራል። በቍጥር 14 ላይ የተጠቀሰው መዝሙር ከሌላ መጽሐፍ እንደተጠቀሰ /ተወሰደ/ የአማርኛውና የእግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በዕብራይስጡም እንደዚሁ ነው። የተጠቀሰበትም መጽሐፍ "መጽሐፈ ፀብዑ ለእግዚአብሔር" "ሰፈር ሚልሐሞዝ ያህዌህ" ነው። ነገር ግን የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ "ወበበይነ ዝንቱ ይብል በውስተ መጽሐፈ ፀብዑ ለእግዚአብሔር አውዐያ ለዘዓለም፣ ወአቀመ ወኀይዝተ አርኖን ዘሀለው ውስተ አርዝ ይሰመይ ደወለ አሮኖን" ይላል ይህም የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ነው። ይሁን እንጂ መሠረቱ የዕብራይስጡ ነው። የሔስና ሱፋህ የታወቁ ሀገሮች አይደሉም።

ሐ. 22÷1-36፣13 በሞዓብ ሜዳ የተፈጸሙ ድርጊቶች

1. 22-24 ያሉ ምዕራፎች በለዓምና ትንቢቱ

የበለዓም ታሪክ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ፡- በ2ጴጥ 2÷15፣ ይሁዳ 2፣ ራእይ 2÷14 ተረጋግጦአል። በምዕራፍ 22 ቍጥር 12 እግዚአብሔር በልዓምን እንዳይሄድ ከልክሎታል፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መርገም አይገዳውምና በ22÷2 ላይ ደግሞ በለዓም ተፈቅዶለታል። ሆኖም ለመሄድ አልታዘዘም ነገር ግን ቢሄድም ለእግዚአብሔር ሀሳብ መታዘዝ ነበረበት በለዓም ለእግዚአብሔር ሀሳብ ባለመታዘዝ ወደ ባላቅ ለመሄድ ጉዞ ሲጀምር የእግዚአብሔር መልአክ በመንገድ ተገልጦ እግዚአብሔር የሚሰጠውን መመሪያ እንዲከተል በተግሣጽ ነግረው /22÷35/

በለዓለም በአራት የተከፈሉ ትንቢቶችን ስለ እስራኤል ሕዝብ ተናገረ። ዘኁል 23÷7-10፣ 18-24፣ 24÷3-9፣ 15-24። ነገር ግን በለዓለም የእስራኤል ሕዝብ የሚጠፉበትን መንገድ ለባላቅ ሳይመክር አልቀረም ዘኁል 31÷16/

2. ምዕራፍ 25÷1-18 እስራኤላውያን ከሞዓባውያን

ጋር ማመንዘራቸውንና ብዔል ፌጎርን መከተላቸው በዚህ ምክንያት 24000 ሰዎች መሞታቸውና የፊንሐስ መንፈሳዊ ቅንዓት።

3. ምዕራፍ 26 ሁለተኛው የእስራኤል ሕዝብ ቈጠራ

በሲና በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ የነበሩት ሽማግሌዎች በሞዓብ በተደረገው ቈጠራ አልነበሩም፣ ምክንያቶች በቍጥር 64-65 ተገልጦአል። በምዕራፍ 2 እና 3 ካለው የሕዝብ ብዛት በምዕራፍ 26 የተቈጠሩት ሕዝብ ያንሳሉ የሲናው ሕዝብ 603550 ሲሆኑ የሞዓብ ደግሞ 601730 ነበሩ።

4. ምዕራፍ 27 ቍጥር 1-11 የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች

ስለ ርስት ያቀረቡት አቤቱታ፡- በስለጽዓድ ሴቶች ልጆች ምክንያት ወንድ ልጅ የሌለው እስራኤላዊ ሁሉ ሴቶች ልጆች ርስቱን መካፈል ወይም መውረስ እንደሚችሉ ይህ ሐግ ተሰጥቶአል፡፡ ቊጥር 12-14 ሙሴ በዓበሪም ተራራ ሆኖ የተስፋውን ሀገር አይቶ እንደሚሞት ተነገረው ቊጥር 15-23 ሙሴ ከራሱ በኋላ ሕዝቡን ስለሚመራው ሰው እግዚአብሔርን በመጠየቁ እያሱን እንዲሾም ታዘዘ፡፡

5. ምዕራፍ 28 እና 29 ልዩ ልዩ መሥዋዕታትና በዓላት

ሀ. ምዕራፍ 28፥1-8 የዘወትር መሥዋዕት ቊጥር 9-10 የሰንበት መሥዋዕት ቊጥር 11-15 የመባቻ መሥዋዕት፣ ቊጥር 16-25 የበዓለ ፋሲካና የበዓለ ናዕት መሥዋዕት፣ ቊጥር 26-31 የበዓለ ሠዊት መሥዋዕት፡፡

ለ. ምዕራፍ 29፥1-6 በዓለ መጥቅዕ፣ ቊጥር 7-11 በዓለ አስተሥርዬ ቊጥር 12-40 በዓለ ዳሐስ /መፀለት/፡፡

6. ምዕራፍ 30 ስእለትን የሚመለከት ሕግ

በዚህ ክፍል የተገለጠው የስእለት ሕግ፣ በአባት ወይም በባል ሥር ያለች ሴትን ይመለከታል፡፡ አባት ወይም ባል የሌላት ግን ሥልጣን የራሷ ነው፡፡

7. ምዕራፍ 31 እስራኤላውያን ከምድያማውያን ጋር በበቀል ያደረጉት ጣርነት

ቊጥር 1-12 የእስራኤል ሰልፈኞች ምድያሚያውያንን ገድለው ከተሞችን አቃጥለው ምርኮውን ይዘው ወደ ሞዓብ ተመለሱ፡፡ ነገር ግን ሴቶችን አልገደልሁም ቊጥር 13-24 ገዳዮችና ምርኮው የሚነዱበት ሥርዐት ቊጥር 25-54 የምርኮው አከፋፈል፡- አከፋፈሉ በሁለት መደብ ነበር፡፡ 1ኛው በጦር ሜዳ የዋሉት፣ ሁለተኛው ያልዘመቱት ማኅበረ እስራኤል ናቸው፡፡ ሁለቱም ለእግዚአብሔር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሲታዘዙ የዘመቱት ከአምስት መቶ አንድ ያልዘመቱት ከሐምሳ አንድ እንዲያወጡ ታዝዘዋል፡፡

8. ምዕራፍ 32፥1-42 የሮቤል፣ የጋድ ልጆችና መንፈቅ ነገደ ምናሴ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በኩል መስፈራቸው

እነዚህ ሁለት ነገድና የአንድ ነገድ እኩሌታ ሌሎችን ማለት ዘጠኙን ነገድ ተኩል ዮርዳኖስን አሻግረው የከነዓንን ሰዎች ድል ካደረጉ በኋላ ተመልሰው እላይ በተጠቀሰው ቦታ ሰፍረዋል ቊጥር 34-42/ ይህም የሆነው በስምምነት ነበር/ ቊ 16-24

9. ምዕራፍ 33፥1-49 የጉዞና የመካነ ምዕራፍ

ዝርዝር፡- እስራኤል ከራምሴ ተነስተው እስከ ሞዓብ ያደረጉት ጉዞና የሰፈሩበት ቦታ በዚህ ክፍል ተገልጦአል፡፡ በዚህ ዘመን ይህ ዓይነት ሊስት /ዝርዝር/ መሠራቱን እጅግ

የሚየሰደንቅ ነበር፡፡ በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መሪነት መጻፉን ያመለክታል፡፡ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትም ይህን የሊሰት አሠራር በመመልከት በሙሴ ዘመን ሳይሆን ከእርሱ በኋላ እንደ ተዘጋጀ ገምተዋል፡፡ ነገር ግን የጉዞው ቅድመ ተከተልና የቦታዎች ስም በኋላ በተነሡ ሊቃውንት ሊስተካከለ ስለማይችለ ዝግጅቱ የሙሴ ከመሆኑ አይወጣም፡፡

10.ምዕራፍ 34፥1-29 እስራኤላውያን በዕጣ እንዲከፋፈሉአት የተሰጣቸው ሀገርና ወሰኑ

በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰውን ርስት የሚከፈለ ዘጠኙ ነገድ ተኩል ብቻ ናቸው፡፡ ሁለቱ ነገድ ተኩል፡፡ ከዮርዳኖስ ማዶ ርስት አግኝተዋልና፡፡ ቍጥር 13-15 ርስቱ የሚከፈለው በካህኑ አለአዛርና በኢያሱ እንደዚሁም ከዐሥሩ ነገድ በተመረጡ ዐሥር አለቆች አከፋፋይነት ነበር፡፡ /ቍጥር 16-29/

11.ምዕራፍ 35፥1-34 የሌዋውያን ከተሞችና የነፍስ ገዳዮች ምስካይ

ሌዋውያን ከዐሥራ አንዱ ነገድ ጋር ርስት አልተካለም፡፡ ስለዚህ ለቤት መሥሪያና ለከብት መሠማሪየ ያህል ዐሥራ አንድ ነገዶቱ እንዲሰጡአቸው ታዘዙ የሌዋውያን ከተሞች በጠቅላላ 48 ሲሆኑ ስድስት የመማጸኛ ከተሞች ናቸው፡፡

12.ምዕራፍ 36፥1-13 ርስት ከነገድ ወደ ነገድ እንዳይተላለፍ የተሰጠ ትእዛዝ

ከዚህ በፊት አንድ ሰው ወንድ ልጅ ባይኖረው ርስቱ ለሴቶች ልጆች እንዲተላለፍ የተሰጠውን ትእዛዝ ተመልክተናል፡፡ /ዘኁ 27፥1-11/ አሁን ደግሞ ሴቶች ልጆች የአባታቸውን ርስት ከወረሱ በኋላ ባል በሚያገቡበት ጊዜ ርስቱ ወደ ባሎች ርስት ስለሚጨመር ወይም ስለሚዛወር ሌላ ችግር ተፈጠረ፡፡ ስለዚህም በዚህ ክፍል የአባታቸውን ርስት የወረሱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ነገድ ብቻ እንዲያገቡ ትእዛዝ ተሰጠ፡፡ ከቍጥር 5-9 በዚህም ትእዛዝ መሠረት ርስት ከአንድ ነገር ወደ ሌላው ነገድ እንዳይተላለፍ ሆነ፡፡ ይህ ችግር የተጀመረው በሰለጰዓድ ሴቶች ምክንያት ሲሆን መፍትሔውም የተገኙለት በእርሱ አቤቱታ ነው፡፡

ማጠቃለያ

- ኦሪት ዘኁልቍ እስራኤል በምድረ በዳ የገጠማቸውን ችግር ይዘረዝራል፡፡
- ከግብፅ ከወጡ እስራኤላውያን በሕይወት ሥጋ ምድረ ርስት የገቡ ሁለቱ ካሌብና ኢያሱ ናቸው፡፡
- ሙሴ ከርሱ በኋላ እስራኤልን /ሕዝቡን/ ስለሚመራው ሰው በመጠየቁ ኢያሱን እንዲሾም በእግዚአብሔር ታዘዘ፡፡

- እስራኤል ምድረ ርስትን ሲከፋፈሉ ርስቱ የሚከፋፈለው በካህኑ አልዓዛር እና በኢያሱ ከዐሥሩ ነገድ በተመረጡ ዐሥር አለቆች አከፋፋይነት ነበር።
- በዕብራውያን ታሪክ የአባታቸውን ርስት የወረሱ ሴቶች ልጆች የሰለጳዓድ ሴቶች ልጆች ናቸው።

የኦሪት ዘኁልቁ የሙከራ ጥያቄዎች

ውድ የሩቅ ደቀ መዝሙሬ ከኦሪት ዘኁልቁ አንብበህ በተገነዘብከው መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በፅሑፍ መልስ ሰጥ?

1. ኦሪት ዘኁልቅ የተባለበት ምክንያት ምንድነው?
2. በዓለ ፋሲካ ለሁለተኛ ጊዜ የተከበረው የት ነው?
3. በኦሪት ዘኁልቁ ሕዝቡ ወደ ግብፅ ለመመለስ ለምን ፈለጉ?
4. እግዚአብሔር በአሮን በትር ላይ ያደረገው ምልክት ምሥጢር ምንድነው?
5. ከሌዋውያን ከተሞች የመማፅኛ ከተሞች የተባሉት ስንት ናቸው?

ኦሪት ዘዳግም

መግቢያ

ውድ በርቀት ያለኸው ደቀ መዝሙሬ ስለ አምስተኛው የኦሪት መጽሐፍ እና በውስጡ ሥለያዛቸው ምሥጢራትና ትርጉም ተዘጋጅቶ ቀርቦልሃል ተመልከተው አቀራረቡም፡-

- ስለ መጽሐፉ ሥምና አሠያየም፣
- ስለ መጽሐፉ ፀሐፊ፣
- ስለ መጽሐፉ ዓላማ፣
- ስለ መጽሐፉ አከፋፈል ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 ድረስ ያለው ዝርዝር፣ከሰፊ ትንታኔ ጋር ስለቀረበልህ በማስተዋል ተመልከተው፡፡

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

አምስተኛውም የሙሴ መጽሐፍ በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ወእሌህ ዲባሪም ወይም በአጭሩ ዲባሪም ይባላል፡፡ ይህም እሌህ ቃላት ወይም በአጭሩ ቃላት ማለት ነው፡፡ ይህ ስያሜ የተወሰደው ከምዕራፍ 1 ቍጥር 1 ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሚሽናህ ቶራህ ወይም በቀላሉ ሚሽናህ ተብሎ ይጠራል ይህም ዘዳግም ሕግ ማለት ነው፡፡ ዘዳግም ማለትም በአማርኛ የተደገመ የተከለሰ ማለት ነው፡፡ ይህ ስያሜ የተወሰደው ከዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 17 ቍጥር 18 ላይ ነው፡፡ ቃሉም “ወሶበ ነበረ ውስተ ምኩናኑ ለይጽሐፍ ሎቱ ዘንተ ዳግመ ኦሪት” ይላል፡፡ እንደገናም “መጽሐፈ ምክር ተብሎ ይጠራል፡፡ ሰብዓው ሊቃናትም በምዕራፍ 17 ቍጥር 18 ላይ የተጠቀሰውን ቃል በመከተል ዲዩትሮኖሚዮን የሚል ርእስ ሰጥተውታል፡፡ ይህም ዳግም ሕግ ማለት ነው፡፡ የእኛም ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ኦሪትን ወደ ግእዝ በተረጐሙ ጊዜ ለዚህ ለአምስተኛው የሙሴ መጽሐፍ ዘዳግም ሕግ የሚለውን ርእስ ተጠቅመዋል፡፡ ይኸውም ከአይሁድና ከሰብዓ ሊቃናት ስያሜ ጋር ይስማማል፡፡ በእንግሊዘኛውም መጽሐፍ ቅዱስ “ዲዩትሮኖሚ የሚለው አጠራር ከግሪኩ የተወረሰ ነው፡፡ አምስተኛው የሙሴ መጽሐፍ ዘዳግም ሕግ መባሉ ዘጸአት ጀምሮ እስከ ዘኁልቍ ያሉት ሦስት መጻሕፈት ተደግመው ተከልሰው ስለተጻፈበትና ከግብጽ ለወጣው ለሁለተኛው ትውልድ ስለተነገረ ነው፡፡

ጸሐፊው

በኦሪት ዘዳግም ውስጥ ሙሴ ለሕዝቡ በአንደኛ መደብ እንደሚናገር ሆኖ ሌላ ሰው በ3ኛው መደብ ታሪኩን ያብራራል። አዘጋጂው በዚያው ዘመን፣ በምዕራብ ዮርዳኖስ ይኖር የነበረው ሰው ይመስላል። ምክንያቱም የሙሴን ቦታ፣ የመጨረሻ ንግግሮችና በዮርዳኖስ ማዶ የሙሴን መሞት ይተርካልና /ይጠቅሳልና/ ዘዳግም 1፥5፣4፥46/።

የኦሪት ዘዳግምን መጨረሻ ክፍል የጻፈ ሰውና መጀመሪያውን ክፍል የጻፈ ሰው አንድ ከሆነ ዕብራውያን በከነዓን ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ የነበረው ሰው መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደሙሴ ያለ ነቢይ ከዚህ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልነሣም "በማለት ስለሙሴ ይተርካልና" ዘዳግም 34፥10-12/። በእስራኤል ላይ ስለሚነግሰው ንጉሥ በኦሪት ዘዳግም /17፥14-20/ የተሰጠው መመሪያ ሳሙአል በኋላ ስለ አዲስ የእስራኤል ንጉሥ የሰጠው መመሪያ እንደሆነ በአንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ተገምቶአል። ይህንም የሚመስሉ አንዳንድ ክፍሎች በኋላ ዘመን የተጻፉ ይመስላሉ። እንዲህ ከሆነ የመጽሐፉን አብዛኛውን ክፍል ማን ጻፈ? ሙሴ ነው? ወይስ ሌላ ሰው የመሴን መጨረሻ ንግግር በነጻነት አዘጋጅቶት አቀረበ።

የመጽሐፉ አብዛኛው ክፍል ያለጥርጥር በሙሴ የተጻፈ ነው። ለዚህም ከውስጥና ከውጭ የተገኙትን አስረጂዎች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. የውስጥ ማስረጃዎች ዘዳግም 31፥9-26 ወዘተርፈ።
2. የውጭ ማስረጃዎች 1 ነገሥ 2፥3፣ 8፥53

2ኛ ነገሥት 14፥5-6፣ 18፥6-12። እነዚህን ከዘዳግም 19፥9፣ 9፥26፣ 24፥16፣ 10፥20 ጋር አመዛዝን ጌታችንና ሐዋርያት ከኦሪት ዘዳግም ሲጠቅሱ አብዛኛውን ጊዜ የሙሴ ጸሐፊነት ጨምረው ጠቅሰዋል። ማቴ 19፥7-8፣ ማር 10፥3-4፣ ዮሐ 5፥46-47፣ ማር 12፥19፣ ሉቃ 20፥28 ወዘተርፈ። ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ባረው ቀዳማዊ ስብከቱ ከዘዳግም ወስዶ በተናገረው ክፍል ላይ የተጠቀሰው ክፍል በሙሴ የተነገረ መሆኑን አረጋግጦአል /የሐዋ 3፥22/። ቅዱስ እስጢፋኖስ በሐዋርያት ሥራ 7፥37 ላይ ያንኑ የጴጥሮስን ቃል ደግሞታል። እንደዚሁም ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 10የ19-20 ኦሪት ዘዳግም በሙሴ የተዘጋጀ መሆኑን በሚያስረዳ መንገድ ተነግሮአል። እነዚህንም የመሰሉ ሌሎች ማስረጃዎች በሐዲስ ኪዳን በብዛት ይገኛሉ። ከዚህም ሌላ በቤተ እስራኤል መምህራንና በቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ሊቃውንት ዘንድ የዘዳግም ጸሐፊ ሙሴ መሆኑ በትክክል ይታመናል።

ዓላማው

ኦሪት ዘዳግም፡- ሙሴ የሕዝብ እስራኤል መሪ ሆኖ ለብዙ ዓመታት ካገለገለ በኋላ የአገልግሎቱ ዘመን ፍጻሜ ሲቃረብ በመድረ በዳ ውስጥ ተወልዶ ላደገው አዲስ ትውልድ ቀደሞ በደብረ ሲና የተሰጠውን ሕግ በልዩ ልዩ ንግግር ምክርና ማሳሰቢያ እየከለሰ በሞዓብ ሜዳ የተናገረውን ያስረዳል፡፡

አከፋፈሉ

ኦሪት ዘዳግም በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል፡፡

ሀ. መጀመሪያው የሙሴ ንግግር ከኮሬብ እስከ ሞዓብ ምዕራፍ 1፥1-4፣ 43

በዚህ በመጀመሪያ ክፍል ሙሴ እግዚአብሔር ከግብጽ ጀምሮ ለእስራኤላውያን ያደረገው ታሪክ ሁሉ በድጋሚ ልብን ከሚነካ ጋር ለአዲሱ ትውልድ ይተርካል፡፡

1. ምዕራፍ 1፥1-5 የንግግር መግቢያ ቁጥር 6-18 ምድሪቱን ስለመያዝና አለቆቹን ስለመምረጥ የተሰጠ ትእዛዝ ቁጥር 19-46 ሕዝቡ በቃዴስ በርኔ መቆየታቸው፡፡
2. ምዕራፍ 2፥1-25 በዓዶም በሞዓብና በአሞን በኩል የተደረገው ጉዞ፡፡ ቁጥር 26፥3-11 ሆሴቦንና ባሃሳን በእስራኤላውያን ድል መሆናቸውና መያዛቸው፡፡ ምዕራፍ 3፥12-22 የነገደ እስራኤል በምሥራቅ ዮርዳኖስ መስፈራቸው፡፡ ቁጥር 23፥29 ጸሎተ ሙሴና የጸሎቱ መልስ፡፡
3. ምዕራፍ 4፥1-14 ለእስራኤላውያን ሁሉ በአደባባይ በግልጥ ስለሚነገረው ሕግ መግቢያ፡፡ ቁጥር 15-31 የሕጉ /ዲካሎግ/ የመጀመሪያው ክፈል ትንታኔ፡፡ ቁጥር 32-40 በቃል ኪዳን የእስራኤል ልዩነት /ልዩ ሕዝብ መሆን ቁጥር 41-43 ሀገረ ምስካይ/ /የመማፀኛ ከተማዎች/

ለ. ሁለተኛው የሙሴ ንግግር የመጽሐፈ ሕጉ መግቢያ ምዕራፍ 4፥4411፣ 32

በዚህ በሁለተኛውና በሚቀጥለው 3ኛው ክፍል ሙሴ ከዘጸአት እስከ ዘኁልቁ ባሉት 3 መጻሕፍት የተሰጠውን ሕጐች እየከፈለ በአጭር አገላለጥ ይናገርል፡፡

1. ምዕራፍ 4፥44-49 የንግግሩ መግቢያ
2. ምዕራፍ 5፥1-22 ዐሥርቱ ቃላት በዘጸአት ምዕራፍ 20 ከተነገረው ክፍል ከጥቂት ልዩነት ጋር በድጋሚ ተነግረዋል፡፡ ቁጥር 23-33 ሕጉን ለማብራራት አለቆቹን መሰብሰብ /መምረጡ/

3. ምዕራፍ 6፥1-19 ሕዝቡ ወደ ተስፋ ሀገራቸው ሲገቡ ቃል ኪዳኑን በታማኝነት እንዲጠብቁ የተሰጣቸው ምክር፡፡ ቁጥር 20-25 የእስራኤልን ከግብጽ በታላቅ ተአምር መውጣት ያስታውሳል፡፡
4. ምዕራፍ 7፥1-16 እስራኤላውያን ከከንዓናውያን ጋር ሕርመት እንጂ ንብረት እንዲኖራቸው ፈጽመውም እንዲያጠፉአቸው ጥብቅ ትእዛዝን ምክር ይሰጣል፡፡ ቁጥር 17-26 ድል አድራጊ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሰው የእግዚአብሔርን ኃይል መመልከትና በእርሱም መመካት የሚገባው መሆኑን ይገልጣል፡፡ ይህ ክፍል ኦሪት ዘዳግም የተጻፈ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከገቡ በኋላ ሳይሆን ከመግባታቸው በፊት መሆኑን በትክክል ያስረዳል፡፡ ምክንያቱም እስራኤል ወደ ከነዓን እንደገቡ ከንዓናውያንን እንዲያስወግዱና በቦታቸው እነርሱ እንዲኖሩ ይናገራልና፡፡
5. ምዕራፍ 8፥1-20 እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ሁሉ ሕዝቡ እንዲያስታውሱ የተሰጠ ምክር ነው፡፡
6. ምዕራፍ 9፥1-7 ሕዝበ እስራኤል ኃያላን አሕዛብን ድል ያደረጉ ወደ ተስፋ ሀገራቸውም የሚገቡ በጽድቃቸውና በልባቸው ቅንነት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሆኑን ይገልጣል፡፡ ቁጥር 8-29 የኮሬቡንና የቴብራውን ዐመድ /ክህደት/ ያሰታውሳል፡፡
7. ምዕራፍ 10፥1-11 የቃል ኪዳኑ መታደስ የአሮን ሞት የልጁ የአልአዛር ክህነትና የነገደ ሌዊ መለየት ቁጥር 12፥11፥7 በቃል ኪዳን ጸንቶ መኖር እንደሚገባ ይናገራል፡፡ ምዕ 11፥8-25 የቃል ኪዳኑ ፍጻሜ ተስፋ ምድረ ከነዓን መሆኑን ያስረዳል፡፡ ቁጥር 26፥32 ለሕጉ መታዘዝ በረከትን እንደሚያሰጥ፣ አለመታዘዝ ግን መርገምን እንደሚያመጣ ይናገራል፡፡ እንደዚሁም ሕዝቡ በረከትን ወይም መርገምን ለመምረጥ የነጻነት መብት እንደአለባቸው ይገልጣል፡፡

ሐ. መጽሐፈ ሕጉ ምዕራፍ 12፥1-28-68

ይህ ክፍል ከአንዳንድ ጥቃቅን ልዩነት በቀር የሲናውን ሕግ የያዘ ነው፡፡ ዋና ዓላማው የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ወደ ከነዓን ሀገር ሲገቡ ውስጣዊ ሕይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ለማድረግ ነው፡፡

1. ምዕራፍ 11፥1-14 አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽምበት አንድ የተለየ መካነ አምልኮት መኖር እንደሚገባው ይናገራል፡፡ ይህ ሕግ በዘጸአት 20፥21 ላይ ስለመሥዋዕት ከሚናገረው ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በዚህ በዘዳግም የተለየ ቅዱስ

መካን አምልኮት የተባለች ኢየሩሳሌም መሆኗ ግልጥ ነው። ነገር ግን ሌሎች መካናት አምልኮት ሲሉ፣ ጌባል /ምዕራፍ 27፥5/ መኖራቸው የታወቀ ነው። ይህ ከሆነ ዘዳግም የተዘጋጀው በ7ኛው ምዕተ ዓመት ይሆናል ብለው የሚተቹ ሊቃውንት አሉ። ይሁን እንጂ ይህ አስተያየታቸው የሚጸናበት ምክንያት አለ። ይኸውም በቁጥር 5 ላይ የተጠቀሰው ቦታ ኢየሩሳሌምን ሳይሆን ማንኛውንም መካነ አስተርእዩ ይመለከታል። ይህንም ከቁጥር 15-28 ስ ለቅዱስና ርኩስ ሥጋ የተሰጡ ሕጐችን ይዞአል። ቁጥር 15 እና 16 ከዘሌዋውያን 17፥1 ጋር የሚጋጭ ይመስላል። ነገር ግን ሊጋጭ የማይችልበት ምክንያት አለ። ይኸውም ዘሌዋውያን የሚናገረው ሕዝቡ በምድረ በዳ ሳሉ የሚያርዱትን ወደ መገናኛው ድንኳን ማምጣት እንዳለባቸው ነው። ዘዳግም ግን የሚናገረው፡- ሕዝቡ ወደ ከነዓን ከገቡና ከተደላደሉ በኋላ በየቤታቸው አርደው እንዲበሉ ነው። በምድረ በዳ ገና ሕጉን በመለማመድ ላይ ስለነበሩ ታዛዥነታቸውን ለመግለጥ ያህል ወደ መገናኛው መምጣት ግዴታ ነበረ። አሁን ግን ወደ ተስፋ ሀገራቸው ሲገቡ ሕጉን ስለ ለመዱ በቤታቸው እንዲያርዱና እንዲበሉት ዘዳግም ይናገራል። ቁጥር 29፥32 እስራኤላውያን በከነዓን የነበረውን አምልኮተ ጣዖት እንዳይከተሉ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

2. ምዕራፍ 13፥1-18 የመምለክያን ጣዖት ቅጣትና ወደ አምልኮተ ጣዖት የሚያደርሱ ነገሮች ቁጥር 1 ከምዕራፍ 4፥2 ጋር በምስጢር ተመሳሳይ ነው። በዚህ ክፍል ወደ አምልኮተ ጣዖት የሚመሩት 3 ምክንያቶች ተጠቅሰዋል።
   ሀ. ቁጥር 2-6 ወደ አምልኮተ ጣዖት የሚመሩ ነቢይና ሕልም ሐላሚ
   ለ. ቁጥር 7-12 ቅርብ ከሆኑ የሥጋ ዘመዶችና ወዳጆች የሚመጣ የአምልኮተ ጣዖት ፈተና።
   ሐ. ቁጥር 13-18 ወደ አምልኮተ ጣዖት የምትመራ ከተማ
3. ምዕራፍ 14 እስራኤላውያን ሊከለክሉአቸው የሚገቡ ልምድ አሕዛብና ርኩስ መባልዕት እንደዚሁም የቀዳማያት ዐሥራት በዚህ ምዕራፍ ተዘርዝረዋል። ቁጥር 1-2 ይህ ግብረ አሕዛብ ቀደም ብሎ በዘሌዋውያን 19፥28 ተጠቅሶአል። ይህም ግብረ አሕዛብ በከንዓን የተስፋፋ ነበር። /ኢሳ 3፥24፣ ኤር 16፥6፣ አሞጽ 8፥10/ ቁጥር 3-21 ይህ ክፍል ስለ ርኩስና ንጽሕ እንስሳ ዝርዝር ይናገርል። ይህም ከዘሌዋውያን 11፥2-20 ካለው የርኩስና የቅድስ እንስሳ አንቀጽ ጋር ይመሳሰላል።

መሠረቱ ዘሌዋውያን ነው። ይህ ግን የዚያ አስተዋጽኦ ነው ቍጥር 4 እና 5 በዘሌዋውያን አልተጠቀሱ። ከዚያ ስላልተነገሩ የማይበሉ ስለሆኑ አልተጠቀሱም እንዳይሉና ሕዝቡ እንዳይከለክሉአቸው እንዲበሉ የተፈቀዱ መሆናቸውን ለማስረዳት ከዚህ ዘርዝሮ ተናገራቸው። ቍጥር 21 የዘጸአት 23፥19፣ 34፥26 ተደጋሚ ነው። ቍጥር 22-29 ዐሥራቱን ስለማቅረብ ይዘረዝራል። ይህ ክፍል ከዘኍልቍ 18፥21 ጋር የሚቃረን ይመስላል። ግን አይቃረንም በቀደመው ሕግ ለምሳሌ ዘሌዋውያን 27፥30፣ ዘኍልቍ 18፥21 ሕዝቡ ገና በዘላልነት ኑሮ በነበረው ጊዜ ዐሥራቱ ለካህናትና ለሌዋውያን ይሰጥ ነበር። አሁን ሕዝቡ ወደ ከንዓን ገብተው የዕረፍት ኑሮ መሣር ከጀመሩ በኋላ ሕዝቡ ራሳቸው በዐሥራቱ ለካህናትና ለሌዋውያን ይሰጥ ነበር አሁን ሕዝቡ ወደ ከንዓን ገብተው የዕረፍት ኑሮ መኖር ከጀመሩ በኋላ ሕዝቡ ራሳቸው በዐሥራቱ እንዲጠቀሙ በዘዳግም ታዘዘ።

4. ምዕራፍ 15፥1-23 ስለባሮችና ድሆች የሚናገሩ ሕጐች።
   ሀ. ቍጥር 1-11 ዓመተ ህድገት /ዘጸአት 23፥20 ... ዘሌዋውያን 25፥1-7
   ለ. ቍጥር 12-18 ዕብራውያን ባሮች ነጻ መውጣት። ይህ ሕግ በዘጸአት 21፥2-6 ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ ደግሞ መነገሩ ግን እንዴት መፈጸም እንደሚችል ለማብራራት ነው።
   ሐ. ቍጥር 19-23 የእንስሳት በኩራት /ዘጸአት 13፥2-12 ዘሌ 27፥26፣ ዘኍ 18፥15/
5. ምዕራፍ 16፥1-17 ሦስቱ ዓመታውያን በዓላት ዘፀ 12 ዘሌዋ 23 ዘኍ 28፥29
   ሀ. ቍጥር 1-8 ፋሲካ ከፋሲካው በግ ጋር የተጠቀሰው መሥዋዕት ሁሉ ለፋሲካ ሳይሆን ከፋሲካ በኋላ ለሰባት ቀናት የሚቀርበው ነው።
   ለ. ቍጥር 9-12 የሰባቱ ሱባዔ በዓል /ዘጸ 23፥16ዋ 34፥22 ዘሌ 23፥15 ... ዘኍል 28፥26/
   ሐ. ቍጥር 13-17 የዳስ በዓል /ዘጸአት 23፥16፣ 34፥22 ዘሌ 23፥33 ዘኍ 29፥12/
6. ምዕራፍ 16፥17፣17፥20 የፍትሕ አስተዳደርና የንጉሥ ምርጫ፣
   ሀ. ቍጥር 18-20 የዳኞች ሹመት፣
   ለ. ቍጥር 21-22 የአምልኮ ዛፎችና ሐውልቶች መከልከል
   ሐ. ምዕራፍ 17፥1-7 የማምለኪያ ጣዖት ቅጣት
   መ. ቍጥር 8-13 የከፍተኛ ፍርድ ቤት መቋቋም።

ሠ. ቍጥር 14-20 የንጉሡ ምርጫ፡፡ ሕጉ መብታዊ ነው፡፡ ነገር ግን ስለ ንጉስ የቀረቡት ህጎች ሁለ በጣም የጠበቁ ናቸው፡፡ ንጉሡ እስራኤላዊ መሆን አለበት /ቍጥር 15/ ሕዝቡን ወደ ግብጽ ለመመለስ ፈረሶችን ማብዛት የለበትም /ቍጥር 16/፡፡ ከ1ኛ ነገሥት 10፥28 ጋር አመዛዝን፡፡ ብዚ ሚስቶችን ማብዛት ወርቅና ብር ለራሱ ማከማቸት አይገባውም /ቍጥር 17/፡፡ ነገር ግን የሕጉን መጽሐፍ ቅጅ መያዝና በእርሱ መመራት አለበት፡፡

ከዚህ የተጠቀሰው የንጉሡ ወግና ሥርዐት በ1ኛ ሳሙኤል 8፥6-17 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ለተጠየቀው ንጉሥ ከተሰጠው ወግና ሥርዓት ጋር የሚጣላ፣ መስሎ ይታያል፡፡ ነገር ግን ሊጣላ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ ጊዜው ሳይደርስ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ስለመጠየቁ በ1ኛ ሳሙኤል 8፥6-11 ላይ ያለው የንጉሥ ወግና ሥርዐት ተነገራቸው፡፡ ከዚህ ከተጠቀሰው ንጉሥ ትንቢታዊ ንጉሥ ግን፡- ጊዜው ሲደርስ ለሚነግሰው ለንጉሠ ነገሥት እግዚአብሔር አምሳል፣ ስለሚሆን፣ በ1ኛ ሳሙኤል ከተነገረው የተለየ ወግና ሥርዓት ነበረ፡፡ ጊዜው ሲደርስ የሚነግሠው ንጉሥ፡- ጨቋኝ ራስ ወዳድ ተቀናቃኝ አልባ መሆን የለበትም፡፡ ግን በእግዚአብሔር ሕግ የሚመራ አስተዋይና በትክክለኛ ፍትሕ ለመንግሥቱ በረከት የሚያመጣ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሠጥ መሆን አለበት፡፡

7. ምዕራፍ 18 ካህናት ሌዋውያንና ነቢያት

ሀ. ቍጥር 1-8 የካህናትና የሌዋውያን መብት፡፡ በቍጥር አንድ ላይ “ሌዋውያን ካህናት” የሚለው ቃል በካህናትና ሌዋውያን መካከል ዩልነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም “የሌዊ ነገድ ሁለ” በሚለው፣ በካህናትና /ቁ 3-5/ በሌዋዊ ቍጥር 6-8 መካከል ባለው ልዩ አጠራር ይታወቃል፣ በዚህ መሠረት ካህናት የሚባሉ የአሮን ልጆች ናቸው፡፡ ሌዋውያን የሚባሉት ደግሞ የሌሎች ደቂቀ ሌዊ ልጆች ናቸው፡፡

ለ. ቍጥር 9-22 የነቢያ ሕግ እስራኤላዉያን ወደ ተስፋ ሀገራቸው ሲገቡ መለኮታዊ አስተርእዮ በተጨማሪ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህም ነቢይ መኖር ግድ አስፈላጊ ነው፡፡ /1/ ቍጥር 9-13 እስራኤላዉያን ሊማሩአቸው የማይገቡ ዘጠኙ የከነዓናውያን አስቃቂ ነገሮች፡፡ /2/ ቍጥር 14 እና 15 በእነዚህ ዘጠኝ አሰቃቂ ነገሮች ምክንያት ከነዓናውያን ሀገራቸውን መልቀቅ እንዳለባቸው ይናገራል ነቢይ ይነሳልና ከንቱ የሆኑ የከነዓናውያን ምርቶች አያስፈልጉም፡፡ /የኪም ላኪ ያህዌ/ እግዚአብሔር ነቢይ ያስነሣልሃልና፡፡ ስለዚህ መዳኢያችን ለማስተዋል፣

የከነዓን ሞራ ገላጭ አያስፈልግህም ማለት ነው፡፡ ነቢዩ /ሀ/ እስራኤላዊ መሆን አለበት /ለ/ እንደሙሴ ያለ በእግዚአብሔርና በስዎች መካከል ማዕከላዊ መሆን አለበት /3/ ቁጥር 16-18 የነቢዩ መነሣት እስራኤል በኮሬብ ማዕከላዊ እንዲሆንላቸው በጠየቁት /በለመኑት/ መሠረት ነው፡፡ /4/ ቁጥር 19-32 በእውነተኛው በሀሰተኞቹ ነቢያት መካከል ልዩ መታወቂያ ይሆን ዘንድ የተሰጠ ምልክት /መመዘኛ/

8. ምዕራፍ 19 የተለያዩ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ሕጐች ቁጥር 1-13 ሀገር ምስካይ /ዘኁልቁ 35÷9-34፣ ዘጸአት 21÷12-14/ ቁጥር 14 ወሰንና ምልክቶችን /ድንበሮችን/ ማፍረስ ወይም ማለፍ እንዳይገባ ይናገራል፡፡ ቁጥር 15-21 ስለ ምስክርነት የሚናገሩ ሕጐች፡፡
9. ምዕራፍ 20 ጦርነትን የሚመለከቱ ሕጐች፡፡ ቁጥር 1-9 ስለውትድርና አገልግሎት አስፈላጊነት ይናገራል፡፡ ቁጥር 10-20 ወረራን ይመለከታል፡፡
10. ምዕራፍ 21 ደረቅ ሕጐች፡፡ ቁጥር 1-9 በአንድ ባልታወቀ ሰው ስለተገደለ ሰው የምርመራ ሁኔታ ይናገራል፡፡ ይህም ዓይነት ምርመራ ከሙሴ በፊት የነበረ ንጉሥ ነው በሐሙራምቢ ሕግ /24/ የታወቀ ነበር፡፡ ቁጥር 10-14 በጦርነት የተማረከች ሴትን ማግባት የሚመለከት ሕግ ነው፡፡ ቁጥር 15-17 የበኩር ልጅ መብት ቁጥር 18-21 የባለጌ ልጅ ቅጣት ቁጥር 22-23 እንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ሰው ቀብር በዕለቱ መሆን እንዳለበት ይናገርል፡፡
11. ምዕራፍ 22 ደረቅ ሕግ ቁጥር 1-12 አንድ እስራኤላዊ ለባልንጀራውና ለሌላው ፍጥረት ሕይወት ሊያደርገው የሚገባውም ያብራራል፡፡ ቁጥር 13-30 ክብረ ንጽሕናን ዝሙትን፣ ከታጨች ልጃገረድና ካልታጨች ልጃገረድ ጋር ስለሚደረግ ኢሕጋዊ ሩካቤ የሚናገሩ ሕጐችን ይዞአል፡፡
12. ምዕራፍ 23 በእግዚአብሔር ቅዱስ ጉባኤ ውስጥ ለመገኘት የዜግነት መብት ቁጥር 10-14 በጦርነት ጊዜ ሰፈርን ስለማጽዳት ይናገርል፡፡ ቁጥር 15-18 የኮበለለ አገልጋይ እንደገና ወደ ጌታው መመለስ እንደሌለበትና በእስራኤል መካከል ጋለሞታ መኖር እንደማይገባ ይገልጣል፡፡ ቁጥር 19-25 የተለያዩ መብቶችን ይዘረዝራል፡፡
13. ምዕራፍ 24 የተለያዩ ሕጐችን የያዘ ምዕራፍ ነው፡፡ ቁጥር 1-4 በታወቀ ምክንያት ከተፈታችው ሴት ጋር እንደገና መጋባት የማይገባ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ቁጥር 5

አዲስ የተጋቡ ሰዎችን ከጦርነት /ውትድርና/ አገልግሎት ይከለክላል። ቊጥር 6-9 የተለያዩ ክልክሎችን ዝርዝር ይዞአል። ቊጥር 10-15 ድሃን መጨቆን እንዳይገባ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። ቊጥር 16-22 ስለኢርቱዕ ፍትሕ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎችና ለድሃ መደረግ የሚገባውን ልግስና የሚመለከቱ ሕጐች።

14. ምዕራፍ 25 የአካል ቅጣትን የሚመለከቱ ሕጐች ቊጥር 1-3 የአካል ቅጣት ከተወሰነው በላይ እንዳይሆን ይከለክላል። ቊጥር 4 ለእንስሳት ሰብአዊ ርህራሄ ሊደረግላቸው የሚገባ መሆኑን ያስረዳል። ቊጥር 5-10 ወንድም ዋርሳውን ለማግባት ስላለው መብት ይናገራል። ቊጥር 11-16 የተለያዩ ደረቅ ሕጐችን ይዟል። ቊጥር 17-19 አማሌቃውያንን ለማጥፋት የተሰጠ ትእዛዝ ነው።
15. ምዕራፍ 26 የእህሉን በኩራትና /ቀዳማያት/ ዐሥራቱን በማቅረብ ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ይናገራል። ቊጥር 12-15 የእህሉን በኩራት /ቀዳምያት/ የማቅረብ ሥነ ሥርዓት። ቊጥር 12-15 የ3ኛ ዓመት ዐሥራት ሥነ ሥርዓት ቊጥር 16-19 የመጽሐፈ ኪዳን /ሕጉ/ ፍጻሜ ከዚህ ከእህሉ ቀዳምያት ሕግ ጋር ይሆናል።
16. ምዕራፍ 27፥1-26 የሕጉ መጽደቅ ወይም መረጋገጥ። ቊጥር 1-8 እስራኤላውያን ዮርዳኖስን በተሻገሩ ጊዜ በደብረ ገባል ትልቅ ደንጋይ እንዲያኖሩ በዚያም ላይ ሕጉን እንዲጽፉ እንደዚሁም መሥዋዕት እንዲሠሩ መታዘዛቸውን ይናገራል። ቊጥር 9-10 ሕዝቡ ለሕጐ እንዲታዘዙ ይናገራል። /ያውጃል/ ቊጥር 11-26 መርገመ ጌባል።
17. ምዕራፍ 28 በረከትና መርገም። 1-14 ለሚታዘዝ በረከቱን ቊጥር 15-68 ለማይታዘዙ መርገሙን ያውጃል።

የመጨረሻው የሙሴ ንግግር የሙሴ መጨረሻ ቀንና ሞቱ ምዕራፍ 29፥1-34፥12።

1. ምዕፍ 29፥1-14 የታደሰው ቃል ኪዳን በአስተዋጽአ ቀርቦአል ቊጥር 15-29 ስለ ቃል ኪዳኑ ተግባራዊነት የተሰጠ ምክር ነው።
2. ምዕራፍ 30፥1-20 የቃል ኪደኑ መደምደሚያ። ከሕይወትና ሞት ከበረከትና መርገም ለእስራኤል የቀረበ ምርጫ።
3. ምዕራፍ 31፥1-29 የመጨረሻ ዝግጅት ቊጥር 1-8 የኢያሱ መሾም ቊጥር 9-13 ሕጉ በየሰባት ዓመት መነበብ እንደለበት ይናገራል። ቊጥር 14-23 ለኢያሱ

የተሰጠ ሥልጣንና መዝሙሩን ስለ መጻፍ የተነገረ ትእዛዝ ነው። ቊጥር 24-30 ሕጉ በታቦቱ ውስጥ መቀመጥ እንዳለበት ይናገራል።

4. ምዕራፍ 32 መዝሙረ /ጸሎት/ ሙሴ/። ቊጥር 1-3 የመዝሙሩ /የጸሎቱ/ መግቢያ። ቊጥር 4-6 የመዝሙሩ ዓላማና የእግዚአብሔር ታማኝነት ቊጥር 7-14 እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው ነገር ሁሉ ከጥንት ጀምሮ ይመረምራል። ቊጥር 15-18 የእስራኤላውያን ክህደት ያስታውሳል። ቊጥር 19-33 እግዚአብሔር ዓመፀኞችን ይበቀላል። ቊጥር 34-43 ምህረት ለሕዝቡ በቀልም በጣቶቹ እንደሚሆን ይናገራል። ቊጥር 44-52 የመዝሙሩ ፍጻሜና ሙሴ ምድረ ርስት እንደማይገባ የተነገረው ቃል።
5. ምዕራፍ 33 ሙሴ ለአሥራ ሁለቱ ነገድ እስራኤል የሰጠው በረከት በ3 ክፍሎች ይከፈላል። /1/ ቊጥር 1-5 አርእስትና መግቢያ ነው /2/ በቊጥር 6-25 ለእየነገዱ ነገሩ በረከቶች /3/ ቊጥር 26-29 መደምደሚያ። ይህ በረከት በሙሴ ተነግሮአል። ነገር ግን በእርሱ የተጻፈ አይመስልም። በቊጥር 1 ላይ እንደምንመለከተው ጸሐፊው ሌላ ነው። ከዚህም ጋር ቊጥር 4 ሙሴን ለጽሕፈቱ ባዕድ ያስመስለዋል ሙሴ አሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል የባረካቸው በሚሞትበት ጊዜ ስለነበረ ተናግሮት ሳይጽፈው ሞቶአል። ይህንና የሚቀጥለውን ምዕራፍ 34 ተከታዩ ኢያሱ ጽፎታል። ስምዖንን ለበከረት አልጠቀሰውም ሰብአ ቡቂማን ተተናኩሎ ነበር። ሰባቱ ያዕቆብም ቢያነሣውም በቅሬታ እንጂ በደስታ አይደለም /ዘፍ 49÷5-7/
6. ምዕራፍ 34÷1-12 የሙሴ ሞትና ቀብር የኢያሱ በሙሴ እግር መተካት። ፊሉ አይሁዳዊ ዘእስክራድርያ ዮሴፍ ወልደ ኮርዬን ይህን ምዕራፍ ሙሴ ስለራሱ ሞተ አስቀድሞ እንደጻፈው አምነዋል። /ሰባ ባትራ/ ያልሙድ 14/ ነገር ግን ይህ የዘዳግም መሠረሻ በብዙዎች የአይሁድና የክርስቲያኖች ሊቃውንት ዘንድ ለኢያሱ ተሰጥቶአል። አብን /ወልደ/ እዝራ የተባለው ረቢም ይህ 34ኛው ምዕራፍ በኢያሱ መጻፉን ገምቶ ተናግሮአል።

እርግጥ ነው ይህ የመጨረሻው ምዕራፍ በኢያሱ ባይሆንም ከሙሴ በኋላ በአለብዎት እግዚአብሔር ወይም በመንፈሰ እግዚአብሔር በሌላ እጅ መጻፉ የማይጠረጠር ነው። ምክንያቱም ሙሴ ለራሱ ሞትና ቀብር ታሪክ ከሞት በኋላ ሊጽፍ አይችልምና።

ማጠቃለያ

- አምስተኛው የኦሪት መጽሐፍ ዘዳግም ሕግ መባሉ ከዘፀዓት ጀምሮ እስከ ዘኁልቁ ያሉት ሦስቱ የኦሪት መጻሕፍት ተደግመው ተከልሰው ስለተፃፈበትና ከግብፅ ለወጣው ለሁለተኛው ትውልድ ስለተነገረ ነው፡፡
- በቤተ እስራኤል መምህራንና በቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ሊቃውንት ዘንድ የዘዳግም ፀሐፊ ሙሴ መሆኑ በትክክል ይታመናል፡፡
- ኦሪት ዘዳግም በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል፡፡
- የዘዳግም የመጨረሻው ምዕራፍ በኢያሱ ባይሆንም ከሙሴ በኋላ በአለብዎት እግዚአብሔር ወይም በመንፈሰ እግዚአብሔር በሌላ እጅ መጻፉ የማይጠረጠር ነው፡፡ ምክንያቱም ሙሴ ስለራሱ ሞትና ቀብር ታሪክ ከሞት በኋላ ሊጽፍ አይችልምና፡፡

የኦሪት ዘዳግም የሙከራ ጥያቄዎች

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ በኦሪት ዘዳግም ካነበብከውና ካስተዋልከው በመነሳት ለሚከተሉት ጥያቄዎች የፅሑፍ መልስ ስጥ፡፡

1. አምስተኛው የኦሪት መጽሐፍ ለምን ዘዳግም ተባለ?
2. ኦሪት ዘዳግም በሙሴ የተፃፈ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድነው?
3. ሕዝበ እስራኤል ኃያላን አሕዛብን ድል ያደረጉበት ምስጢር ምንድነው?
4. በካህናትና በሌዋውያን መካከል ያለውን ልዩነት በጽሑፍ አብራራ?
5. ሙሴ ለአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የሰጠው በረከት በስንት ይከፈላል?

ክፍል፡ ሁለት

አጭር መግለጫ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀመዝሙሬ ከአምስቱ የአሪት መጻሕፍት ቀጥሎ የምታነግኛቸው መጻሕፍት ሁለተኛው የብሉይ ኪዳን ቀኖና ክፍል ነቢያት ተብሎ ስለሚጠራውና ነቢያት በስንት እንደሚከፈሉና አመዳደባቸው እንዴት እንደሆነ የነቢያትን መጻሕፍት ከመጀመርህ በፊት ለግንዛቤ በሚረዳ መልኩ የቀረበውን አጭር መግለጫ ተመልከተው ብዙ ማስተዋል ታገኝበታለህ።

ነቢያት

ሁለተኛው የብሉይ ኪዳን ቀኖና ክፍል ነቢያት ተብሎ ይጠራል። ይህም መጻሕፍቱ የትንቢት ይዘት ስላላቸው ብቻ ሳይሆን ጸሐፊዎቹ ግብረ ትንቢት ስላላቸው ነው።

ነቢያት በሁለት ክፍል ይከፈላሉ። እነዚህም ቀደምትና ደኅርት ይባላሉ። በመጀመሪያው ክፍል አራት መጻሕፍት ይገኛሉ። እነርሱም፡- ኢያሱ፣ መሳፍንት 2/ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት እያንዳንዱ ጭምር ስለ አንድ ይቈጠራል ስለዚህ አራት መጻሕፍት ይሆናሉ።

በመጀመሪያው ክፍል ካሉት መጻሕፍት ሁለቱ መሳፍንትና ነገሥት /አኖኒሞስ/ የጸሐፊ ስም የላቸውም። አጻጻፋቸውም እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከገቡ ጊዜ ጀምሮ እስከ ፄዋዊ ድረስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን ነገር ሁሉ መተረክ ነው።

ሁለተኛው የነቢያት ክፍል "ደኅርት" ነቢያት በመባል የታወቀ ነው። በዚህ ክፍልም አራት መጻሕፍት አሉ። እነዚህም፣ ኢሳይያስ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል እና ዐሥራ ሁለቱ ነቢያት ናቸው። በአይሁድ ሊውንት የብሉይ ኪዳን አመዳደብ ዐሥራ ሁለቱ ነቢያት እንደ አንድ ነጠላ መጽሐፍ ይቆጠራሉ። አንዳንድ ጊዜ ይህ ሁለተኛው ክፍል የጽሑፍ ጽሕፈት ነቢየት እየተባለ ይጠራል። ይህን የራሳቸውን መጽሐፍ ራሳቸው ስለጻፉ የተሰጠ ስያሜ ነው። /ኢሳ 8÷1፣ 30÷8፣ ዕንባ 2÷1፣ ኤር 30÷2፣ 36÷1።/ ደግሞም ይህ ስያሜ ከእግዚአብሔር የመጣላቸውን ቃል በሌላ ሰው ማጻፋቸውን ያመለክታል /ኤር 36÷4፣ ኢሳ 8÷16/

ዳኅርት ነቢያት እንደገና በሁለት ንኡሳን ክፍሎች ይከፈላሉ እነዚህም፡- ዐበይት ነቢያት ደቂቀ ነቢያት ይባላሉ። ዐበይት፡- ኢሳይያስ፣ አርምያስ፣ ሕዝቅኤል ሲሆኑ ደቂቅ

፬ሥራ ሁለት ነቢያት ናቸው። ስያሜው የጽሕፈት ብዛትና ማነስን እንጂ የዘመነ ቅድምናን አየመለክትም።

መጽሐፈ ኢያሱ

መግቢያ

ውድ በሩቅ ያለኸው ደቀ መዝሙሬ ከቀደሙት ነቢያት የመጀመሪያ መጽሐፍ ስለሆነው መጽሐፈ ኢያሱ ባማረ አቀራረብ ተዘጋጅቶ ቀርቦልሃል በማስተዋል ተመልከተው የዝግጅቱ አቀራረብም፡-

- ስለ መጽሐፈ ኢያሱ መጽሐፍ ሥም አሠያየም፡
- መጽሐፈ ኢያሱ በቀኖና መጻሕፍት አቀማመጥ፣
- ስለ መጽሐፉ ፀሐፊ፣
- ስለ መጽሐፉ ዓላማ፣
- ስለ መጽሐፉ አከፋፈልና /ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ድረስ በዝርዝር ቀርቦልሃል ተመልከተው።

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

የቀደምት ነቢያት መጀመሪያ መጽሐፍ፡- መጽሐፈ ኢያሱ ነው። ይህ መጽሐፍ የታሪኩ ዋና ባለቤት በሆነው በኢያሱ ስም ተሰይሞአል። በዕብራይስጥ፡- ኢያሱ የሚለው ስም አራተ ዓይነት ቅርጽ /ፎርም/ አለው። 1. የሆሹእ /ዘዳግም 3፥21/ 4 የሹአ ዘኑልቁ 13፥15/ ነህምያ 8፥217። በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ደግሞ ስሙ ኢየሱስ የሚል መልክ አለው። በሱልጌቱም ጁሱ ተብሎ ይጠራል። በግእዙም ሆነ በአማርኛው ትርጉም ደግሞ ከሰብዓ ሊቃናት አጠራር ባልራቀ ስያሜ ኢያሱ የሚል መልክ ይዞአል።

ኢየሱ ማለት "እግዚአብሔር መድኃኒት ነው" ማለት ነው። ኢያሱ የተወለደው በምድረ ግብጽ ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ የ54 ዓመት ሰው እንደ ነበር ይገመታል። ወደ ከነዓን ከተላኩት 12 ሰላዮች /ሰብአዐይን/ አንዱ ኢያሱ እንደነበር ይታወሳል። ኋላም በሙሴ እጅ ተቀብሎ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆኖአል።

መጽሐፈ ኢያሱ በቀኖና መጻሕፍት አቀማመጥ

በሦርያው ትርጉም፡- ከመጽሐፍተ ሙሴ ቀጥሎ መጽሐፈ ኢዮብ ይገኛል። ይህም ሊሆን የቻለው የመጽሐፈ ኢዮብ ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ በሦሪያ ቤተ ክርስቲያን

ስለሚታመን ነው። ነገር ግን በዕብራይስጡ የብሉይ ኪዳን ቀኖና መጽሐፍ ኢያሱ አምስቱ ብሔረ ኦሪትን /መጻሕፍተ ሙሴን/ ይከተላል። ትክክለኛ ቦታውም ይህ እንደሆነ በሁሉ ዘንድ ይታመናል።

በጥንተ ቤተ ክርስቲያን፡- አክታቴዎክስ እና ኤፕታቴዎክስ የሚል አከፋፈል እንደነበረ የተረጋገጠ ነው መጻሕፍት ማለት ነው። /አክታስምንት ቴዎስስ መጻሐፍ/ ኤፕታቴዎክስ ማለትም ሰባት መጻሕፍት ማለት ነው። /ኤፕ 7 ቴዎኮስ መጽሐፍ/

የጥንት የግሪክ የመጻሕፍት ቀኖና /ዝርዝር/ ከዘፍጥረት እስከ ሩት አንድ ክፍል በማድረግ ይቆጠራል። ይህንም አክታቴዎክስ ይሉታል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ቀኖናም ከዘፍጥረት እስከ ሩት ያሉት መጻሕፍት "ስምንት ብሔረ ኦሪት" መባላቸው ከዚህ ትውፊት መሠረት ነው። እስከ መሳፍንት ድረስም አንድ አድርገው ኤፕታቴዎክስ ማለት ሰባቱ ብሔረ ኦሪት የሚሉ አሉ።

ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 24፥27፣44 ላይ ለይቶ እንደተናገረው ሕግ /ኦሪት/ የሚባለው በሙሴ ብቻ የተጻፈው ነው። ስለዚህ ሌሎችን ሦስት መጻሕፍት ደርቦ ኦሪት ማለት በብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተባለው የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ፡- የሕግ መጻሕፍት መባል የሚገባው አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ብቻ መሆናቸውን ለይቶና አረጋግጦ ጽፎአል። /ኮንትራ ፒኦኔም 1፥7/ ሳምራውያንም አምስቱን ብሔረ ኦሪት ብቻ ሲቀበሉ ሌሎቹን ይልቁንም መጽሐፈ ኢያሱን እንደ ኦሪት አድርገው አልተቀበሉትም።

ይህ ከሆነ አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ኢያሱን ከአምስቱ መጻሕፍተ ኦሪት ጋር በመቀጠር ስድስቱ ብሔረ ኦሪት ማለት፣ እንደዚሁም ሁለቱን መሳፍንትንና ሩትግ ጨምሮ ሳምንቱ ብሔረ ኦሪት ማለት አይገባም።

ስለዚህ የመጽሐፈ ኢያሱ ቍጥር በአይሁድ ሊቃውንት ሀሳብ መሠረት ከቀደምት ነቢያት ነው እንጂ ከብሔረ ኦሪት ጋር አይደለም።

ጸሐፊው

የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ፡- በምዕራፍ 24 ቍጥር 26 ላይ በተጻፈው ቃለ መሠረት ራሲ ኢያሱ እንደሆነ ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ያምናሉ።

ነገር ግን እንደገና ምዕራፍ 24 ቍ 29-33 ስናነብ ከኢያሱ ሞት በኋላ የተዘጋጀውን ታሪክ እናገኛለን። ስለዚህ መጽሐፉ በሙሉ በኢያሱ የተጻፈ አይመስል። እንደዚሁም ምዕ 19፥47 ያለው ታሪክ ከኢያሱ በኋላ በዘመነ መሳፍንት የተጻፈው መሆኑን በመጽሐፈ

መሳፍንት ምዕ 18፥1-29 ለመረዳት እንችላለን ከዚህም ጋር የሚከተሉት ጥቅሶች ሁሉ ታሪኩ ከተፈጸመ ብዙ ጊዜ ቆይቶ መጽሐፉ እንደ ተዘጋጀ ያመለክታሉ /4፥9፣ 7፥26፣ 5፥9፣ 13፥13፣ 15፥63/

ምዕራፍ 10-13 ላይ ለው ቃል ደግሞ መጽሐፉ ከሌላ የታሪክ ምንጭ የተወሰደ ሀሳብ እንዳለበት ይገልገለ ይህም የታሪክ ምንጭ "መጽሐፈ ያጀር" ይባላል፡፡ ይህም መጽሐፈ ጻድቃን ማለት ነው፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ ነገ እስራኤል ተውጣጥተው ከነዓንን ይመረምሩ የነበሩ ሰዎችም ማስታወሻ እየጻፉ ለኢያሱ ያቀርቡ ስለነበር /18፥4-10/ ለመጽሐፉ ዝግጅት የተለያዩ ምንጮች እንደነበሩ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ዓላማው

መጽሐፈ ኢያሱ፡- እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምድረ በዳ አውጥቶ ወደ ተስፋ ሀገር እንዴት እንደአገባቸው ያሳያል፡፡ ከሙሴ ሞት በኋላ የተፈጸመውን ታሪክ ይዘረዝራል፡፡ እንደዚሁም ኢያሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የሥራ ኃላፊነት እስከ መጨረሻ በታማኝነት እንደጠበቀ ይገልጣል፡፡ ከዚህም ሁሉ ጋር እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ተስፋ ሀገር አንደሚያገባቸው አስቀድሞ የሰጠውን ተስፋ መፈጸሙን ይህ መጽሐፍ ያስረዳል፡፡ /ዘፍ 13፥14-17፣ 15፥7፣ 18-21/ በመጨረሻም ኢያሱ ስለተናገራቸው የመሰነባበቻ ቃላትና ስለ ሞቱ ይተርካል፡፡

አከፋፈሉ

መጽሐፈ ኢያሱ በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል

1. ምዕራፍ 1፥1-5፥12 የኢያሱ ጥሬና እስራኤላውያን ዮርዳኖስን መሻገራቸው፡፡

በዚህ ክፍል የሚከተሉትን ድርጊቶች እናገኛለን፡፡

ሀ. እግዚአብሔር ከሙሴ ሞት በኋላ በሙሴ ፈንታ ኢያሱን የሕዝቡ መሪ እንዲሆን ጠራው፡፡ ሕዝቡን ዮርዳኖስን እንዲያሻግራቸው፣ ለሕጉም ታማኝና ታዛዥ ቢሆን ሁሉም እንደሚከናወንለት መመሪየ ሰጠው፡፡ ቁጥር 1-9 በቁጥር አንድ ላይ ያለው ቃል መጽሐፍ ኢያሱ ከኦሪት ዘዳግም ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡ የዚህ ክፍል ጠቅላላ አነጋገር ከኦሪት ዘዳግም 11፥22-25 ጋር ይተባበራል፡፡ /ኢያሱ 1፥9/ ከዘዳግም 3፥21 ... ጋር አመዛዝን፡፡

ለ. ምዕ 1፥10፥24 ዮርዳኖስን ለመሻገር የተደረገ ዝግጅት

ኢያሱ፡- ከእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደተቀበለ ወዲያውኑ ስለ ሥራው ዝግጅቱን ቀጠለ፡፡ ሮቤል፣ ጋድና መንፈቀ ነገደ ምናሴ ቀደም ሲል በገቡት ቃል ኪደን መሠረት ለዐሥሩ ነገድ ተኩል እርዳታ እንዲያደርጉ አስታውስ፡፡ /ቁ 12-18/፡፡ ኢያሪኮን ሰልለው እንዲመጡ ሁለቱን ሰብአ ዐይን ላከ፡፡ ሰላዮችም ረዓብ በተባለች ዘማ ተረድተው የስለላ ሥራቸውን አከናውነው ተመለሱ /ም 2፥1-24/

ሐ. ምዕ 3፥1-4፥24 ዮርዳኖስን በተአምር መሻገር

ከቁጥር 1-6 ዮርዳኖስን ለመሻገር የተደረጉ ዝግጅቶችን እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ፡- 1/ ታቦት 2/ በታቦቱና በሕዝቡ መካከል የተደረገው ርቀት 3/ የሕዝቡ ቅድስና ከ7-17 ባሉት ቁጥሮች ሕዝቡ ዮርዳኖስን እንዴት እንደ ተሻገሩ ተገልጦአል፡፡

ምዕራፍ 4፥1-14 ሕዝቡ ዮርዳኖስን እንደተሻገሩ በምዕ 3 የተተረከውን ታሪክ ከልዩ መግለጫ ጋር ያብራራል፡፡ 4፥15-24 ሕዝቡ ዮርዳኖስን ተሻግረው በጌልጌላ ሰፈሩ ለመሻገራቸውም መታሰቢያ ይሆን ዘንድ 12 ድንጋዮችን በዮርዳኖስ አኖሩ፡፡

መ. ምዕራፍ 5፥1-12 በጌልጌለ የተፈጸሙ ድርጊቶች

እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ በጌልጌላ ሰፈሩ፡፡ በጌልጌላ ሳሉም ሀ/ አዲሱ ትውልድ በባልጩት ተገረዘ፣ ለ/ በዚህ ቦታ ለመጀመሪያ ጊዜ በተስፋዋ ሀገር ዳርቻ የፋሲካን በዓል አከበሩ፡፡ ሐ/ በዚህ ቦታ ሳሉ ለ40 ዓመታት ይወርድላቸው የነበረው መና ተመቋርጦ፡፡ መናው የተቋረጠበትም ቦታ ግእዙ “ፊንቆን” ይለዋል፡፡ ዘንባባ ያለበት ቦታ ለማለት ነው፡፡

2. ምዕራፍ 5፥13-12፥24 የከነዓን መያዝ

ሀ. 5፥13-15 የእግዚአብሔር መልአክ ኢያሱን ያጽናናዋል፡፡ ይህ ታሪክ በደብረ ሲና /ኮሬብ/ ለሙሴ የተደረገውን ታሪክ ይመስላል /ዘጸአት 3፥5/

ሀ. የኢያሪኮ ግምብ መውደቅ፣ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ኢያሱ የኢያሪኮን ከተማ ለስድስት ቀናት አስከብቦ፣ በሰባተኛው ቀን ከተማዋ ተያዘች፡፡ ረዓብ ብቻ ከወገኖችዋ ጋር ዳነች፡፡

ይህ ታሪክ በዕብራውያን 11፥30-31 ላይ ተረጋግጦአል፡፡ ኢያሱ ከኢያሪኮ የሚገኘው ምርኮ ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም እንዲሆን ወስኖ ነበር፡፡ /6፥17-20/ ነገር ግን ሕዝቡ ይህን አልጠበቀም፡፡

ለ. ምዕራፍ 7፥1-26 የአካን ስርቆት

እግዚአብሔር በኢያሪኮ ለእስራኤላውያን መሐሪና ረዳኢ የሆነው ያህል በጋይ ደግሞ በአካን ኃጢአት ምክንያት ፈራጅነቱን አስታወቀ፡፡

ሐ. ምዕራፍ 8፥1-35 የጋይ መደምሰስ

ኢያሱ በልዩ የጦር ዘዴና በደብቅ ጦር ሰብአ- ዓይን ለማጥፋት ቻለ፡፡ ሙሴ አማሌቃውያንን ሲያጣሩ እጁን ዘርግቶ እንደዋለ ኢያሱም ሰብአ-ጋይን ፈጽሞ እስኪያጣሩ ድረስ እጁን አላጠፈም፣ ቁጥር 26 እስራኤል የኢያሪኮን ምርኮ ለእግዚአብሔር እርም እንዳደረጉ የጋይን ምርኮ ዳግም ለራሳቸው አደረጉ ቁጥር 27 በመጨረሻ ኢያሱ በደብረ ጌባል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፡፡ መሠዊያውም በዘጸአት 20፥25 የተጠቀሰውን መሠዊያ ይመስላል፡፡

መ. ምዕራፍ 9፥1-27 ሰብአ ገባኦን ኢያሱን ማታለላቸው፡፡

ቁጥር 1 እና 2 ለምዕራፍ ዘጠኝ ዐሥርና አንድ መቅድም ነው፡፡

ሠ. ምዕራፍ 10፥1-43 የደቡብ ከነዓን መያዝ

ኢያሱ በመጀመሪያ አምስቱን ነገሥታት በቤተ ሐሮን ድል አደረገ ቀጥሎም የደቡብ ከተማዎችን ይዞታ አገኘ፡፡

ከ12-14 ያሉት ቁጥሮች በመጽሐፍ ያሻር የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሣ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት የፀሐይ የጨረቃ መቆም ተአምራት ምሳሌያዊ የቅኔ ንግግሮች እንጂ ተአምራትን እንደማያሳዩ የገመቱ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ /የተነገረው/ ያለው ሀሳብ ሁሉ እውነተኛ ተአምርን የሚያመለክት መሆኑ በመጽሐፉ ሲራክ 46-4 ተገልጦአል፡፡

ረ. ምዕራፍ 11፥1-15 የሰሜን ከንዓን መያዝ

ኤዎስ፡- በኢያቤስ የበላይ ሰብሳቢነት የተሰበሰቡ ነገሥታት በማሮን ውኃ አጠገብ ድል አደረገ፡፡ ከተማዎቹንም /የኢያቡስን/ ማረከ፡፡ በመሳፍንት 4፥2 ላይ የተጠቀሰው ኢያቢስ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ራሱ ስም ነው፡፡

ሰ. ምዕራፍ 11፥16-12፥24 የሀገሪቱ /ከንዓን/

ፈጽሞ መያዝና ድል የሆኑት የነገሥታት ዝርዝር

ዝርዝር 11፥16-23 ስለ ውስጥ ወረራ ይገልጣል፡፡ 12፥1-6 በምሥራቅ ዮርዳኖስ በኩል ሙሴ ድል ያደረጋቸውን ነገሥታት በአጭር ይዘረዝራል 12፥7-24 ኢያሱ በፖለስታይን /ከንዓን/ ድል ስላደረጋቸው 31 ነገሥታት ዝርዝር ይናገራል፡፡ ይህ ምዕራፍ ከአንድ እስከ 11 ላሉት ምዕራፎች ማጠቃለያ ነው፡፡

3. ምዕራፍ 13፥23፥34 የሀገሪቱ /የከንዓን/ በዕጣ መከፈል

ሀ. ምዕራፍ 13፥1-7 ገና ያልተያዙ ከተማዎች መኖራቸውንና ለዘጠኙ ነገድ ተኩል ሀገርዋን ለማከፋፈል ለኢያሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትዕዛዝ ይናገራል፡፡ በቊጥር 4-6 ላይ የተጠቀሰችው ሲዶን በኋላ ጢሮስ ዋና እስክትሆን ድረስ የፊኒቂ ዋና ከተማ ነበረች፡፡ በሰሎሞንም ጊዜ እንኳ ዋና እንደነበረች በ1 ነገሥ 5፥6 ተገልጦአል፡፡

ለ. 13፥8-33 ምሥራቃውያን ሁለቱ ነገድ ተኩል /ሮቤል፣ ጋድና መንፈቀ ነገድ/ ምናሴ/ ከዮርዳኖስ ማዶ በስተምሥራቅ ርስታቸውን ተቀበለ፡፡

ሐ. ምዕራፍ 14፥1-19፥51 የምዕራባውያን ነገድ /የዘጠኙ ነው ተኩል/ ሀገሮች፡፡ 14፥1-5 ሀገሮችን በዕጣ እንደተፈለአቸው ይበልጥ መቅድም ነው፡፡ ከቊጥር 6-12 ካሌብ ወልደ ዬፍኒ ማመልከቻ ያቀርባል ኢያሱ ለካሌብ ከብሮንን በርስትነት ይሰጣል ቊጥር 13-15፡፡ ነገደ ይሁዳና ረስታው ምዕራፍ 15፡፡ ነገደ ዮሴፍና ርስታቸው ምዕራፉት 16 እና 17፡፡

ለአርባ ዓመታት በጉዞ ላይ የነበረችው ደብተራ ኦሪት ለመጀመሪያ ጊዜ በተስፋ ሀገር በሴሎ ተተከለች ምዕ 18፥1፡፡

ለሁለተኛው ክፍያ የተደረገ ዝግጅት

18፥2-20 ነገደ ብንያምና ርስታቸውን 18፥11-28፡፡ ነገደ ስምዖንና ርስታቸው ምዕራፍ 19፥1-9፡፡ ነገደ ዛብሎንና ርስታቸው 19፥10-16 ነገደ ይሳኮርና ርስታቸው ቊጥር 17-23፡፡ ነረደ አሴርና ርስታቸው ቊጥር 24-31፡፡ ነገደ ንፍታሌምና ርስታቸው ቊጥር 32-39፡፡ ነገደ ዳንና ርስታቸው ቊጥር 40-48፡፡

እስራኤላውያን የየራሳቸውን ድርሻ ካገኙ ለኢያሱ ወልደ ነቼ በመካከላቸው የምትገኘውን ተምና ሴራ የምትበላውን ከተማ በርስትነት ሰጡት ቊጥር 49-51፡፡

በዚህ ክፍል አንዳንድ ጥንታውያን ምልክቶች ይታያሉ፡፡ በምዕራፍ 15 ውስጥ የከነዓን ከተሞች በጥንት ስሞቻቸው ተጠርተዋል፡፡ ለምሳሌ በቊጥር 9 በአላ፣ በኋላ ቂርያትይ ዓረም ትባላለች፡፡ ቊጥር 49/ ቂርያትስና በኋላ ዳቤር፣ ቊጥር 54 ቂርያት አርባቅ በኋላ ከብሮን ተብላ ተጠርታለች፡፡ በምዕ 9፥10 ከነዓናውያን በጊዜው እንዳሉ ይታያሉ፡፡ ነገር ግን በሰሎሞን ዘመን /1ነገሥ 9፥66/ ፊርያን አጥፍቶአቸዋል በምዕ 18፥16 እና 28 እንደምናየው ኢየሩሳሌም የእስራኤላውያን ዋና ከተማ ገና አልሆነችም ነበር፡፡

መ. ምዕራፍ 20፥1-9 ሀገር /ረ/ ምስካይ/

ሠ. ምዕራፍ 21፥1-45 የካህናትና የሌዋውያን ከተሞች፡፡

ረ. ምዕራፍ 22፥1-55 ሁለት ነገድ ተኩል በገቡት ቃል መሠረት ዘጠኙ ነገድ ተኩል ርስታቸውን እስከሚያገኙ ድረስ ርዳታ አድርገው በኢያሱ ተመርቀው ወደ ርስታቸው ተመለሱ፡፡ በዮርዳኖስም አጠገብ መሠዊያ ሠሩ ነገር ግን ከየነገዱ የተውጣጡ ሰዎች በካህኑ በፊንሐስ መሪነት ሂደው ስለመሰከሩአቸው ከዓመፃቸው ተመለሱ፡፡ የሠሩትንም መሠዊያ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ይህ በመካከላችን ምስክር ነው፣ ሲሉ “ምስክር ብለው ጠሩት” /ቁጥር 34/

4. **ምዕራፍ 23፥1-24፥33 የመጽሐፉ ጠቅላላ መደምደሚያ**

ሀ. ምዕራፍ 23፥1-2 የኢያሱ የመጀመሪያ ንግግር መግቢያ ነው፡፡ ከቁጥር 3-13 ኢያሱ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን ድንቅ ሥራ ሁሉ ያስታውሳቸዋል፡፡ ከቁጥር 14-16 ኢያሱ ለሕዝቡ አጭር ምክር ይሰጣል፡፡

ለ. ምዕራፍ 24፥1-28 ኢያሱ የቃል ኪዳኑን መታደስ በሴኬም ያብራራል፡፡ ከቁጥር 29-33 የኢያሱንና የካህኑን የአልዓዛርን መት ይናገራል፡፡

ማጠቃለያ

- የቀደምት ነቢያት መጀመሪያ መጽሐፍ ኢያሱ ነው፡፡
- በዕብራይስጡ የብሉይ ኪዳን ቀኖና መጽሐፉ ኢያሱ አምስቱ ብሔረ ኦሪትን ተከትሎ ይጻፋል፡፡ ትክክለኛ ቦተውም ይህ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል፡፡
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል (24፡27፡44) ላይ ለይቶ እንደተናገረው ሕግ ወይም ኦሪት የሚባለው በሙሴ ብቻ የተጻፈው ነው፡፡
- መጽሐፉ ኢያሱ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምድረ በዳ አውጥቶ ወደ ተስፋ ሀገር እንዴት እንዳስገባቸው ያሳያል፡፡
- መጥሐፉ ኢያሱ በአራት ዐበይት ክፍሎችይከፈላል፡፡.

የመጽሐፉ ኢያሱ የሙከራ ጥያቄዎች

1. ከነቢያት የመጻሕፍት ቁጥር የሚቆጠሩት የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?
2. የሕግ መጻሕፍት መባል የሚገባቸው አምስቱ በሙሴ የተጻፉት ብቻ ናቸው ያሉ ጸሐፍት እነማን ናቸው?

3. እስራኤል ለመጀመርያ ጊዜ በተስፋዋ ሀገር ዳርቻ የፋሲካን በዓል ያከበሩት የት ነው?
4. ለነቢዩ ኢያሱ እስራኤላውያን የሰጡት ከተማ ማን ትባላለች?
5. ዘጠኙ ነገድ በዮርዳኖስ አጠገብ የሠሩትን መሠዊያ ምን ተብሎ ይጠራል?

መጽሐፈ መሳፍንት

መግቢያ

ውድ በርቀት የምትገኘው ደቀ መዝሙሬ የቀደምት ነቢያት ሁለተኛ የሆነው መጽሐፍ በነቢዩ ኢያሱና በነቢዩ ሳሙኤል መካከል ባለው ዘመን የእስራኤልን ሕዝብ ያስተዳድሩ በነበሩ መሳፍንት ሥም ተሠይሞ ስላለው መጽሐፍ ከዚህ በታች ባለው ርዕስ መሠረት ቀርቦልሃል፡-

- ስለ መጽሐፈ መሳፍንት የሥም አሠያየም፣
- ስለ መጽሐፉ ፀሐፊ፣
- ስለ መጽሐፉ ዓላማ፣
- ስለ መጽሐፉ አከፋፈል ከፊደል ሀ እስከ ፊደል ሐ
- ስለ መሳፍንት ዜና መዋዕል፣በዝርዝር ቀርቦልሃል ተመልከት፣

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

የቀደምት ነቢያት ሁለተኛው መጽሐፍ በኢያሱና በሳሙኤል መካከል ባለው ዘመን የእስራኤልን ሕዝብ ያስተዳድሩ በነበሩት መሳፈንት ተሰይሟል፡፡ በዕብራይስጥ ሾፊትም ይባላል፡፡ ትርጓሜውም መሳፍንት ማለት ነው፡፡ ሾፊት /መሳፍንት/ ፍትሕ/ሚሽፋት/ የሚሰጥ ነው፡፡

ሰብዓው ሊቃናት የዕብራይስጡን ርእስ ቃል በቃል በመተርጐም “ኪሪቱይ” ብለውታል፡፡ በእኛም በግእዙ ትርጉም “መሳፍንት” የሚለው ርእስ የዕብራይስጡ ትክክለኛ ትርጉም ነው፡፡ መስፍን ማለት እንደ ዕብራይስጡ ሾፊት ፈታሔ ወይም ገዢ ማለት ነውና፡፡ እንደዚሁም አባ ሄሮኒሞስ /ጀሮም/ በቡልጋት ትርጉማቸው “ኢዮዲሴስ” የሚል ርእስ ሰጥተውታል፡፡ ይህም መሳፍንት ማለት ነው፡፡ ከነዓናውያን የእስራኤልን ልብ መማረክ ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ ከነዓናውያን የሚያመልኩአቸው በዓልና አሳታሮት የሚባሉ ሁለት አማልክት ነበሩ፡፡ በዓል ወንድ አምላክ ሲሆኑ አስታሮት ሴት አምላክ ነበረች፡፡ በእነዚህ አማልክት ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ አስጸያፊ የብልግና ተግባር ይፈጽም ነበር፡፡ ይህም አስጸያፊ ተግባር የተሞላበት ሥርዓት ቀስ በቀስ የእስራኤልን እምነት መመረዝ ጀመረ፡፡

ከኢያሱ ሞት በኋላ በዘመነ መሳፍንት በሙሴና በኢያሱ ዘመን እንደ ነበረው በእስራኤል ዘንድ አጠቃላይና ቀዋሚ አስተዳደር ወይም ማዕከላም መንግሥት አልነበረም፡፡ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር /21፥25/ ከዚህም ጋር ከእግዚአብሔር በቀር የማያስተባብራቸው ኃይል ሳይኖር በወንድማማችነት ወይም በእያንዳንዱ ነገደ አስራኤል ጎብረት /ኮንፌዴሬሲ ይኖሩ ነበር፡፡ በዘመነ መሳፍንት የነበረው መልክህ መንግሥት ቴዎክራሲ መንግሥተ እግዚአብሔር/ ነበር፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር ራሱ የሕዝቡ መሪ ወይም አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጠላት በተነሳባቸው ጊዜ እግዚአብሔር አንዳንድ የጦር መሪ /መስፍን እያስነሣ በጦርነት ጊዜ ድልን ይሰጣቸውና ነጻነትን ያጐናጽፋቸው ነበር፡፡ ስለዚህም መሳፍንት መድኀኒን /ዋሼይም/ እየተባሉ ይጠሩ ነበር፡፡ /2፥16፣ 10፥1/

እስራኤላውያን በመሳፍንት መሪነት ከጠላቶቻቸው ጥቂት ዕርፍት ካገኙ በኋላ የእግዚአብሔርን ውለታ እየረሱ ወደ አምልኮተ ባዕድ ይመለሱ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ ካህናትና ያስከተለው ቅጣት /ፍርድ/ ለብዙ ጊዜ ተደጋግሞአል፡፡

ጸሐፊው

ሳሙኤል በራስ ስም የተሰየመውን መጽሐፈ መሳፍንት፣ ሩትንም ጻፈ ተብሎ በታልሙድ እንደተነገረው የመጽሐፈ መሳፍንት ፀሐፊ ሳሙኤል ነው፡፡ መጽሐፈ መሳፍንት በጣም ጥንታዊ መጽሐፍ እንደሆነ የሚያመለክት ድርጊት አለ፡፡ በምዕራፍ 1፥21 እንደሚያመለክተው መጽሐፈ መሳፍንት በተጻፈ ጊዜ ኢያቡሳውያን እስከ ዛሬ ድረስ በኢየሩሳሌም ነበሩ፡፡ ስለዚህ መጽሐፉ በ2ኛ ሳሙኤል 5፥6 ከተመዘገበው ታሪክ በፊት የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ በምዕራፍ 1፥29 ፊርያን ለሰሎሞን ከተማዋን ከመስጠቱ በፊት ከነዓናውያን በሬዝር ይኖሩ እንደነበር ተመልክቶአል፡፡ /1ነገሥ 9፥16/ በምዕራፍ 3፥3 ላይ ከጢሮስ ይልቅ ሲዶና የፊኒቄ ዋና ከተማ ነበረች ይላል፡፡ ይህም ከ12ኛው ምዕተ ዓመት ቅልክ በፊት ያለውን ዘመን ያመለክታል፡፡

እንደዚሁም በምዕራፍ 17፥6፣ 18፥1 21፥25 ላይ “በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፡፡” የሚለውን ዐረፍተ ነገር ስንመለከት መጽሐፈ የእስራኤል የዘውድ መንግሥት እንደ ተቋቋመ የተጻፈ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ምናልባትም በሳኦል ዘመነ መንግሥት ወይም በዳዊት ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያም ሆነ በዚህ በሳሙኤል ዘመነ ምስፍና አይወጣም፡፡ ስለዚህም የታልሙድ ምስክርነት ይፀናል፡፡

ዓላማው

መጽሐፈ መሳፍንት፡- ከኢያሱ ሞት በኋላ በእስራኤል መካከል ይታይ የነበረውን የፖለቲካ የማኅበራዊና የሃይማኖት ሁኔታ ይገልጣል፡፡ እስራኤል በድል አድራጊነት ወደ ከንዓን ገብተው በከንዓን ሰፍረው ነበር፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ ከንዓናውያንን ጨርሰው አላጠፉም፡፡ ስለዚህ የቀሩት ከነዓናዊያን የእስራኤል ልብ መማረክ ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ ከነዓናዊያን የማያመልኳቸው በዓልና አስታሮት የሚባሉ ሁለት አማልክት ነበሩ፡፡ በዓል ወንድ አምላክ ሲሆን አስታሮት ሴት አምላክ ነበረች፡፡ በእነዚህ አማልክት ስርዓተ አምልኮ ውስጥ አስፀያፊ የብልግና ተግባር ይፈጸም ነበር፡፡ ይህም አስፀያፊ ተግባር የተሞለበት ሥርዓት ቀስ በቀስ የእስራኤልን እምነተ መሰረዝ ጀመረ፡፡ እስራኤል አንዱን አምላክ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አምልኮተ ባዕድ አዘነበሉ፡፡ እግዚአብሔርም በጦረቤቶቻቸው በከነዓናዊያን ይቀጣቸው ጀመረ፡፡ ከኢያሱ ሞት በኋላ በዘመነ መሳፍንት በሙሴና በኢያሱ ዘመን እንደነበረው በእስራኤል ዘንድ አጠቃላይና ቀዋሚ አስተዳደር ወይም ማዕከላዊ መንግሥት መሳፍንት በአንድ በኩል የጣር መሪዎች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝብ አስተዳዳሪዎችንና ዳኞች ነበሩ፡፡ የአንዳንዶች አስተዳደር መላው እስራኤልን አያጠቃልልም ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ መስፍን በላይ በእስራኤል ላይ የሚገኙበት ዘመን ነበር፡፡ የመሳፍንት ምስፍና ከራስ ወደ ልጅ በውርስ አይተላለፍም ነበር፡፡ ዕብራዊ ሹፊት /መስፍን/ ከገዥ የተለየ ነው፡፡ እንደ ነቢይ የእግዚአብሔር ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህመ መሠረት በሶምሶን ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ይገዙ ነበር፡፡ ግን እስራኤላውያን የራሳቸው መስፍን ነበራቸው /14፥4/፡፡

መጽሐፈ መሳፍንት በአጠቃላይ፡- እስራኤል ከእግዚአብሔር ሥልጣን በታች ሆኖ የሚያስተዳድር አንደ እውነተኛ ንጉሥ ይፈልጉ እንደነበር ያሳያል፡፡ /ምዕ 1፥1-2፣ 20፥18/ በተጨማሪም ለእግዚአብሔር መታዘዝ እርሱንም ማመን ሕይወት ሰላም ሲሆን አለመታዘዝ ግን ውጤቱ በጠላት እጅ መውደቅ እና ሞት መሆኑን ያስረዳል፡፡

አከፋፈሉ

መፍሐፈ መሳፍንት በ3 ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል

ሀ. ምዕራፍ 1፥1-2፥5 መግቢያ

1. 1፥1 ጠቅላላ የመጽሐፉ መግቢያ ነው

ይህ ቍጥር አንዳንድ ተቃዋምያን ለሚያቀርቡት አስተያየት እንደ አጥር ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ክፍል /1፥1-2፥23/ ከኢያሱ ሞት ታሪክ ጋር የሚቀጥል /የሚከተል/

ሳይሆን ከኢያሱ ታሪክ ጋር ትክክል ነው። የሚል አስተሳሰብ አለና ነው። ስለዚህ ይህ ቍጥር የአንድ ሌላ አዘጋጅ ዝግጅት እንጂ በኢያሱ የታሪክ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ይህ ቍጥር ልክ እንደ መጽሐፈ ኢያሱ ይጀምራል /ኢያ 1፥1/ ከኢያሱ ሞት በኋላ ያለውን ታሪክ በግልጥ የስቀምጣል እነዚህም ድርጊቶች ከኢያሱ ታሪክ ጋር የለ መግቻ እኩል በእኩል የሚሄድ ሳይሆን የቀጠሉ ናቸው።

2. <u>1፥2-36 በጊዜ የነበረ የፖለቲካ ሁኔታ አስተዋጽኦ</u>

ይህ ክፍል የያዘውን የነገደ እስራኤልን ተግባር ያጸናል እንደ መጽሐፈ ኢያሱ የኢያሱን ታላቅ መሪነት አይዘረዝርም። በምዕራፍ 1፥10 ላይ ይሁዳ የካሌብ ምትክ /ተለዋጭ/ ነው። ተብሎአል /ኢያ 15፥13-19/ ግን አይጠላም። ካሌብ በይሁዳ መካከል አንድ ክፍል ተቀብሎአል። ኬብሮንን ለመዋጋት መሪነቱን ለምን አልወሰደም አዎ ይሁዳ ካሌብን ወክሎ ኬብሮንን ወግቶአል። በምዕራፍ 1፥21 ላይ ብንያም ለይሁዳ ምትክ እንደሆነ ተነግሮአል። /ኢያ 15፥63/ አሁንም ይህ ሊጠላ አይችልም። ያለ ጥርጥር ሁለቱም ነገድ ኢየሩሳሌምን ተቃውመዋልና። ሆኖም ያን ጊዜ ኢያቡሳውያንን ለማስወጣት አልቻሉም። ነገር ግን በኋላ ከተማዋ በይሁዳና በብንያም መካከል ተከፍላለች።

ምዕ 1፥8 ይሁዳ ኢየሩሳሌምን እንደያዛት ይናገራል። ይህም ከ1፥21 ጋር ሲነጻጸር ትክክል አይመስልም። ኢየሩሳሌም ለመጀመሪያ ጊዜ የተያዘች በዳዊት ዘመን ነውና ይሁን እንጂ ይህ ነገር 1፥7 በአደኒቤዜቅ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ጊዜ ይሁዳ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ጥሎአል በእሳትም አቃጥሎአታል። ነገር ግን በቀዋሚነት አልያዙአትም። 1፥21 እንደሚያመለክተው፡- ኢያቡሳውያንን አላስወጡአቸውም። ስለዚህ 1፥8 ኢያሱ ሳውያንን ለማስወጣትና ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የነበራቸው ሙከራ ያሳያል። እንደ ገና 1፥18 እና 1፥19 የሚላሉ ይመስላሉ። ግን አይጣሉም። 1፥18 የፍልስኤምን ዳርቻ ምርኮ ይናገራል። ይህም ያለ ጥርጥር ወቅታዊ ነበር።

ምዕራፍ 1 ከኋለኞች የመጽሐፍ ክፍሎች ጋር የሥነ ጽሑፍ አንድነት ድርጊቶችን ያሳያሉ።

1. በአንድ እጅ አሳልፎ መስጠት 1፥2፣ 2፥14-23፣ 6፥1፣ 7፥7፣ 13፥1፣ 15፥12፣ 28፥10፣ 20፥28
2. በእሳት መቃጠል 1፥8።
3. በሰጥፍ ስለት መቍረጥ 1፥8፣25፣ 20፥48

4. እስከ ዛሬ ድረስ 1፥21፣ 6፥24፣ 15፥19፣ 10፥4
5. *መቀመጥን ማጽናት /መፍቀድ/* 1፥20-35፣ 17፥11፣ 19፥6፣ ምዕራፍ 1፥1-2 ከምዕራፍ 20፥18፣ 23፥27 *ጋር* እንዲሁም 1፥16 ከምዕራፍ 4፥11 *ጋር* መነጻጸር ይገባዋል፡፡

3. **2፥1-5 በመልአክ እግዚአብሔር ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር የነበቸውን ኪዳን በፍረሳቸው ይገሠጻሉ፡፡**

ለ. ምዕራፍ 2፥6 16፥31 *መሳፍንተ* እስራኤል

1. **2፥6፣ 3፥6 የእስራኤላውያን ግንኙነት** ከእግዚአብሔር ጋር ምን ያህል እንደነበር በዚህ ክፍል እንመለከታለን፡፡ ኢያሱ በመጨረሻ ጊዜ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ብቻ መከተል እንዳለባቸው ቃል አስገብቶአቸው ነበር፡- ነገር ግን ኢያሱ ከሞተ በኋላ ያላቸውን አክብረው አልተገኙም፡፡ የከነዓንን አማልክት በኖልንና አስታሮትን የሚከተል፣ እግዚአብሔርን የማያውቅ፣ ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ የዘነጋ አዲስ ትውልድ ተነሣ፡፡ /2፥10-12/ እግዚአብሔርም እስራኤል እርሱን ስለተውት በጠላቶቻቸው ድል አንዲሆኑ አደረገ /2፥14/ ይሁን እንጂ በፈታሒዊነቱ ሲፈረድባቸው በመሐሪነቱ ከጠላቶቻቸው የሚያድኑአቸው *መሳፍንትን* አስነሣላቸው፡፡ /2፥16/ ነገር ግን መስፍኑ በሞተ ጊዜ እንደገና እግዚአብሔርን ትተው ወደ ጣዖት ይሄዱ ነበር /2፥19/ ስለዚህም እግዚአብሔር እስራኤልን ይፈተንባቸው ዘንድ በእያሱ ጊዜ የቀሩትን አህዛብ በከነዓን እንዲኖሩ አደረገ /2፥22/ እነዚህም አሕዛብ በምዕራፍ 3፥1-6 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡

አሕዛብ ከከነዓን ፈጽመው እንዳይወጡ ስለመደረጉ በምዕራፍ 3፥1-3 ላይ የተሰጠው ምክንያት እስራኤላውያን የጦርነት ስልት እንዲማሩባቸው ነው ይላል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ 2፥22 እና በ3፥4 እስራኤል በሞራል እንዲፈተኑ ነው ይላል፡፡ ይህም አከራካሪ /የሚጠላ/ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ጦርነት እንዲደሩባቸው ማለት ከከነዓናውያን ጋር ጦርነት ባደረጉ ጊዜ እግዚአብሔር ረዳታቸው መሆኑን እንዲያውቁ አሕዛብን ፈጽሞ አላጠፋቸውም ማለት ነውና፡፡ የዚህም መሠረተ ሀሳብ የሞራል ፈተናን ያሳያል፡፡

በምዕራፍ 3፥3 ላይ የተዘረዘሩት አሕዛብ በ3፥5 ላይ ከተጠቀሱት ወገኖች ጋር ተመሳሳይ አይደሉም፡፡ የመጀመሪያዎቹ አንዳንድ ወረዳዎችን የያዙትን ሳያመለክቱ የኋለኞቹ ጠቅላላ ሕዝቡን /የከነዓንን/ ይወክላሉ፡፡ ግን በ3፥3 ላይ የተመለከቱት በኢያሱ 13፥2-6 ከተመዘገቡት አሕዛብ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

2. 3፥7-11 **የኢትኒኤል ምስፍና ይህ መስፍን** በግእዙና በአማርኛው ትርጉም ጎቶንያል ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም ስያሜ ከሰብአጌንታ /ሰብዓ ሊቃናት/ የተወሰደ ነው፡፡ የዕብራይስጡን ግን "አትኒኤል" ነው፡፡ የአባ ሮሜ /አብርሃም/ ትርጉም የዕብራይስጡን ይከተላል፡፡ የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል አስራኤልን ከመስፖታሚያ ንጉሥ ከኩሰርስቴም/ ኩሽንሪሻታይም/ አዳናቸው፡፡ በእርሱ ምስፍና ለአርባ ዓመታት ዕረፍት አገኙ፡፡

3. 3፥12-30 **የብንያማዊው ናያድ ምስፍና**

ስሙ በዕብራይስጥ ኢሁድ ነው፡፡ የአባሮሜ /አብርሃም/ ትርጉምም የዕብራይስጡን ይከተላሉ፡፡ ናያድ ግራኝ ነበር፡፡ በሞዓብ ንጉሥ በአግሎን ለ18 ዓመታት ተጨቁነው ከተገዙ በኋላ እግዚአብሔር ናያድን አስነሣላቸው፡፡ /3፥14-15/ ከድል በኋላ እስራኤል በናያድ አመራር ለ80 ዓመታት በሰላም ኖሩ፡፡ /3፥30/፡፡ በናያድና በጎቶንያል ዘመን ምስፍና እስራኤላውያን ሁሉ በጨቋኞች ጠላቶቻቸው ላይ በርትተው ነበር፡፡

4. 4፥31፣ **ሰሜጋር ወልደ እናት ሸምጋር /ስሜ ጋር/** በበሬ በውጊያ ስድስት መቶ ፍልስጥኤማውያንን ገድሏል፡፡ ስሜጋር እንደ መስፍን አልተጠራም፡፡ ዘመነ ምስፍናውም በዜና መዋዕል አልተገለጠም፡፡

5. 4፥1፣ 5፥31 **እስራኤል በኢያሱ መጠቃታቸው መጨቆናቸው፣** በዲቦራና በባርቅ ነጻ መውጣታቸው፡- ኢያቡሽ የግሪክ ፎርም ሲሆን የዕብራይስጡ ያሲን ነው፡፡ አባ አብርሃምም ይህን የዕብራይስጡን ያጸድቃሉ፡፡ የሴሳራ የሠራዊት አለቃ መሆንና የእስራኤል ድል አድራጊነት በቅኔ መልክ ተገልጦአል /ምዕራፍ 5/

ቅኔው ወይም መዝሙሩ በጣም ጥንታዊነት ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ኩፋሌ እንደሆነ ሊቃውንት ገምተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አስተያየት ልክ አይመስልም፡፡ በታሪኩ ይዘት የራስዋ የዲቦራ ወቅታዊ ተግባር ነው፡፡ እርግጥ መጽሐፈ መሳፍንትን በሙሉ ያዘጋጀ ሰው አንዳንድ ሀሳብ ሳይጨምርበት እንዳልቀረ ይታመናል፡፡

በቅልህ ጦርነር ውስጥ ነገደ አስራኤል በሙሉ አልተካፈሉም፡፡ ሮቤል፣ ገልዓድ፣ ዳንና አሴር በጦርነት አልገቡም፡፡

ምዕራፍ አራት ከምዕራፍ አምስት በአንዳንድ አስፈላጊ ዝርዝሮች ይለያል፡፡

1. በጦርነቱ የገጠሙ በምዕራፍ አራት ሁለት ሲሆኑ በምዕራፍ አምስት 6 ናቸው፡፡ /4፥10ን ከ5፥14-15፣ 18 ጋር አነጻጸር / ነገር ግን እነዚህ የተለያዩ የታሪክ መዝገቦች አይደሉም፡፡ 4፥10 በቀላሉ የባርቅን የመጀመሪያ ተግባር ይናገራል፡፡ ምዕራፍ 5 ቅኔ ሲሆን ሌሎችን ነገዶች በተለመደው የቅኔ አቀራረብ ይጠቅሳል፡፡

ምዕራፍ 4፥23-24 ድሉን በሁለቱ ነገዶች ሳይሆን ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ይሰጣል፡፡

2. ሲሶራ ተኝቶ ሳለ በኢያኤል እንደተወጋ ምዕራፍ 4፥21 ይገልጣል፡፡ ምዕራፍ 5 ግን ሲሰራ ከድንኳኑ ወጭ እርጉ ሲጠጣ ራሱን እንደተመታ ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱ የታሪክ ዘገባዎች መካከል ግጭት እንደሌለ ይታወቃል፡፡ ምክንየቱም በቅኔ መልክ የቀረበው /ምዕራፍ 5/ ዝርዝሩን ሁሉ ለመስጠት አይፈልግም፡፡ ነገር ግን የሲሳራን ነገረ ሞት ብቻ በአጭሩ በቅኔ መልክ ይገልጣል፡፡ /5፥27/፡፡
3. ምዕራፍ 4 ስለ ንጉሥ ኢያቢስ /የኢያቤስን ንጉሥነት/ ይናገራል፡፡ ምዕራፍ 5፥19 ሲሳራ ጋር ነገሥተ ከነዓን እንደነበሩ ይጠቀሳል፡፡ የኢያቤስ ንጉሥነት /አለቅነት/ ግን አይጠቀስም፡፡ አሁንም ምዕራፍ 5፥9 ቅኔ መሆኑን አንዘንጋ ስለዚህ ነገሥት የሚለው ቃል በቀላሉ ከኢያቤስ በታች ያሉትን የጦር መሪዎችን አለቆችን/ ሁሉ ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ምዕራፍ 5 ሲሳራ የነገሥታት አለቃ /ንጉሠ ነገሥት/ ነው አይልም፡፡ የኢያቤስ ጄኔራል ሆኖ ይመራ እንደነበር በምዕራፍ 4 እና 5 ላይ ተነግሮአል፡፡
4. አንዳንድ ሊቃውንት ዲቦራ ታሪካዊት ሴት መሆኗን ይክዳሉ፡፡ በምዕራፍ 5፥7 ላይም “የእስራኤል እናት” የሚለው ቃል አጠቃላይ አነጋጋር እንጂ አንድ ግለሰብን አያመለክትም ይላሉ፡፡ ሆኖም በዘፍጥረት 35፥8 ዲቦራ የሚለው ቃል በግልጥ ታሪካዊ ሰውን ያሳያል፡፡ ምዕራፍ 4 በምዕራፍ 5 የሌሉትን አንዳንድ ዝርዝሮችን ይጨምራል፡፡ ይህም በምዕራፍ 5 ያለውን መዝሙር ወይም ቅኔ ለማስተዋል ይረዳል፡፡
5. ከ1 እስከ 5 ያሉ ምዕራፎች ስለ ዓመጸኞች ሕዝቦች ያለውን የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሕዝቡ በቦኪም በመልአክ እግዚአብሔር ተወቀሱ /2፥1-5/ ስለዚህም እንዲህ ተባለ “ከነዓናውያን” በአጠገባችሁ እሾህ ይሆንባችኋል፣ አማልክቶቻቸውም ወጥመድ ይሆንባችኋል፡፡ /2-3/፡፡
6. 6፥1-8፥35 የጌዴዎን ምስፍና

   ጌዴዎን የሩበዓል ይባላል፡፡ በዘመኑ እስራኤልን ይጨቁኑ የነበሩ ምድያማውያን በእርሱ ድል ሆነዋል፡፡ ጌዴዎን ወደ ምድያም ከመዝመቱ አስቀድሞ ድል እንደሚያደርግ በመልአክ እግዚአብሔር ተነግሮታል፡፡ ቃል ኪዳንም ተሰጥቶታል /6፥11-40/

7. 9፥1-57 ተከታዩ የአቤሜሌክ ታሪክ በዚህ ክፍል በጣም ጥሩ የሆኑ ያልተለመደ ምሳሌ ይገኛል፡፡
8. 10፥1-5 ቶለና ኢያኤር 23 እና 22 ዓመት መሳፍንት ሆነው በክብር እስራኤልን አገልግለዋል፡፡

የምዕራፍ 6-10፥5 አመሠራረት /አቅዋም/ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር እንደገና ሕዝቡን በነቢይ ማዕከላዊነት ይገሥጻል፡፡ /6፥7-10/ እስራኤል ለ7 ዓመታት ከተጨቆኑ በኋላ ለአርባ ዓመታት በጌዴዎን ዕረፍት አግኝተዋል /6፥1፣ 8፥28/ ቤቶላና በኢያኤር አርባ አምስት የሰላም ዓመታትን አይተዋል /10፥1-3/ ይህ ዘመን የውስጥ ረብሻና አለመተባበር የተሞላበት ነበር፡፡ የኤፍሬም ልጆች በጌዴዎንና በድል አድራጊዎች ነገዶች ላይ በከፍተኛ ቅናት ተነሳስተው ነበር፡፡ ሦኮትና ጵኒኤል ርዳታ ለማድረግ ፈቃደኞተ አልነበሩም /8፥4-9፣ 14-17/

ከጠላት ጋር ጦርነት ለማድረግ እንዳይወጡ የከለከሉ እስራኤል ሁሉ ብቻ አይደሉም፡፡ ከጌዴዎን የውስጥ ሠራዊትም ሁሉም ለጦርነት እንዲወጡ አልተፈቀደላቸውም፡፡ እግዚአብሔር በ300 ሰዎች እጅ ብቻ ድልን አጐናጽፎአቸዋል፡፡ ይህም “እስራኤል እንጂ አዳኝ ነኝ ብሎ እንዳይታበይ” ነው /7፥2/፡፡

9. 10፥6፣ 12፥7 በዮፍታሔ የተገኘው ነጻነት

የጋለሞታዋ ልጅ ዮፍታሔ መሪ እንዲሆናቸው በገልዓድ መሪዎች ተጋበዘ፡፡ ድል ያደረገ እንደሆነ በመሪነቱ እንዲቀጥል ስምምነት ነበር፡፡ ዮፍታሔም ድል ያደረገ እንደሆነ መጀመሪያ ሊገናኘው ከቤቱ የወጣውን እንደሚሠዋ ለእግዚአብሔር ተሣለ፡፡ ዮፍታሔ የተሣለ ሴት ልጅን እንደሆነ በውጤቱ ተዋቋል፡፡ ለዘለዓለማዊ ድንግልና ተሥሎአት ይሆናልና፡፡ ነገር ግን ይህ እርግጠኛ መሆኑ አይታወቅም፡፡

10.12፥8-15 ሦስቱ መሳፍንት ኢብፃን፣ ኢሉምና ዐቢደን፡፡ ሰባት፣ ዐሥርና ስምንት ዓመታት በክብር ገዝተዋል፡፡

11.13፥1-16፣ 31 የሳምሶን ታሪክ በመሳፍንት ላይ የተገለጠው መለኮታዊ ኃይል ናዝራዊ በመሆን ይህን ኃይል ባገኘው በሳምሶን ተፈጽሞአል፡፡ ሳምሶን በፍጥረታዊ ጠባይው ፍጹም ደካማ ሰው ነበር፡፡

ከ10 እስከ 16፥31 ያሉ ምዕራፎች አመራረት /አቅዋም/ እንደሚከተለው ነው፡፡ ሕዝቡ አሁንም እንደገና በጌታ ይገሠጻሉ /ይወቀሳሉ1 /10፥13-14/ የውስጥ ድክመት በጣም ግልጽ

ሆኖ ይታይ ነበር። ስለዚህም ዮፍታሔ በገልዋድ ገሾዎች ተጠራ። ሳምሶን ከእናቱ ማሕፀን ተለየ።

ሐ. ምዕራፍ 17፥1፣ 21፥25 ሁለት ተጨማሪ ታሪኮች

1. 17፥1-18፥31 የኤፍሬማዊው የሚካና በቤቱ ውስጥ በካህንነት የተቀጠረው የአንድ ሌዋዊ ታሪክ እነዚህ ሁለት ተከታታይ ታሪኮች በዚህ ዘመን የንጉሥ ተፈላጊነትን በግልጽ ያሳያሉ።
2. 19፥1-21፥25 በብንያማውያን ላይ በገባያን የተፈጸመውን ድርጊት የሚተርክ ክፍል ነው።

የመሳፍንት ዜና መዋዕል

1. ዘመነ መሳፍንት በመጽሐፈ መሳፍንት በተመዘገበው መሠረት 410 ይሆናል። ይህም እንደሚከተለው ነው።
    1. እስራኤል በመሳፍንት አሕዛብ ተሠቍነው የተገዙበት ዘመን 111 ይሆናል። ይህንም ኋላ በቦታው እንመለከታለን።
    2. መሳፍንተ እስራኤል በሰላምና በዕረፍት እስራኤልን ያስተዳደሩበት 299 ነው። የዚህንም ዝርዝር በኋላ እናያለን። 111 በ299 ጋር ሲደመር 410 ይሆናል። ይኸውም ከጐቶንያል እስከ ሳምሶን ያለው ዘመን ነው።

በመዘነ መሳፍንት ፍጻሜ አካባቢ የነበረው መስፍን ዮፍታሔ እስከ እርሱ ድረስ ያለው ዘመነ መሳፍንት 300 ዓመት መሆኑን ይናገራል። /መሳፍንት 11፥26/ ይኸውም 1400-110 ቅልክ ያለው ዘመን ነው። ከጸአተ ግብጽ እስከ ሰሎሞን አራተኛ ዓመት መንግሥት ድረስ 480 ዓመት እንደሆነ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 6፥1 ተመልክቶአል። ከዚህ በላይ የሳኦልና የዳዊት ዘመነ መንግሥት 80 ዓመት ሲቀነስ አራት መቶው ዓመት የመሳፍንትን ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው።

ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 13፥20 ላይ "እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ድረስ ለአራት መቶ ሃምሳ ዓመት መሳፈንትን ሾመላቸው" በማለት ጽፎአል። በዚህ መሠረት ዘመነ መሳፍንት 450 ዓመት እንደሆነ እናያለን። የዚህም አቆጣጠር እንደሚከተለው ነው። የመሳፍንተ አሕዛብ 111፤ የመሳፍንተ እስራኤል 299 ሲደመር 410 ይሆናል። የኤሊ ዘመን መስፍና 40 ዓመት ነው፤ ይህ ከ410 ሲደመር 450 ይሆናል። እንግዲህ በዚህም ሆነ በዚህ ዘመነ መሳፍንት በ400 ክልል ውስጥ መሆኑ ተረጋግጦአል።

2. ዘመነ መሳፍንት ዜና መዋዕል ዝርዝር

በዜና መዋዕል ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው በአብዛኛዎቹ መሳፈንት እስራኤል አንጻር መሳፍንተ አሕዛብ ይታያል። የጥቂቶቹ መሳፍንተ እስራኤል አንጻር ግን ባዶ ነው። ይህም በዘመናቸው ጠላት መኖሩንና አለመኖሩን ያመለክታል ከዚህም የተነሣ የአይሁድ መምህራን መሳፈንትን በሁለት ከፍለው ዐበይትና ደቂቀ መሳፍንት በማለት ይጠሩአቸዋል።

	መሳፍንተ እስራኤል	ዘመኑ	ነገዱ	መሳፍንተ አሕዛብ	ዘመኑ	ምዕ.ቁ.
	አትኒኤል /ጎቶንያል/	40	ይሁዳ	ኩስርስተም	8	3፥7-11
	ናየድ /ኤሁድ/	80	ብንያም	መሰጸጠማውያን ኤግሎማ፣ ሞዓባውያን፣ አማሌቃውያን አሞናውያን	8	
	ሰሜጋር		ብንያም	ፍልስጥኤማውያን		3፥12-30
	ዲቦራና ባርቅ	40	ኤፍሬም ንፍታሌም	ኢያቢሳ፣ ከነዓናውያን	20	3፥31
	ግዴዎን /ይሩበዓል/	40	ምናሴ	አማሊቃውያን	7	6፥1-8፥35
	አቤሜሌክ	3	ምዕ.ምናሴ		3	1-57
	ቶላ	23	ይሳኮር			10፥1-2
	ኢያኤር	22	ምሥራ.ምናሴ			10፥1-2
	ዮፍታሔ	6	ምሥራ.ምናሴ	አሞናውያን	18	10፥6-12፥7
	ኢብፃን	7	በቤተልሔም ይሁዳ			12፥8-10
	ኤሎም	10	ዘብሎን			12፥11-12
	አብዶን	8	ኤፍሬም			12፥13-15
	ሳምሶን	20	ዳን	ፍልስጥኤማውያን		13፥1-16፥31

ዐበይት መሳፍንት

1. ግዶኒያል
2. ናየድ
3. ዲቦራና ባርቅ
4. ጌዴዎን
5. ዮፍታሔ
6. ሰሜጋር ናቸው።

ደቂቀ መሳፍንት

1. ቶላ
2. ያኢር
3. አብፃን
4. ዓለን
5. አብዶን ናቸው

ዐበይት መባላቸው በመዘናቸው በእስራኤላውያን ላይ የተነሡትን መሳፍንት /ነገሥት/ አሕዛብ ድል አድርገው እስራኤልን በሰላመና በዕረፍት ስለ አስተዳደሩ ነው። ደቂቀ መባላቸውም በዘመናቸው ጠላት ተነሥቶ ተጠግተው በድል አድራጊነት ኃይላቸውን ባለማሳየታቸው ነው። አቤሜሌክ ግን ከደቂቅም ከዐበይትም ሳይሆን ለብቻው ነው። የዘመነ መንግሥቱ ጊዜው ሳይደርስ ንጉሥ ነኝ ብሎአልና ከዚህም ሌላ ያደረገው ጦርነት ከሕዝብ ጋር ሳይሆን ከወንድሞቹ ጋር ነውና።

ማጠቃለያ

- በግእዙ ትርጉም መሳፍንት የሚለው ርእሰ የዕብራይስጡ ትክክለኛ ትርጉም ነው፡፡
- በዘመነ መሳፍንት የነበረው መልክዐ መንግሥት (ቴዎክራሲ) መንግሥተ እግዚአብሔር ነበር፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር ራሱ የሕዝቡ መሪ ወይም አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡
- መጽሐፈ መሳፍንት በአጠቃላይ እስራኤል ከእግዚአብሔር ሥልጣን በታች ሆኖ የሚያስተዳድር አንድ እውነተኛ ንጉሥ ይፈልጉ እንደነበር ያሳያል፡፡

የመጽሐፈ መሳፍንት የሙከራ ጥያቄዎች

1.

መጻሕፍተ ሳሙኤል

መግቢያ

ውድ በርቀት ያለኸው ደቀ መዝሙሬ አሁን ደግሞ ንጉሠ መዓት ሳያልንና ቅዱስ ዳዊትን ቀብቶ ባነገሠው ነቢዮ ሳሙኤል ሥም ስለተሰየሙት ሳሙኤል ቀዳማዊና ሳሙኤል ካልዕ መጽሐፍ በውስጡ ስለያዛቸ ጥልቅ ታሪኮችና ምሥጢራት በዝርዝር በሚከተለው መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧልና ተመልከት፡-

- ስለ መጽሐፈ ሳሙኤል ሥምና ሥያሜ፣
- ስለ መጽሐፉ ፀሐፊ፣
- ስለ መጽሐፉ ዓላማ፣
  - በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣
  - በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣
- ስለ መጽሐፍቱ አከፋፈል
- መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ከሀ እስከ ሐ ድረስ፣
- መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ከሀ እስከ መ ደረስ፣

ቀርቦልሃል ተመልከተው፡፡

መልካም ንባብ!

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ በሳሙኤል ተሰይመዋል ይህም ሊሆን የቻለው ሳሙኤል በመጀመሪያ ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ 24 የታሪኩ ዋና ባለቤት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ በመጻሕፍት ውስጥ ባለታሪኮች የሆኑትን ሳኦልንና ዳዊትን ቀብቶ ስለ አነገሠም ነው፡፡

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠሩ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በአይሁድ ዘንድ አንድ መጽሐፍ ናቸው፡፡ ሰብዓ ሊቃናት ግን ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ በተረጐሙ ጊዜ አንድ የነበረውን መጽሐፍ ሳሙአል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕን ሁለት መጻሕፍት አድርገው ከፈሉት አለ፡፡ ሄሮሚሞስም /ጀሮም ቡልጌት የተባለውን ትርጉም ባዘጋጀ ጊዜ የሰብዓው ሊቃናትን አከፋፈል ተከትለዋል፡፡

ሰብዓ ሊቃናት እነዚህ ሁለት መጻሕፍት አንደኛና ሁለተኛ መጻሕፍተ መንግሥታት /በብሉይ ባሴልዎን/ በማለት ሲጠሩአቸው ከሳሙኤል ቀጥሎ ያሉትን መጻሕፍተ ነገሥት ቀዳማዊና ካልእን ሦስተኛና አራተኛ መጻሕፍተ መንግሥታት በማለት ሰይመዋቸዋል፡፡ የቡልጋት ተርጓሚ ደግሞ መጽሐፈ መንግሥት በማለት ፈንታ መጽሐፈ ነገሥት ብለው ለርእሱ ጥቂት ለውጥ አድርገዋል፡፡

የግእዙ ብሉይ ኪዳንም ከሳሙኤል እስከ መጨረሻው መጽሐፈ ነገሥት ድረስ ቀዳማዊ ካልዕ ሣልስና ራብዕ መጽሐፈ ነገሥት በማለት ስለሚዘረዝር ከሰብዓው ለሊቃናት ትርጉም ጋር ይስማማል፡፡ ፍትሕ መንፈሳዊም በአንቀጽ ሁለት “አርባዕቱ መጻሕፍተ ነገሥት በማለት የሰብዓ ሊቃናትን ሀሳብ ያጸናል እንደገናም ይኸው ፍትሕ መንፈሳዊ “መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ወካልእ አሐዱ መጽሐፍ” ስለሚል ከዕብራይስጡ የብሉይ ኪደን ቀኖና ጋር ይገናኛል፡፡

ጸሐፊው

በአይሁድ ትውፊት መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕን ራሱ ነቢዩ ሳሙኤል እንደ ጻፋቸው እምነት አለ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሐሳብ ብዙ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በአንደኛው ሳሙኤል 25፥1 ላይ ስንመለከት ሳሙኤል መሞቱን እናገኛለን፡፡ ይህ ከሆነ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ የተፈጸመውን ድርጊት ሁሉ ሳሙኤል እንደጻፈው ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ለምሳሌ 1ሳሙ 28፥3 ላይ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ የተፈጸመ ታሪክ እናያለን፡፡ እንደዚሁም 1ሳሙኤል 27፥6 ማቅላል እስከ ዛሬ ድረስ ለይሁዳ ነገሥታት ሆነች የሚለውን ታሪክ ስናነብ ከመንግሥት መካፈል በኋላ የተፈጸመ ታሪክ መሆኑን እንረዳለን በዚህ ጊዜ ይህን ሁሉ ሳሙኤል የፃፈው በማለት ማመን ስለማይችል ከእርሱ ቀጥሎ የተነሡ ነቢያት የሳሙኤልን ጅምር ፈጸሙት ቢባል ትክክለኛ አስተያየት መሆኑን ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ያምናሉ የቤተ ክርስቲያናችንም ሊቃውንት በዚህ ይስማማሉ፡፡ ይልቁንም በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ መጨረሻ ላይ ለመጽሐፈ ሳሙኤል “ቀዳማዊ ወጠና ሳሙኤል ወፈጸምዎ ናታን ወጋድ” … “መጀመሪያውን መጽሐፈ ሳሙኤል ሳሙኤል ጀመረው ናታንና ጋድም ፈጸሙት” የሚል፣ ዘርእ ጨምረው በመተርጐም ሳሙኤል መጀመሩን ናታንና ጋድም መፈጸማቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ እንደዚሁም መጽሐፈ ሳሙኤል ካለእን ሲደመድሙ “ተፈጸመ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ ዘጸሐፍዎ ናታን ወጋድ” … ናታንና ጋድ የጻፉት መጽሐፈ ሳሙኤል

ካልእ ተፈጸመ የሚለውን ዘርእ እንደ አብነት አድርገው ይጨምራሉ፡፡ በዚህም የመጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ ጸሐፊ ናታንና ጋድ ለመሆናቸው ያላቸውን እምነት ይገልጣሉ፡፡

የመጻሕፍቱ ዓላማ

1. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ መጀመሪያው ክፍል የዘመነ መሳፍንትን መደምደሚያ ታሪክ ይሰጣል፡፡ ለአርባ ዓመታት በክህነትና በምስፍና ያገለገለውን የኤሊን ታሪክ፣ እንደዚሁም በእስራኤል መካከል ነቢይና /3፥20/ መሳፍንት /7፥6፥15-17/ ሆኖ ያስተዳደረውን የሳሙኤልን ታሪክ ይጨምራልና፡፡ በተለይም ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ ከሞራል ውድቀት በጠላት ድል ከመነሳት ለማዳን የደረገውን ጥረት ይገልጣል፡፡

ቀሪው ክፍል ደግሞ በሕዝብ ጥያቄ መሠረት አንድ መንግሥት /ሞናርኬ/ መቋቋሙን፣ የሳኦልን ቅብዐ መንግሥት መቀባት ግዛት፣ መውደቅና መት ይተርካል፡፡ ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ አንድ መንግሥት በማቋቋሙ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በሁለት ክፍላተ ዘመናት መካከል መገናኛ ወይም የዘመነ መሳፍንት ፍጻሜ የዘመነ ነገሥት ጅማሬ እየተባለ ይጠራል፡፡

በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የነቢያት ትምህርት ቤቶች መመሥረታቸውን እናገኛለን፡፡ ትምህርት ቤቶችን የመሠረታቸው ሳሙኤል ነው የሚል እምነት አለ፡፡ የተመሠረቱትም የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ለማደስ ነበር፡፡ ትምህርት ቤቶቹ ስለ መንፈሳዊ መዝሙር /ዜማ/ ስለ ቅኔ ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡ 1ኛ ሳሙ 10፥5-10፣ 19፥18-20፡፡

2. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ፡- ዳዊት በመጀመሪያ በይሁዳ ነገድ ላይ ለሰባት ዓመታት ከዚያም በኋላ በመላው እስራኤል ላይ ለ33 ዓመታት መንገሡን ይተርካል /2ኛሳሙ 5፥5/ መጽሐፉ ከሚተርካቸው /የሚያስረዳቸው/ ዋና ዋና ነገሮች መካከል የማንበራዊና የሃይማኖት አስተዳደር ተጠቃልሎ መንበሩ በኢየሩሳሌም መሆኑ የዳዊት ግዛት እስከ ግብጽና እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ መስፋፋቱ፣ የዳዊት መውደቅና መነሣት ናቸው፡፡

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ፡- ከምዕራፍ 2 እስከ 4 ያለው ክፍል በሳኦልና በዳዊት ተከታዮች መካከል የተደረገውን ውጊያና በመጨረሻም ቤተ ዳዊት ያገኘውን ድል ይገልጣል፡፡ የዳዊት ቤት ድል ቢቀዳጅም እንኳ ለሳኦል ቤት ክብር አልነሣውም፡፡ የዳዊት

የጦር መሪ ኢዩአብ የሳኤልን ጄኔራል አቤነርን በመግደሉ ዳዊት ማዘኑንና የሳኦልን ልጅ ኤሽቦሽትን /ኢያቡስቴን/ በገደሉት ሰዎች ላይ ዳዊት መበቀሉን መጽሐፉ በተሠለሪ ይገልጣል፡፡ /ምዕ 4፥5-12/ ዳዊት ከቤርሳቤሕ የወለደው ሕጻን በመሞቱ ከማዘኑም በላይ በቤተሰቡ ውስጥ ብዙ ችግር እንደደረሰበት መጽሐፉ ያስታውሳል፡፡ ከችግሩም አንድ የአቤሴሎም መሸፈትና አሳዛኝ የሆነው አሟሟቱ ነው /ምዕ 13-18/ መጻሕፍቱ የያዙት ታሪክ በ100 ዓመታት ወስጥ የተፈጸመ ሲሆን ይህም ከ1075-975 ነው፡፡

<u>የመጻሕፍቱ አከፋፈል</u>

1. <u>የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ</u>

<u>ሀ. የሳሙኤል የመስፍንነትና የነቢይነት ሕይወት</u>

1. ምዕ 1፥1-3፥21 የሳሙኤል መጀመሪየ ሕይወቱና መጠራቱ፡፡
2. ምዕ 4፥1-6፥21 የታቦተ ጽዮን መማረክና በቤተ ኤሊ ላይ የመጣው ፍርድ
   ሀ. በኦሪት ጦርነት ላይ የታቦተ ጽዮን መማረክ 4፥1-10
   ለ. የደቂቀ ኤሊና የአባታቸው የኤሊ መት 4፥11-12
   ሐ. በኤሎፍላውያን ላይ የወረዱት መቅሠፍቶች 5፥1-12
   መ. የታቦተ ጽዮን ወደ ቤተ ሳሚስ መመለስ 6፥1-21
3. ምዕራፍ 7፥1-17 የሳሙኤል የምስፍና አገልግሎት በምጽጳ በዚህ ክፍል የሳሙኤል የክህነትና የምስፍና ተግባር በሰፊው ተገልጦአል፡፡

ለ. <u>ምዕራፍ 8፥1-15፥35 የሳኦል መጀመሪያ ግዛት /አስተዳደር/</u>

1. ምዕ 8፥1-22 የመንግሥት ጥያቄ
2. ምዕ 9፥1-11፥15 የሳኦል መመረጥና መቀባት
3. ምዕ 12፥1-25 ሳሙኤል ምስፍናውን መልቀቁና መሰናበቱ
4. ምዕ 13፥1-15፥35 በ3 ስህተቶች ምክንያት እስከሚናቅና እስከሚወድቅ ድረስ የሳኦል መንግሥት አስተዳደር
   ሀ. መጀመሪያ ስህተቱ ካህን ሳይሆን መሥዋዕት ማቅረብ /ምዕ 13/
   ለ. ሁለተኛ ስህተት በችኮላ ያደረገው መሐላ ምዕ 14፥36-46
   ሐ. ሦስተኛ ስህተት አማሌቃውያንን በሙሉ እንዲገድል በታዘዘ ጊዜ አጋግን ማትረፉ /ምዕ 15/
   ሐ. <u>ምዕራፍ 16፥1-31 የሳኦል መንግሥት እየቀነሠ መሄድና የዳዊት መነሣት</u>

1. ምዕ 16፥1-13 የዳዊት መቀባት /1-13/ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል መራቅሃ ሳኦል በክፉ መንፈስ መያዙ /14-23/
2. ምዕ 17፥1-58 ዳዊት ጐልያድን ድል ማድረጉ
3. ምዕ 18፥1-19፥17 በዳዊት ላይ የሳኦል መቅናት ሳኦል በዳዊት ላይ ያደረጋቸው ፈተናዎች፡፡ 3 ጊዜ ልጁን እንደሚድርለት እያወራ ካደው 18፥17-19፣ 21፣22-29፡፡
4. ምዕ 19፥18-24 ዳዊት ወደ ራማ ወደ ሳሙኤል መሰደዱ
5. ምዕ 20፥1-42 ዳዊትና ዮናታን በዚህ ክፍል ሁለቱ ኃያላን ዳዊትና ዮናታን በምሥጢር ይነጋገራሉ፡፡ የመጨረሻ ስንብትም ያደርጋሉ፡፡
6. ምዕ 21፥1-27፣12 29፥1-30፥31 ዳዊት እንደ ስደተኛ ሆኖ የኖረው አስደናቂ ኑሮ፣ የሳሙኤል ሞት /25/
7. ምዕ 28፥1-25 ሳኦልና የዐይን እንጸር መተተኛ
8. ምዕ 31፥1-13 የሳኦል ድል መሆንና አሳዛኝ የሆነው ሞቱ፡፡

2. <u>መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ</u>

<u>በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል</u>

ሀ. <u>ምዕራፍ 1፥1-4፥12 ዳዊት በኬብሮን ሆኖ ይሁዳን መግዛቱ</u>

1. ምዕ 1፥1-27 ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን ማልቀሱ
2. ምዕ 2፥1-4፥12 በዳዊትና በሳኦል ልጅ በኤጂቦሼት /ኢ.ያቡስቴ/ መካከል በሥልጣን መንግሥት የተደረገ ትግል

ለ. <u>ምዕራፍ 5፥1-11፥27 ዳዊት ዐቢይ ኃጢአት እስኪፈጸም ድረስ በእስራኤል ሁሉ ላይ መንገሱ</u>

1. ምዕ 5፥1-25 የዳዊት መንግሥት መጽናቱና ንጉሥ መባሉ፣ መናገሻ ከተማውን ኢየሩሳሌም ማድረጉ ኤሊፍላውያንንም /ፍልስጥኤማውያን/ ድል ማደረጉ፡፡
2. ምዕ 6፥1-7፥29 ዳዊት ቤተ መቅደስን ለመሥራት ያቀደው ዓላማና እግዚአብሔር ዓላማውን አለመፍቀዱ
   ሀ. የታቦተ እግዚአብሔር ከቤተ አሚናዳብ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ጽዮን መምጣት /ምዕ 6/
   ለ. እግዚአብሔር መሢውን ኪዳን ለዳዊት በተስፋ መስጠት /ምዕ 7/
3. ምዕ 8፥1-18፡፡ 10፥1-19 የዳዊት ድሎች

4. ምዕራፍ 9፥1-13 ንጉሥ ዳዊት ለዮናታን ልጅ ለሚፊቦሼት /ማበፊቡስቴ/ ያደረገው ቸርነት፡፡
5. ምዕ 11፥1-27 ዳዊት የፈጸመው ዐበይ ኃጢአት ቤርሳቤሐን ማግባቱ /ቤትሻባ/

ሐ. <u>ምዕራፍ 21፥1-20፡26 ዳዊት በኃጢአቱ ምክንያት መቀጣቱ</u>

1. ምዕራፍ 12፥1-35 የዳዊት ቅጣት ከቤት ሻባ /ቤርሳቤሐ/ መጀመሪየ የተወለደው ልጅ መሞቱና ሰለሞን መወለዱ፡፡
2. ምዕ 13፥1-39 የአምኖን ኃጢአትና ሞት
3. ምዕ 14፥1-19፥43 የአቤሴሎም መሸፈት
4. ምዕ 20፥1-26 የሳቤኔ ዘብንያም መሸፈት

መ. <u>ምዕራፍ 21፥1-24፥25 የታሪክ ስብስባች /መስተጋብኦች/ እና በተለያዩ ቀናት የተደረጉ ንግግሮች</u>

1. ምዕራፍ 21፥1-22 በተለያዩ ጊዜየት ከተፈጸሙ ድርጊቶች የተሰበሰቡ ታሪኮች
2. ምዕራፍ 22፥1-51 የዳዊት መዝሙር
3. ምዕራፍ 23፥1-7 የዳዊት የመጨረሻ ቃላት
4. ምዕራፍ 23፥8-39 የዳዊት ኃያላን ስም ዝርዝር
5. ምዕራፍ 24፥1-25 ዳዊት ሕዝቡን በመቍጠሩ ምክንያት ያደረገው በደልና ንስሐ መግባቱን ይናገራል፡፡

የዳዊት ዜና መንግሥት በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ተጀምሮ ዋናው ክፍል በመጽሐፈ ሳሙኤለ ካልእ ቢተረክም በዚሁ አይፈጸምም፡፡ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች የታሪክ ፍጻሜ ይሆናል፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

❖ .

<u>የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ የሙከራ ጥያቄዎች</u>

1.

መጻሕፍተ ነገሥት ቀዳማዊና ካልእ

መግቢያ

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

ይህ መጽሐፍ የነገሥተ ይሁዳና የነገሥተ እስራኤልን ታሪክ ስለሚናገር መጽሐፈ ነገሥት ተብሎአል። በዕብራይስጡ መልካም ይባላል። ነገሥት ማለት ነው።መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልእ እንደ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልእ በአይሁድ ቀኖና አንድ መጽሐፍ ነው ግን አስቀድመን እንደ ተናገርን ሰብዓው ሊቃናት ሁለት መጽሐፍ አድርገው ከፈሉት። ከዚህም ሌላ ከመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ጀምሮ በመቍጠር ሦስተኛ አራተኛ መጽሐፈ ነገሥት ብለውታል።

ጸሐፊው

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በትክክል አልታወቀም። ነቢዩ ኤርምያስ፡- በመጽሐፈ ነገሥት ካልእ 24 እና 25 ምዕራፎች ላይ በሚገኘው ዘመነ ታሪክ ውስጥ ይኖር ስለነበር በይሀን መጽሐፍ የጻፈ እርሱ ነው ብለው የሚያምኑ ሊቃውንት አሉ። ይህም አስተያየት በታልሙድ የተደረገፈ ነው። ኤርምያስ በራሱ ስም የተለሰየመውን መጽሐፍ መጽሐፈ ነገሥትንና ሰቆቃውን ጻፈ ይላልና /ታልሙድ 15/ ጸሐፊው ኤርምያስ ይሁን ሌላ ሰው መጽሐፈ ነገሥትን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የተለያዩ የታሪክ ምንጮች ተጠቅሞአል። የታሪክ ምንጮቹም የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ መፍሐፈ ዜናሁ ለሰሎሞን 1 ነገሥት 11÷41 2ኛ መጽሐፈ ነቢያት ዘነገሥተ እስራኤል /1ነገሥት 14÷19፣ 15÷23፣ 16÷3፣20፣27/። 3ኛ መጽሐፈ ነቢየት ዜና መዋዕል ዘነገሥተ ይሁዳ 1 ነገሥት 14÷29፣ 22÷45 2ነገሥት 15÷36፣21÷17/ ጸሐፊው እነዚህን ምንጮች መሠረት በማድረግ ራሱም በዘመኑ ያየውን ታሪክ በመከታተል በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመራ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊንና ካልእን አዘጋጅቶአል።

መጽሐፈ ነገሥት የተጻፈው እስራኤል ተማርከው በባቢሎን ሳሉ ወይም ከምርኮ /ከዜዋዌ/ በኋላ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም በመጽሐፍ ነገሥት ካልእ 25÷27 ላይ የባቢሎን ንጉሥ የርማሮዴቅ በነገሠ በ1ኛው ዓመት የይሁዳ ንጉሥ ዩአኪን በተማረከ በ37ኛው ዐመት ከእሥር ቤት የመፈታቱን ታሪክ እናገኛለን። የመጀመሪያው የባቢሎን ፀዋዌ በ598 ቅልክ ሲሆን ዮርማርዴቅ ወልደ ናቡከደነጸር በ562 ቅልክ ነገሠ። ከዚህ መካከል 37

ዓመታት ይገኛሉ። እንግዲህ መጽሐፉ ይህን ስለሚተርክ ከዚህ ዘመን በኋላ መጻፉ ግልጥ ነው።

<u>የመጻሕፍቱ ዓላማ</u>

1. <u>መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ</u>፡- በመጀመሪያው ክፍል የሰሎሞንን መንግሥት፣ የግዛቱን ታላቅነትና የቤተ መቅደስን መሠራት ይናገራል። የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በ966 ቅልክ ተጀምሮ እስከ 586 ቅልክ ድረስ በአገልግሎት ላይ ከኖረ በኋላ በ586 ቅልክ በናቡከደነፆር እጅ ተደምስሶአል። ቤተ መቅደሱ በብዙ ወጭና የሰው ኃይል የተሠራ ታላቅ ግርማ ያለው ነበር።

   ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ከሙሉ ዝግጅቱ ጋር ከፈጸመ በኋላ ታላቅ የምረቃ ሥነ ሥርዐት አደረገ። ታቦተ እግዚአብሔር ቀድሞ ከነበረበት ከመገናኛው ድንኳን በታላቅ ግርማ ተነሥቶ ወደ ቤተ መቅደሱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገባ። በዚህም ጊዜ 22000 በሬዎችና 120000 በጎች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ቀርበዋል። እግዚአብሔርም ሥርዓቱንና መሥዋዕቱን የተቀበለ መሆኑን ለማስታወቅ ቤተ መቅደሱን በደመና ሞላው። ንጉሥ ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱ የተሠራበትን ዓላማና ሁኔታ የሚገልጽ ንግግር አድርጐ እጅግ ምርጥ የሆነ የምረቃ ጸሎት ጸለየ። ሕዝቡንም እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልክ መከረ /ምዕራፍ 8/ ከቤተ መቅደሱ ሌላ ንጉሥ ሰሎሞን ለራሱና ግብጻዊት ለሆነች ሚስቱ ግርማ ሞገስ ያላቸው ቤቶችን አሠርቶአል /ምዕራፍ 7፥1-12፣ 9፥24/።

መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ የጣዖት አምልኮትንና የዓመጽ ብዛትን አንድ የነበረው የዳዊት መንግሥት በይሁዳና በእስራኤል መካከል መከፈሉን ይገልጣል።

እስራኤላውያንን የከፋፈሉአቸው ምክንያቶች የቆዩና ሥር የሰደዱ ነበሩ ሁለቱ ነገድ እያደሩ መብትና ሥልጣን እያገኙ በመሄዳቸው ዐሥሩ ነገድ ቅናት አደረባቸው። የኢየሩሳሌም ከተማ በይሁዳ ነገድ /በሁለቱ ነገድ/ ዕፃ ውስጥ መሆንዋም ለቅናት ሰበብ ሆኖ ነበር። በተጨማሪ ንጉሡ ሰሎሞን ከውጭ አገር መንግሥታት የነበረው ግንኙነት በአገር ወስጥ በወንድማማች መካከል የነበረው ሕብረት ሊያዳክመው ችሎአል። ሰሎሞን ከአረማውያን ጋር የሚፈጸመው ጋብቻና እያደር የሚወለደው አምልኮተ ጣዖት የሃይማኖትን ኃይል አድክሞት ነበር። የሰሎሞን ልጅ ንጉሥ ሰሎሞን በህዝቡ ላይ ግብርና ሥራ መጫኑ የህዝቡን ልብ ሊያሸፍት ችሎአል። /ሮብዓም/ ሕዝቡ የለመነውን ለውጥና ግልግል ሳይሰማ በመቅረቱ በሕዝቡ መካከል ታላቅ መሸበር ተፈጠረ። በእነዚህ ሁሉ

ምክንያቶች፡- ዐሥሩ ነገድ ማለት ይሁዳና ብንያም ሲቀሩ አምጸው የሮብዓምን /ኢዮርብዓምን/ አነገሡ፡፡ ሴኬም አዲሲቷ መናገሻ ከተማ ሆነች፡፡ የሸፈቱት /የተገነጠሉት/ ነገዶች ሕዝቡን ከኢየሩሳሌም ለማራቅና የኢየሩሳሌምን ክበርና ግርማ ለመቀነስ በቤቴልና በዳን አብያተ ጣዖትን ተከሉ፡፡

የንጉሥ ዳዊትን ቤት በመደገፍ ሳያምፁ የቀሩት ሁለቱ ነገድ የይሁዳ መንግሥት ወይም የደቡብ መንግሥት በሚል ስም ተጠሩ፡፡ ለመሢሕ መምጣትም የትውልድ መሥመር ሆኑ፡፡ የተገነጠሉት ዐሥሩ ነገድ ደግሞ የእስራኤል መንግሥት ወይም የሠሜን መንግሥት በሚል ስም ተጠርተዋል፡፡ አንድ የነበረው መንግሥተ ዳዊት የተከፈለው በ931 ቅልክ ነበር፡፡

ከመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ቀሪ ክፍል ከምዕራፍ 13 ምዕራፍ 22 እንደምንረዳው በሁለት መንግሥታት መካከል የነበረው የጥላቻ ስሜት ነበር፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የጋራ ጠላት ሲገጥማቸው ይተባበሩ ነበሩ፡፡ በዳዊትና በሰሎሞን ዘንድ ጸጥ ብለው ይገዙ የነበሩ መንግሥታት፡- መንግሥቱ ከተከፈለ በኋላ ማመጽ ጀመሩ፡፡ የኢየሩሳሌምን ታላቅ ሀብት በመጓጓት የሚመኙ ጠላቶች በከተማይቱ ላይ ዘመቻቸውን ያከታትሉበት ጀመር፡፡

የጣዖት አምልኮት በሁለቱም መንግሥታት በተለይ ግን በእስራኤል መንግሥት እየበዛ የሄደ እንደነበር መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ያስረዳል፡፡ በአይሁድ መንግሥት ውስጥ መጠኑ ይለያይ እንጂ የጠራው እምነት ሁልጊዜ እንደተጠበቀ ቆይቶአል፡፡ በዚሁ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ንስሐ ለመጥራትና ለመምራት ስመጥር የሆኑ ታላላቅ ነቢያትን አሥነስቶ ነበር እነዚህም ነቢያት ሳይፈሩ የእግዚአብሔርን ፍርድና የማጽናኛ ቃል ለሕዝቡ ይናገሩ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ነገሥታት የጠራውን ሃይማኖት በመከተልና በሥነ ሥርዓት ለማስተዳደር እጅግ ይጣጣሩ ነበር፡፡ ብዙዎች ግን በአካባቢያቸው የነበረው የሠለጠነው አምልኮተ ባዕድ እያሸነፋቸው ፍርድ ያጐድሉና በጭካኔ ይገዙ ነበር፡፡ ከነገሥታት ሁሉ ክፉ ስም ያተረፈው አክአብ የተባለው የእስራኤል ንጉሥ ነበር፡፡ ሚስቱ ኤልዛቤል የአረማዊው የሲዶን ንጉሥ ልጅ ነበረች፡፡ በእርስዋ ሀሳብ እጅግ አሠቃቂና ወራዳ የነበረውን የበዓልንና የአስታሮትን አምልኮ በእስራኤል ውስጥ አስፋፋ፡፡ ነቢዩ ኤልያስም አክአብን ደጋግሞ እንዳስጠነቀቀውና እንደወቀሰው መጽሐፈ ነገሥት በሰፊው ይገልጣል፡፡

2. <u>መጽሐፈ ነገሥት ካልእ</u>

መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ የሁለቱን መንግሥታት ታሪክ ከመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ በመቀጠል ሁለቱ መንግሥታት በጠላት ተከበው እስከ ተማረኩበትና ሕዝባቸውም ወደ ጽዋዌ እስከሄድበት ጊዜ ድረስ ያለውን ታሪክ ያስረዳል።

<u>የመጽሐፍቱ አከፋፈል</u>

1. **<u>መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ</u>**

ሀ. <u>ምዕራፍ 1፥1-2፥11 የዳዊት የሕይወቱ መጨረሻ ቀኖች</u>

1. ምዕራፍ 1፥1-38 አዶንያስ ንጉሥ ለመሆን ያደረገው ሙከራና ዓላማው ሳይፈጸም መቅረቱ፣
2. ምዕ 1፥39-53 ሰሎሞን ንጉሥ እንዲሆን መቀባቱ፣
3. ምዕ 2፥10-91 ዳዊት በመጨረሻ ጊዜ ለሰሎሞን የሰጠው ትእዛዝ
4. ምዕ 2 10-11 የዳዊት ሞት

ለ. ምዕራፍ 2፥12-11፥43 የሰሎሞን አመራር

1. ምዕ 2፥13-46 ሰሎሞን ተቀዋሚዎቹን መቅጣቱ።
2. ምዕራፍ 3፥1-4፥34 የሰሎሞን ጥበብና እስራኤልን ለመምራት የነበረው ከፍተኛ ዕቅድ።
3. ምዕራፍ 5፥1-6-38 ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ለእግዚአብሔር ማቅረቡ።
4. ምዕ 7፥1-8፥66 ሰሎሞን የሠራቸው አብያተ መንግሥትና በቅዳሴ መቅደስ ጊዜ ያደረገው ንግግርና ረዥም ጸሎት።
5. ምዕራፍ 9፥1-9 እግዚአብሔር ለሰሎሞን የሰጠው ቃል ኪዳንና ማስጠንቀቂያ።
6. ምዕራፍ 9፥10-10፥29 የሰሎሞን ክብር ሀብት ጥበብና ታላቅ ዝነኛ መሆኑ።
7. ምዕራፍ 11፥1-43 ሰሎሞን ብዙ ሚስቶችን ማግባቱ፣ በኃጢአት መውደቁና ኃይሉ እየተቀነሰ ክብሩ እየተዋረደ መሄዱ።

ሐ. ምዕራፍ 12፥1-22፥53 የተከፈለው መንግሥት ወይም የይሁዳንና የእስራኤል ታሪክ እስከ አክአብና ኢዮሳፍጥ ሞት ድረስ

1. ምዕራፍ 12፥1-24፣ 14፥21-31 ሮብዓም /ረሆቢአም/
2. ምዕራፍ 12፥25-14፥20 ኢዮርብዓም ቀዳማዊ /የሮብአም/
3. ምዕራፍ 15፥1-8 አብያም /አቢጀምን/ ንጉሥ ይሁዳ
4. ምዕራፍ 15፥9-24 ኢሳ /አሳፍ/ ንጉሥ ይሁዳ
5. ምዕራፍ 15፥25-26 ናዳብ ንጉሥ እስራኤል። /ናዳብ የኢዮርብዓም ልጅ ነው/

6. ምዕራፍ 15፥27-16፥7 በአሳ /ባሻ/ ንጉሠ እስራኤል
7. ምዕራፍ 16፥8/10 አላ /ኢላህ/ ንጉሠ እስራኤል
8. ምዕራፍ 16፥11-20 ዘምሬ ንጉሠ እስራኤል፡፡ ዘምሪ የነገሠው ሰባት ቀን ብቻ ነው/
9. ምዕራፍ 16፥21-28 ታምኒና ዘንበሬ /አምሬን/ እስራኤል
10. ምዕራፍ 16፥29-22፥40 አክአብ /አሐብ/ እና ነቢዩ ኤልያስ /ንጉሠ እስራኤል ወነቢየ እስራኤል/
11. ምዕራፍ 22፥41-50 ኢዮሳፍጥ /የሆሸፋጥ/ ንጉሠ ይሁዳ
12. ምዕራፍ 22፥51-53 አካዝያስ /አሐዚያ/ ንጉሠ እስራኤል

25 መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ

ሀ. ምዕራፍ 1፥1 17፥41 ከመጽሐፈ ነገሥት

ቀዳማዊ የቀጠለ የሁለቱ መንግሥታት ታሪክ

1. ምዕራፍ 1፥1-18 አካዝያስና /አሐዚያ/ የኤልያሥ ሥራ
2. ምዕራፍ 2፥1-25 የኤልያስ ዕረገትና የኤልሳዕ መተካት
3. ምዕ 3፥1-8፥2-9 የኢዮራም /የሆራም/ ንጉሠ እስራኤል አስተዳደርና የነቢዩ አልሳዕ አገልግሎት
4. ምዕ 9፥1-10፥36 የኢዩ /የሁ/ ንጉሠ እስራኤል አስተዳደርና የኤልሳዕ ሥራ
5. ምዕ 11፥1-22 ግዶልያ /አታልያ/ ንግሥት
6. ምዕ 12፥1-22 ኢዮአስ ንጉሠ ይሁዳ፡፡
7. ምዕ 13፥1-9 ኢዩአካዝ /የሆአሐዝ/ ንጉሠ እስራኤል
8. ምዕ 13፥10-25 ዬአስ / / ንጉሠ እስራኤልና የነቢዩ ኤልሳዕ ሞት
9. ምዕ 14፥1-20 አሜስያስ /አማዚያ/ ንጉሠ ይሁዳ፡፡
10. ምዕ 14፥21-22 15፥1-7 አዛርያስ /አዝያን/ ንጉሠ ይሁዳ
11. 14፥23-29 ኢዮርብዓም /የረባአም/ ዳግማዊ ንጉሠ እስራኤል በዘመኑ ሆሴእ፣ አሞጽ፣ ዮናስ ነበሩ፡፡
12. ምዕ 15፥8-12 ዘካርያስ ንጉሠ እስራኤል፡፡ ይህ የኢዮርብዓም ዳግም ልጅ ነው፡፡
13. ምዕ 15፥13-15 ሳሎም /ሻሎም/ ንጉሠ እስራኤል አንደ ወር ብቻ የነገሰ
14. ምዕ 15፥16-22 ምናሔም /መናሔም/ ንጉሠ እስራኤል ከዚህ ንጉሥ በሄላ እስራኤል ነፃነት፡፡

15. ምዕ 15፥23-26 ፋቂስያስ /ፔካሂያ/ ንጉሠ እስራኤል በቅኝ ግዛት ሆኖ ሁለት ዓመት ነግሧል፡፡
16. ምዕ 15፥27-31 ፋቁሔ /ፔካህ/ ንጉሠ እስራኤል ኢሳ 7፥1
17. ምዕ 15፥32-38 ኢዮአታም ንጉሠ ይሁዳ የአዚያን ልጅ ነው፡፡
18. ምዕ 16፥1-20 አካዝ /አሐዝ/ ንጉሠ ይሁዳ
19. ምዕ 17፥1-41 ሆሴዕ ወልደ ኤላ ንጉሠ እስራኤልና የእስራኤል መንግሥት ፍጻሜ፡፡

ለ. ምዕራፍ 18፥1-25፣ 30 መንግሥተ ይሁዳ ለብቻው እስከ ፍልሰተ ባቢሎን

1. ምዕራፍ 18፥1-20፣21 ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ
2. ምዕራፍ 21፥1-18 ምናሴ ንጉሠ ይሁዳ
3. ምዕራፍ 21፥19-26 አሞጽ /አሞን/ ንጉሠ ይሁዳ
4. ምዕራፍ 22፥1-23፣30 ኢዮስያስ ንጉሠ ይሁዳ
5. ምዕራፍ 23፥31-33 ኢዮአክስ /ዮሆአሐዝ/ ንጉሠ ይሁዳ
6. ምዕራፍ 23፥31፣7 ኢዩአቄም ሲሞት ሳይቀበር ጅብ በልቶታል፡፡
7. ምዕራፍ 24፥8-16 25፥27-30 ዩአኪን /ዮሆ ያኪን/ ስሙ ኢኮንያን ይባላል፡፡
8. ምዕራፍ 24፥17-25፣21 ሴዴቅያስ /ጼዴቅያስ/ እና ኢየሩሳሌም ጥፋት /ፍልስተ ባቢሎን/ የመጀመሪያ ሰው ናታን ነበር፡፡ ሴዴቅያስ የለው ናቡከደነጸር ነው፡፡ ሴዴቅያስ ማለት ባይከዳኝ ማለት ነው፡፡
9. ምዕራፍ 25፥22-26 ጎዶልያስ የይሁዳ ገዥ ሆኖ በናቡከደነጸር ተሾመ

ዘመነ ነገሥት

በእስራኤል ታሪክ ወስጥ መንግሥት ከመከፈሉ በፊትና ከተከፈለ በኋላ ነገሥታቱ ምን ያህል ዘመን እንደገዙ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

1. መንግሥት ከመከፈሉ በፊት ዐሥራ ሁለቱ

ነገደ እስራኤል በአንድ ዘውድ ሥር ለ120 ዓመታት ቆይተዋል፡፡ ይህም የሦስቱ ነገሥት የሳኦል፣ የዳዊትና የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የዐሥራ ሁለቱን ነገደ እስራኤል በአንድ ዘውድ ሥር ለአርባ ዓመት መርተዋልና፡፡

2. የመንግሥት መካፈል

በ1931 ቅልክ መንግሥት ለሁለት ተከፈለ አስቀድመን እንደገለጥነው የተከፈለው መነግሥት የደቡብና የሰሜን መንግሥት እየተባለ መጠራት ጀመረ፡፡ የደቡብ የተባለው የይሁዳ መንግሥት የሰሜን የተባለው ደግሞ የእስራኤል መንግሥት ነው፡፡ የእስራኤል

መንግሥት ተነጥሎ እስከ 722 ቅልክ ድረስ ቆይቶአል። እንግዲህ የዐሥሩ ነገድ መንግሥት ከሁለት ነገድ መንግሥት ተለይቶ ለብቻው 209 ዓመት ቆይቶአል ማለት ነው። በዚህ ዘመን ውስጥ 19 ነገሥት ሲነግሡ እነሱም ከ9 ንጉሣውያን ቤተሰቦች የተገኙ ናቸው። አብዛኛዎቹ ነገሥት ከ10 ዓመት በላይ አላስተዳደሩም። ጠባያቸውም እጅግ የከፋ ነበር። በዘመነ መንግሥታቸው ሀገሩ ሰላም አላገኘም። ይህም ከእግዚአብሔር በመራቃቸው የደረሰባቸው ቅጣት ሆኖ ይታያል።

የሁለቱ ነገድ /የደቡብ/ መንግሥት እስከ 586 ቅልክ ቆየቶአል። እንግዲህ ከተነጠለው ከእስራኤል መንግሥት 135 ዓመት ይበልጣል፡ ማለት ነው። ከዳዊት ቤተሰብ ብቻ የተገኙ 19 ነገሥትና አንዲት ነገሥት ጐቶልያ በእነዚህ ዘመናት ውስጥ አስተዳድረዋል። የእያንዳንዱ ንጉሥ የአስተዳደር ዘመን ድርሻ በጅምላ 17 ዓመት ያህል ይሆናል። የነገሥተ ይሁዳ አስተዳደር ይበልጥ ጸጥታ ሊያገኝ የቻለው ንግሥቲቱ እውነተኛ ሃይማኖት ከእስራኤል ነገሥት ይልቅ ይከተሉ ስለነበር ነው። ከነገሥቱ መካከል፡- ኢዮሳፍጥ ኢዩአስ ሕዝቅያስና ኢዮስያስ አምልኮተ ጣያትንና ኃጢአት ያስከተለውን ጠንቅ ለማረም የሚጣጣሩ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ነገሥት ነበሩ። የነገሥቱን ዓመተ መንግሥት በኋላ እንደመለከታለን።

የዘመነ ነገሥት ነቢያት፡- የሕዝቡን የሞራል ውድቀት በትምህርታቸው በርትተው ይከላከሉ ነበር። በመጠኑም መልካም ውጤት አግኝተዋል። ክፉዎች ነገሥት ግን በነቢያት አፍ የሚነገራቸውን የእግዚአብሔርን ቃል እምቢ ብለው ነቢያትን እንደጠላት በመቍጠር ያስቸግሩአቸውና ብዙዎችንም ይገድሉ ነበር። ሁለቱ መንግሥታት እላይ የተጠቀሱትን ዘመናት ለመኖር የቻሉት በእግዚአብሔር ትእግሥትና የነቢያት አገልግሎት ባስገኘው እርማት መሠረት ነው። ሆኖም መንግሥታት መጨረሻ አልቆየም።

የእስራኤል መንግሥት በ722 ቅልክ ጠፋ። ስልምና ሰር /ሻልማኒዛር/ የተባለው የአሶር ንጉሥ ብዙውን ሕዝብ ወደ አሶር አፈለሰ። የፈለሰውም ሕዝብ ወደ ሀገሩ ሳይመለስ ቀርቶአል። የፈለሰው ሕዝብ "የጠፋው ነገድ" እየተባለ እስካሁን ደረሰ መድረሻው ሳይታወቅ ምርምር ሲደረግበት ይኖራል። ሆኖም የፈለሰው የእስሪኤል ሕዝብ ከአሶር ሕዝብ ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ በተጋዘበት /በፈለሰበት/ አገር ተውጦ የቀረ መሆኑ እስካሁን ይነገራል። የአሶር ንጉሥ ከእስራኤል በፈለሰው ሕዝብ ምትክ ሌሎችን አሕዛብ ወደ እስራኤል አስገባ። አዲስ ገብም የሆነው ሕዝብ በእስራኤል ውስጥ ከቀረው ሐዝብ ጋር በመጋባቱና በመዋለዱ በዘርም በሃይማኖትም ቅይጥ /ውጥንቅጥ/ የሆነ ሳምራዊ በሚል ስም

የሚታወቅ ሕዝብን አስገኘ፡፡ ሳምራውያን እስከ ዘመነ ክርስቶስ ከይሁዳ ሕዝብ ጋር ጠብ ነበራቸው፡፡ ሁለቱም ሕዝብ በማናቸውም ነገር ሕብረት አልነበራቸውም፡፡ የይሁዳ መንግሥት በ586 ቅልክ ተደመሰሰ፡፡ ናቡከደነጸር የተባለው የባቢሎን ንጉሥ ሕዝቡን ወደ ባቢሎን አፈለሰ፡፡ የፈለሰውም ሕዝብ ለ70 ዓመት በፀዋዌ ከቆየ በኋላ በ536 ቅልክ ወደ ሀገሩ ተመልሶአል፡፡ የይሁዳ ነገድ የመሢህ መሥመር ሆኖ በመገኘቱ የይሁዳ ሕዝብ በግዛት /-----/ መመለስ የእግዚአብሔርን ዓላማ ያመለክታል፡፡

የተከፈለው መንግሥት፤ ነገሥታቱና ዘመነ መንግሥታቸው

ተ.ቁ	ነገሥተ ይሁዳ ስም	ዘመነ መንግሥት ዓ.ም	ዘመነ መንግሥት ቅልክ	የተረከቡበት ክፍል ምዕራፍ ቁጥር
1	ሮብዓም	17	931-931	1ነገ 12፥20-24፡፡ 14፥21-11
2	አብያ	3	931-910	1ነገ 15፥1-8
3	አሴፍ	41	911-869	1ነገ 15፥9-24
4	ኢዮሳፍጥ	25	973-848	1ነገ 15፥41-50
5	ኢዮራም	8	848-841	2ነገ 8፥16-24
6	አካዝያስ ጎቶልያ	1 6	841 841-835	2ነገ 8፥25-29 2ነገ 11፥1-21
7	ኢዮአስ	40	835-796	2ነገ 12፥1-21
8	አሜስያስ አዛርያስ	29	796-767	2ነገ 14፥1-20
9	ያዝያን /አዛርያስ	52	791-739	2ነገ 14፥21-22፥15፥1-7
10	ኢዮአታም	16	750-732	2ነገ 15፥32-38
11	አካዝ	16	735-715	2ነገ 16፥1-20
12	ሕዝቅያስ	29	766-689	2ነገ 18፥20 ምዕ
13	ምናሴ	55	685-641	2ነገ 21፥1-8
14	አሞጽ	2	642-639	2ነገ 12፥1-23፣30/19-26
15	አዮስያስ	31	640-908	2ነገ 13፥31-33 /22፥1-23/3
16	ኢዮአክስ	3 ወር	608	2ነገ 23፥31-33
17	ኢዮአቄም	11	608-597	2ነገ 23፥34-24፥7
18	ዩአኪን	3 ወር	597	2ነገ 24፥8-16፣ 25፥27-30
19	ሴዴቅያስ	11	597-586	2ነገ 24፥17-25፥21

የተከፈለው መንግሥት ነገስታቱና ዘመነ መንግሥታቸው

ተ.ቁ	ነገሥተ ይሁዳ ስም	ዘመነ መንግሥት ዓ.ም	ዘመነ መንግሥት ቅልክ	የተረከቡበት ክፍል ምዕራፍ ቁጥር
1	ኢዮርብዓም	22	931-909	1ነገ 12፥20-24፡፡ 14፥21-31

	ቀዳማዊ			
2	ናዳብ	2	909-907	1ነገ 15፥1-8
3	ባኦስ	24	907-883	1ነገ 15፥9-24
4	ኤላ	2	883-881	1ነገ 15፥41-50
5	ዘምሪ	7 ቀን	881	2ነገ 8፥16-24
6	ዘንባሪ ታምኒ	12 5	881-869 880	2ነገ 8፥25-29 2ነገ 11፥1-21
7	አክአብ	22	869-847	2ነገ 12፥1-21
8	አካዝያስ	2	847-845	2ነገ 14፥1-20
9	ኢዮራም	12	845-833	2ነገ 14፥21-22፥15፥1-7
10	ኢዩ	28	833-805	2ነገ 15፥32-38
11	ኢዩአካዝ	17	805-788	2ነገ 16፥1-20
12	ዮአስ	16	788-775	2ነገ 18፥20 ምዕ
13	ኢዮርብዓም ዳግማዊ	41	772-731	2ነገ 26
14	ዘካርያ	16 ወር	731	2ነገ 22፥1-23፣30
15	ሳሎም	1 ወር	731	2ነገ 23፥31-33
16	ምናሎም	10 ወር	731-721	2ነገ 23፥31-33
17	ፋቂስያስ	2 ዓመት	721-719	2ነገ 23፥34-24፥7
18	ፋቁሔ	20 ዓመት	719-699	2ነገ 24፥8-16፣ 25፥27-30
19	ሆሴዕ	9 ዓመት	699-690	2ነገ 24፥17-25፥21

<u>ኅዶልያስ</u>፡- ከጴዋዊ በኋላ ለየሁዳ በትሩፋት ላይ አለቃ ሆኖ ተሾሞ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዘርአ መንግሥት ባለመሆኑ ከነገስተ ይሁዳ አልተቆጠረም 2ነገ 25፥22-26 ከቍጥር 6 በታች ባለው ምልክት /*/ የተጠቀሰችውመ ንግሥት /ታምኒ/ ከነገስት ቁጥር ተራ አትቆጠርም፡፡

በሆሴዕ ወልደ ኤላ ዘመነ መንግስት /722 ቅልክ/ ሰሜናዊው/ የእስራኤል መንግሥት ወደቀ፡፡ ሕዝቡም ወደ አሶር ፈለሱ፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

- .

<u>የመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ የሙከራ ጥያቄዎች</u>

1.

መጽሐፈ ኢሳይያስ

መግቢያ

የመጽሐፉ ሥም አሠያየም

በአይሁድ የብሉይ ኪዳን ቀኖና የደኅርት ነቢያት መጀመሪያ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነው። መጽሐፉ በነቢዩ በኢሳይያስ ስም ተሰይሞአል። ኢሳይያስ የሚለው ስም በዕብራይስጥ ሁለት ዓይነት መልክ አለው። አንደኛው ረጅም ሁለተኛው ግን አጭር ነው። ረዥም "ያሻያሁ" የሚል ነው። ይሻ መድኃኒት ያሁ አምላክ ማለትን ያሳያል። አጭሩ ደግሞ ያሻያ የሚል ሲሆን ትርጉሙ አምላክ መድኃኒት ማለት ነው። የሻያ የሚለው ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል። /1ዜና 3፥21፣ ዕዝ 8፥7፣19፣ ነህ 11፥7/

ኢሳይያስ የሚለው አጠራር የግሪክ ነው። የላቲኑ ደግሞ እስያ ይላል በእንግሊዝኛ ግን አይዛያ ተብሎ ይጠራል። የእግዙም ሆነ የአማርኛው ስያሜ የሰብዓ ሊቃናትን ወይም የግሪኩን ይከተላል።

በመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደተገለጠው የኢሳይያስ አባት አሞጽ ይባላል። ይሁን እንጂ ከነቢዩ አሞጽ የተለየ ነው። በዕብራይስጥ የነቢዩ አሞጽ ስም መጨረሻ ፊደል ሳምኬት ሲሆን የኢሳይያስ አባት የአመጽ ስም መድረሻ ፊደል ግን ጸዴ ነው። በዚያውም ላይ ይጠብቃል። ትርጉሙም ዓሞስ ፀወሪ ማለት ሲሆን አምጽ ደግሞ ኃይል ወይም ጽንእ ማለት ነው።

ከንጉሡ ከአሞጽ የተለየ ነው። የምናሴ ልጅ አሞጽ ተብሎ መጠራቱ በግእዝ እንጂ በዕብራይስጥ አሞን ነው ትርጉሙም አማን የታመነ ወይም እሙን ማለት ነው። /ነህ 7፥59 ዕዝ 2፥57/ የዚህ ተመሳሳይ ነው።

1. ኢሳይያስ የነበረበት ዘመን

ነቢዩ ኢሳይያስ፡- በአራቱ ነገሥተ ይሁዳ በአዝያን ኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግስት ይኖር ነበር። /ኢሳ 1፥1/ በምናሴም ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ እንደ ነበር ይገመታል። ከዚህ ጋር አይሁድ በትውፊታቸው፡- ምናሴ ኢሳይያስ በኩለ ብ አሰቀለ በመጋዝ አስቆርጦ እንደ አስገደለው ይተርካሉ። ይህም ትውፊት በኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡ /2ነገ 21፥16/

2. <u>መጠራቱና ሕይወቱ</u>

ኢሳይያስ ንጉሡ ኦዝያን በሞተበት ዓመት /739 ቅ.ል.ክ/ ለነቢይነት ተጠራ ኢሳይያስ /ነቢዩ ኢሳይያስ ባለሚስትና የሁለት ልጆች አባት ነበረ፡፡ የልጆቹም ስም ሻር ያሹር ትራፍ ይመላሳል /ኢሳ 7፥3/ መሀርሻላል-ሀሽ-በጽ/ምርኮ ፈጠነ ብዘበዛ ቸኮለ ይባላል፡፡ ይህመ ስመ ትእምርት ነው፡፡ /8፥1-4/

<u>ኢሳይያስ የነበረበት ዘመን ሁኔታ</u>

---ዩ ኢሳይያስ የነበረበት ዘመን የይሁዳ መንግሥት ከአንባቢው መንግሥታት ጋር ሰላም አልነበረም ለምሳሌ በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ገደማ ሦርያና እስ-ል ተባብረው በይሁዳ ላይ ተነሡተው ነበር /2ነገ 15፥37/ በአጎዝ ዘመነ መንግስትም አንድ ኃይል የነበረው የአሶር ንጉሥ ቴልጌልቴል ፌልሶር ግልሳዊ ይህንን /ታናናሽ/ መንግሥታትን ለማስገበር በተነሣ ጊዜ ረዐሶን ንጉሠ ሶርያና ፋቁሔ ንጉሠ እስራኤል አሦርን ለመከላከል ተባበሩ በጦርነትም ላይ አካዝ ንጉሠ ይሁዳ እንከባበራቸው ቢጠይቁት ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ በ735 አካዝን ለመጣል ተነሡ፡፡ በዚህ አካዝ ከአሦር ንጉሥ እርዳታን ቴልፌልስርም በሰሜን ገሊላና በምሥራቅ ዩርዳኖስ በኩል ወታደር ማሰፈሪያ ቦታዎችን ተቀብሎ ሶርያሃ እስራኤልን ወጋቸው፡፡ ይህመ የሆነው ከ754-732 ቅልክ ነበር፡፡ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ ይሁዳ ለአሦር ገባር ሆነ፡፡

ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥትም ስልምናሦስ ሐምሳዊ ሰርሳ ዳግማዊና ሰናክሬም የተባሉ የአሦስር ነገሥት በየጊዜው እየተነሡ የይሁዳንና የእስራኤልን መንግሥታት ያውቅ ነበር፡፡ በ722 ቅልክ እስራኤል በአሦር ተያዘች እስራኤልላውያንም ተማረኩ፡፡ የሮም ንጉሥ ሕዝቅየስ አሦርን ስለፈራ የተጣለበትን ግብር ለመክፈል ተስማምቶ ነበር ይሁን እንጂ የአሦር ንጉሥ በዚህ የማይመለስ ስለሆነ ሕዝቅያስና ሠራዊቱ በ-- ንጉሠ ተማመኑ /2ነገ 18፥14-19፥36 ኢሳ 32፥2-37፥37/ ሆኖም ሰናክሬም በንጉሱ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል ድል ሆነ በነዚህም ጊዜ እግዚአብሔር በ--- ያናገረው ቃል ተፈጸመ /2ነገ 19፥29-37/ የኢሳይያስ ተልእኮ እነዚህን ድዎችና እነርሱን የመሰለውን ዓለም አቀፍ ሽኩቻ፣ እንደዚሁም በመዘኑ በይሁዳ የነበረውን ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታዎች የሚመለከት ነበር፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በ--- ኢሳይያስ ከምዕራፍ 1-39 የተመዘገቡ ሲሆን

ከምዕራፍ 40-66 ግን እነርሱን --- ጥቅስ የለም፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስም ከምዕራፍ 40 በኋላ በስም አልተጠቀሰም፡፡

ጸሐፊው

ትንቢተ ኢሳይያስ ጸሐፊ የተለያየ አስተያየት አለ፡፡ ለምሳሌ፡- 1 ታልሙድ ሕገ-ሰዎቹ /ባለሙዋሎቹ ትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፈ ምሳሌን መጋልየ ----ና ራግ መክብብን እንደጻፈ በታልሙድ ተገልጦአል፡፡ ነገር ግን ይህ አስተያየት የኢሳይያሰን ጸሐፊነት አያስተባብልም፡፡ ምክንያቱም ጻፈ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ከተበ ሲሆን ብዙ ትርጉም አለው ለምሳሌ እንደገና መጻፍ ማዘጋጀት መቅዳት ማብዛት ወዘተ ሊሆን ይችላል ስለዚህ ሕዝቅያስ እንደገና አስቀድቶት ይሆናል እንጂ በመሠረቱ ርሱ ጻፈው ለማለት አይቻልም /ምሳ 25፥1/

2. ሙሴ ቤን ሳሙኤል ኢብን ጌካቱላ /110/

ይህ ሊቅ በኢብን እዝራ ጽሕፎች ላይ ባደረገው ምርምርና ትርጉም እጅግ የታወቀ ነው፡፡ በመጀመሪያው በኢሳይያስ ክፍል ያሉ ትንቢቶች በሕዝቅያስ ዘመን የተነገሩ እንደ ነበሩ ሙሴ ቤን ሳሙኤል አመልክቶአል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ያሉት ደግሞ በሁለተኛው ቤተ መቅደስ ጊዜ /537/ እንደ ተነገሩ ጽፎአል፡፡

ኢብን እዝራ ራሱ በመጽሐፈ ኢሳይያስ ላይ ድንቅ የሆነ ትርጓሜ ኮሜንታሪ አዘጋጅቶአል፡፡ በዚህመ ትርጓሜው ውስጥ ከምዕራፍ 40-66 በኢሳይያስ ወልደ አሞጽ መጻፉ ክዶአል፡፡

3. ቤሮንሀርድ ዱም /1847-1920/

ይህ የብሉይ ኪደን ሊቅ በ1892 ዓ.ም በትንቢተ ኢሳይያስ 56-66 ያሉትን ምዕራፎች ከ40-55 ካለው ክፍሉ አንድ ትርጓሜ /ኮሜንታሪ/ ጻፈ፡፡ ዱም አስተያየቱን ሲሰጥ ከ40-55 ያለው ክፍልና ከ56-66 ያለው ክፍል በአንድ ሰው የተጻፈ አይደለም ብሎአል፡፡ በተጨማሪም ስለ ስብሐት ቅኔዔ የሚናገሩት ከ40-55 ያሉት ምዕራፎች በ540 ቅልክ ገደማ ይኖር በነበረ በአንድ ሰው መጻፋቸውን አምኖአል፡፡ የተጻፉበት ቦታመ ባቢሎን ሳይሆን ሊባኖስ ወይም ሰሜን ፊኒቄ እንደሆነ /ተናግሮአል/ መርምሮአል፡፡ ከ55-66 ያሉ ምዕራፎችንም በሚጠት ጊዜ አካባቢ በኢየሩሳሌም ይኖር የነበረ አንደ ሰው እንደ ጻፋቸው ዱም ገምቶአል፡፡

በዚህ መሠረት መጽሐፈ ኢሳይያስ በተለያዩ ሦስት ሰዎች ዘመናትና አርእስት እንደተጻፈ በጥቂት ዘመናውያን ሊቃውንት ዘመንደ ተቀባይነትን አግኝቶአል፡፡ ከዚህም

የተነሣ በእነዚህ ሊቃውንት ዘንድ ኢሳይያስ ቀዳማዊ /1-39/ ኢሳይያስ ካልእ /40/55 ኢሳይያስ ሣልስ /56-66/ በመባል ተሰይሞአል፡፡ ለዚህም የተሰጠው ምክንየት ምዕ 1-39 የኢሳይያስ ስም 16 ጊዜ ሲጠቀስ፣ 40-66 ግን አንድ ጊዜ እንኳ አልተጠቀሰም የታሪኩም ይዘት የተለየ ነው የሚል ነው፡፡

ነገር ግን አብዛኛዎቹ የብሉየ ኪዳን ሊቃውንት በተለይም ኦርቶዶክሳውያን በስሙ የተሰየመውን መጽሐፍ በሙሉ የጻፈ ኢሳይያስ ወልደ አሞጽ መሆኑን አምነው ይቀበላሉ፡፡ ስለዚህም የሚቀርቡት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ኢሳይያስ ከሁሉም ነቢያት ይልቅ በብዛት ተጠቅሶአል፡፡ ይህም በስሙ የተጠራውን መጽሐፍ በሙሉ ኢሳይያስ አልጻፈውም የሚለውን ሀሳብ ይቃወማል፡፡ በዮሐንስ ወንጌል 12፥38-41 ያሉት ጥቅሶች ከሁለቱም ከካልእና ከቀዳማዊ ኢሳይያስ የተወሰዱ ሲሆኑ ለአንድ ኢሳይያስ የተሰጡ ናቸው /53፥1፣6፥9/

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክት 9፥27-33 ከኢሳይያስ ቀዳማዊ 1፥9፣ 8፥14፥ 28፥16 ከጠቀሰ በኋላ እንደገና በዚሁ በሮሜ መልእክቱ 10፥15-21 ከኢሳይያስ ካልእ 52፥7፣ 1፥65-1 እና 2 ሲጠቅስ ኢሳይያስ የሚል አንደ ስም ብቻ ተጠቀመ እንጂ ልዩነትን አላሳየም በዚህ አንጻር ይህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሰበት ክፍል	የተጠቀሰው ምዕራፍ	የጥቅሱ ምንጭ
ማቴ 3፥3	ኢሳይያስ 40፥3	ካልእ
ማቴ 8፥17	ኢሳይያስ 53፥4	ካልእ
ማቴ 12፥17	ኢሳይያስ 41፥1	ካልእ
ማቴ 13፥14	ኢሳይያስ 6፥9 እና10	ቀዳማዊ
ማቴ 15፥7	ኢሳይያስ 29፥13	ቀዳማዊ
ማቴ 1፥2	ኢሳይያስ 40፥3	ካለእ
ማቴ 7፥6	ኢሳይያስ 29፥13	ቀዳማዊ
ሉቃ 3፥4	ኢሳይያስ 40፥3	ካልእ
ሉቃ 4፥17	ኢሳይያስ 61፥1-2	ሣልስ
ዮሐ 1፥23	ኢሳይያስ 40፥3-5	ካልዕ

ዮሐ 12፥38	ኢሳይያስ 53፥1	ካልዕ
ዮሐ 12፥39	ኢሳይያስ 60፥9 እና 10	ቀደማዊ
ዮሐ 12፥40	ኢሳይያስ 53፥7-8	ቀዳ፣ ካልእ
የሐዋ 8፥28	ኢሳይያስ 53፥7-8	ካልእ
የሐዋ 8፥30	ኢሳይያስ 53፥7-8	ካልእ
የሐዋ 8፥32	ኢሳይያስ 6፥9 እና 10	ካልእ
የሐዋ 28፥25	ኢሳይያስ 10፥22 እና 23	ቀዳማዊ
ሮሜ 9፥27	ኢሳይያስ 1፥9	ቀዳማዊ
ሮሜ 9፥29	ኢሳይያስ 53፥1	ቀዳማዊ
ሮሜ 10፥16	ኢሳይያስ 65፥1	ካልእ
ሮሜ 10፥20		ሣልስ

የእነዚህ ጠባይ ጥቅሶች መላው መጽሐፈ ኢሳይያስ ከሐዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች በፊት ለኢሳይያስ ተሰጥቶ ይነገር እንደነበርና የሐዲሰ ኪዳን ጸሐፊዎችም የኢሳይያስ ቃል አድርገው እንደተመለከቱት በግልጥ ያስረዳል፡፡

2. ኤክላስያስቲክስ /መጽሐፈ ሲራክ 195-168/ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 48፥17–25 ኢሳይያስ በጽዮን የሚያለቅሱትን አጽናናቸው በማለት ገልጦአል፡፡ ይህም ማጽናሃት ከኢሳ 40፥1 እና 60-1 የተጠቀሰ ነው በተጨማሪ በጽዮን የሚያለቅሱትን እንጂ በባቢሎን የሚቸገሩትን አጽናና አለማለቱ መጽሐፉ በኢሳይያስ ዘመን በኢየሩሳሌም መዘጋጀቱን ያመለክታል፡፡

<u>የመጽሐፉ ዓላማ</u>

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ድኅነት በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በሰው እንዳሆነ እውነትን ለማስተማር ነው፡፡ ለምሳሌ የይሁዳ ሕዝብ ከጠላቶቻቸው እሥራኤላውያን የዳኑ በተማመኑበት በግልጽ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል ነበር፡፡

ይህ መጽሐፍ ስለ መሢሑ /ክርስቶስ/ በግልጥ ይናገራል ለምሳሌ 7፥14፣ 9፥6-7፣ 52፥13-53 በጠቅላላ በዓለም ላይ ስለሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ይናገራል /24-27/ ምዕራፋት የመጽሐፉ ትንቢት ተግሣጽና ምክር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማለት ይሁዳንና እስራኤልን ብቻ ሳይሆን አሕዛብንም ይመለከታል፡፡ /13-23/ የመጽሐፉን ጠቅላላ ይዘት በአከፋፈሉ ላይ እንደመለከታለን፡፡

አክፋፈሉ

/1ኛ ኢሳይያስ/

ሀ. 1፥12፥6 ይሁዳንና ኢየርሳሌምን የሚመለከቱ ትንቢቶች

1. 1፥1-31 ታላቅ ወቀሳ፡- ቊጥር 1 ጠቅላላ መጽሐፍ መግቢያ ነው፡፡ እንደዚሁም የመጽሐፉን ዓይነት ጸሐፊውንና /አዘጋጂውን/ ዘመን ይገልጣል፡፡ ከ2-9 ባሉ ቊጥሮች የሕዝቡ የሞራል ውድቀት ከእግዚአብሔር የመለየታቸው ውጤትና በሕዝቡ ላይ የሚመጡት መቅሠፍቶች ሁሉ ምክንያት እንደሆነ ይታያል፡፡ ቊጥር 10-20፡- ከእግዚአብሔር የራቀ ልብ ርኩስ ጠባይዕና ግብር ባላቸው ስዎች የሚፈጸመው ሥርዓት ቊርባን ሁሉ ወጋ ቢስ መሆኑን ይገልጣል፡፡ ከ23-31 የሚገኙ ቊጥሮች በጊዜው ያለውን የሞራል ውድቀት ከቀድሞው የኢየሩሳወም /ከተማ/ ቅድስና ጋር ያነጻጽራል፡፡ በተጨማሪም፡- እግዚአብሔርን የሚቋቋሙ እንደሚጠፉና ጽዮን እንደቀድሞዋ እንደምትሆን ይገልጣሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንደኛውና በሁለተኛው ክፍል ሰዶምና ገሞራ በሁለት ዓይነት ጥቅስ ቀርበዋል፡፡ /9፣10/ ቊ 9 በትክክል /በቄሙ/ ሰዶምና ገሞራን ሲመለከት በቊጥር 10 ላይ የሰዶምና ገሞራ መጠቀስ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡

2. ምዕራፍ 2፥1-4፣6 የመሢሑ ግዛትና የክርስቶስ በሕዝቡ ላይ የሚሆኑ ፍርዶች 2፥1 በዚህ ክፈል ለሚነገረው ትንቢት የመግቢያ ርእስ ነው፡፡ ቊጥር 2-4 ሕዝበ እግዚአብሔር በእውነተኛ ሃይማኖት እንደሚኖሩ ቊ 5-8 የሕዝቡ ሁኔታ በኢሳይያስ ዘመን እንዴት እንደነበር ይገልጣል፡፡ 2፥9-11 የሕዝቡን መዋረድ ይጠቅሳል፡፡ ቊ 12-17 እግዚአብሔር የሚከብርበት የሰው መታመኛ የሆነው ሁሉ ዝቅ የሚልበት የእግዚአብሔር ቀን መምጣት ያታውቃል፡፡ ቊ 18፥22 ጣየታት ሁሉ እንደሚደመሰሱ ይናገራል፡፡ 3፥1-15 ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ኃይልና ረድኤት ይርቃል መሪዎችና ታላቅ ሰዎች ይወስዳሉ፣ ይህም በመሪዎች ኃጢአት ምክንያት ይሆናል /ቊ 12 ቊ16-4፥1 የይሁዳ ሴቶች በትዕቢታቸውና መንደላቀቃቸው ይዋረዳሉ፡፡ 4፥2-6 ኢሳይያስ ወደ መሢሑ ርእስ ነገር በመመለስ ይህን ክፈል ይደመድማል ይህም በመሢሑ ጊዜ የተፈጸመውን የቤተ ክርስቲያንን ውስጣዊ ሁኔታ ያመለክታል፡፡ በምዕራፍ 2፥2-4 ያለው ሀሳብ ከጥቂት ልዩነት ጋር በትንቢተ ሚክያስ 4፥1-3 ላይ ይገኛል ከሁለቱ ነቢያት ማንኛው የሌላቹን እንደጠቀሰ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ሚክያስና ኢሳይያስ በአንድ ዘመን ነበሩና፡፡ /745-695/

በትንቢት ኢዮኤልም 3፥9-11 ያለው ቋንቋ በኢሳይያስ 2፥2-4 ተመሳሳይነት አለው፡፡ አዮኤል ከኢሳይያስ ስለሚቀድም ኢሳይያስ ጠቅሶት ይሆናል፡፡ /36-777/ ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት ከኢሳይያስ የኢዬኤልን ቅድምና አይቀበሉም፡፡ እዚህ ላይ ሊያዝ የሚገባው ነጥብ እያንዳንዱ ነቢይ ትንቢት የሚናገረው በመለኮታዊ አነሣሽነት መሆኑ ነው፡፡

3. **ምዕራፍ 5፥1-30 ግልጽ የሆነ የይሁዳ** በደል ቁ 1-7 የነበረውን የሕዝቡን ታላቅ ክብርና በኋላ በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ውድቀት በምሳሌ በቅኔ ይገልጣል፡፡ ቁ 7-30 ምሳሌውን /ቅኔውን/ ይተረጉማል፡፡ በሕዝቡ ላይ ታላቅ ውድቀትና የሚያስከትለው በደልና ወዬታ በዚህ ክፍል በዝርዝር ከመነገሩመ በላይ ቅጣትም ተጨምሮ ተገልጦአል፡፡
4. **6፥1-13 ኢሳይያስ ጌታን ያየበት ራእይና ጥሪው** ምዕራፍ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ 1-8 ራእይ፡፡ 9-13 መልእክት ይህ መዕራፍ ከሚከተሉት ምዕራፎች ጋር ይነጻጻራል፡፡ 6፥9 ከ42፥18-20 እና ከ43፥8፣6፥10 ከ43፥17 ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው የኢሳይያስ ጥሪ የመጀመሪያ የነቢይነት ጥሪ ሳይሆን ለልዩ መልእክት ነው፡፡
5. 7፥1፣ 12፥6 በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተነገሩ ትንቢቶች 7፥1-16 ከሦርያና ከእስራኤል ኃይል የመዳንን ተስፋ እንደዚሁም የመሢሑን ድንግልናዊ ጽንስና ልደት በትእምርት ያውጃል፡፡ 7፥17-25 አካዝ ባለማመኑና ከአሦር ጋር በመተባበሩ ምክንያት በይሁዳ ላይ የሚወጣውን ክፉ ነገር ይገልጣል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ቁ 8 ላይ “በ65 ዓመት ኤፍሬም ይሰባበራል ይላል፡፡

ሀ. ሦርያና እስራኤል በ735 ዓ.ም ይሁዳን ወረሩ፡፡

ለ. በ734 ቅልክ የእስራኤል ሴሚናዊ ግዛት ተወሰደ

ሐ. በ722 ዓ.ም የእስራኤል ብሔራዊ ሕልውና ፈጽሞ ተደመሰሰ

መ. በ669 ቅልክ የእስራኤል ክብረ ዘርእ፣ ስም አጠራር በየትኛውም ጠፋ በዚህ ጊዜ የኢሳይያስ ትንቢት ተፈጸመ /735-669-66/

ሕፃኑና ድንግል 7፥10-16

ንጉሡ አካዝ የእግዚአብሔርን አድንኖት በተጠራጠረ ጊዜ ድንግል በድንግልና ጸንሳ በድንግልና እንደምትወልድ የሚወለደውም ሕጻን ምልክት እንደሚሆንለት ተነገረው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አንዳንድ የብሉይ ኪደን ሊቃውንት የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣሉ፡፡

ነቢዩ፡- እግዚአብሔር ራሱ ምልክት ይሰጣችሁአል ስላለ ይህ ምልክት በዘመኑ ለሚደረገው ነገር ማረጋገጫ ነው፡፡ ስለዚህ ምልክት ይሆናል የተባለው ሕጻን በዚየው ዘመን ተወልዶ ይሆናል የሚሉ አሉ፡፡ ለዚህም 16 ቍጥርን ማስረጃ አድርገው ይጠቅሳሉ፡፡ የሕጻኑ ስም አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፡፡ እግዚአብሔር ከይሁዳ ሕዝብ ጋር በረደኤት በሚሆንበት ጊዜ ስለሚወለድ ይህ ስም ተሰጥቶታል፡፡ አይሁድ ወቅታዊ ድርጊትን በመመርኮዝ ስም የማውጣት ልማድ አላቸው 1ኛ ሳሙ 4፥21 ኢካብድ፡፡ ነገር ግን ነቢዩ በምዕ 9፥6-7 እንደተናገረው በአካዝ ዘመን የሚወለድ ሕጻንን ሳይሆን የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ የተወለደውን ክርስቶስን ያመለክታል፡፡ ከጥንተም ጀምሮ የመንፈሳውያን ሊቃውንት ትርጉም ይህ ነው /ማቴ 1፥23/፡፡

በቍጥር 14 “ድንግል” የተባለው ቃል በዕብራይስጥ ዐልማህ ነው፡፡ ይህንም የሚመስል በዘፍጥረት 24፥43 ዘፀ 2፥8 ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ድንግል ለማለት ዕብራይስጡ በቱላህ ይላል /ዘሌዋ 21፥3/ በኢሳ 7፥14 ዐልማህ የሚለው ቃል በሰብዓ ሊቃናት ፖርቴኖስ ተብሎ ተተርጉሞአል ይህም ድንግል ማለት ነው፡፡

6. 8፥1-4 የሶርያና የእስራኤል ውድቀት እንደገና በምሳሌ ተገልጦአል እዚህ ላይ ምሳሌ ሆኖ የቀረበው ሌላ ሕጻን ነው፡፡ እርሱም የኢሳይያስ ልጅ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ለምሳሌና ለምልክት የተጠቀመባቸው ሕጻናት 3 ናቸው እነርሱም
   ሀ. ሺር ያሹብ
   ለ. አማኑኤል
   ሐ. መሀር ሻላል-ሀሽ-ባጽ ናቸው
7. 8፥5-8 ይሁዳ ባለው በመታመንዋ ምክንያት ትቀጣለች፡፡ 8፥9-22 ሕዝቡ እግዚአብሔርን ብቻ መፍራት መቀደስና ቃሉን መጠበቅ አንደሚገባቸው ነቢያት ያስጠነቅቃሉ፡፡ 9፥1-7 በሀገር ሁሉ ላይ /በይሁዳ/ የሚደርሰው መከራ በድቅድቅ ጨለማ ሲመሰል /8፥22/ በመከራው ፈንታ የሚሆነው ታላቅ ደስታ ደግሞ በታላቅ ብርሃን ተመስሎአል፡፡ ይህም በመሢሑ መወለድ ይፈጸማል በመሲሁ መወለድ ዘለዓለማዊ ደስታና ሰላም ይሆናል፡፡ 9፥8-12 ነቢዩ በድጋሚ የእስራኤልን ውድቀት ይነተብያል፡፡ ይሁን እንጂ /9፥13-17/ ሕዝቡ አልተመለሱም፡፡ 9፥18-21 ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ ይሆናል በአንዱ በሌላው ላይ በጠላትነት ይነሣል የምናሴና የኤፍሬም ሕዝብ እርስ በርሳቸው ይፋጃሉ /2ነገሥት 15፥23-26/ እንደገናም በአንድነት ሆነው በይሁዳ ላይ ይነሣሉ፡፡

8. 1-4 የሕዝቡን ኃጢአተኛነት፣ የእግዚአብሔርም ቍጣ ገና በሕዝቡ ላይ መሆኑን ያብራራል። 10፥5-15 አሦር የእግዚአብሔር የቍጣው በትርና ጨንገር እንደሆነ ተገልጦአል። ነገር ግን አሦር ሀገሮችን ሁሉ በራሱ ኃይል ድል አድርጐ እንደያዘ ይመካል እንጂ እግዚአብሔር መሣሪያ አድርጐ እንዳስነሳው አላስተዋለም። 10፥16-19 በአሕዛብ ላይ የሚሆነው ቅጣት የእሳት አሕዛብም ራሳቸው በእሳት እንደሚቃጠል ጫካ ሆነው ተመስለዋል። 10፥20-23 ትሩፋት ብቻ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚያመልጡ ያሳያል። 10፥23-34 ለትሩፋት የማጽናኛ ቃል ይናገራል።
9. 1-4 ከእሴይ ሥር ቍጥቋጦ /ናዴር/ ይወጣል ለእርሱም ሰባት ሀብታት ይሰጡታል፣ ይህም መሢሑን የሚመለከት ሀብር አምሳል ነው። 11፥5-9 በመሢሑ ዘመን ፍፁም ሰላም ይሆናል። 11፥10-13 /የተሰደዱት ይመለሳሉ/ የተበተኑት ይሰበሰባሉ። 11፥14-16 የእግዚአብሔር ሕዝብ ጥንት ጠላቶች በእግዚአብሔር ኃይል ድል ይሆናሉ።
10. 1-6 የምሥጋና መዝሙር ቍ 1-3 በመጀመሪያው የመዝሙር መስመር ስንኝ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ቍ 4-6 በሁለተኛው ስንኝ /መስመር/ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ታላቅ ሥራ ይገኛሉ።

   መነጻጸር 8፥17 ከ45፥15 እና ከ57፥17። 9፥2። ከ42፥7። 9፥20፣ 49፥26 11፥1 ከ60፥21፣ 11፥1-10 ከ53፥2፣ 11፥2 ከ42 1 እና ከ61፥1 11፥4 ከ49፥26። ከ65፥25 11፥9 ከ65፥25 11፥12 ከ56፥8 እና ከ62፥10 ጋር ይነጻጸራል።

ለ. ምዕራፍ 13፥1-23፣8 ከይሁዳና ከእሰራኤል ውጭ የሆኑ ሕዝባችን የሚመለከቱ ትንቢቶች

በዚህ ክፍል የፍርድ ትንቢት የተነገረባቸው የአሕዛብ ሀገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. ባቢሎን፣ ምዕራፍ 13፥1-14፣32 በዚህ ክፍል ዐሦርና /ምዕ 14፥24-28/ ፍልስጥኤም /ምዕ 14፥29-31/ ተጠቅሰዋል።
2. ሞዓብ ምዕ 15፥1-16፥14
3. ደማስቆ ምዕ 17፥1-14
4. ኢትዮጵያ ምዕ 18፥1-7
5. ግብጽ ምዕ 19፥1-25

6. ምዕ 19፥1-25 ምዕ 20፥1-6 ግብጽና ኢትዮጵያ በአሦር ድል እንደሚሆኑ ነቢዩ ራሱ ምልክት ሆኖ ተሰጥቶአል፡፡
7. ምዕ 21፥1-10 ሀ/ የባቢሎን ውድቀት እንደገና በዚህ ክፍል ተደግሞአል፡፡ ምድረ በዳው በመባል የጠቀሰው ባቢሎን ናት፡፡ ለ/ ኤዶምያስ 21፥11-12 ሐ/ ዐረብ 21፥13-17
8. ምዕ 22፥1-25 የራእይ ሸለቆ እዚህ ላይ የራእይ ሸለቆ በመባል የተጠራች ኢየሩሳሌም ናት፡፡ ይህም ኢየሩሳሌም በተራሮች መካከል ያለች መሆንዋን ያመለክታል፡፡ /መዝ 124፥2፣ ኢዮኤል 3፥12-14/ በተጨማሪም ሸለቆ የሚለው ቃል ምሳሌያዊ ቃል ነው፡፡ የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ታቦተ ጽዮን ይላል፡፡
9. ምዕ 23፥1-18 ጢሮስ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተርቤስ የሚለውን ቃል ግእዙ ኬልቄዶን በማለት ይጠራዋል፡፡

እስካሁን በተጠቀሱት ሀገሮች ሁሉ ላይ የተነገረው ትንቢት "ሸክም" ተብሎአል፡፡ ምክንያቱም በነቢዩ አንደበት የተላለፈው የእግዚአብሔር ፍርድ ከባድ ነውና፡፡ ከዚህ ጋር ነቢዩ ከራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው ስለሆኑ ነው፡፡

ሐ. ምዕራፍ 24፥1-27፣13 በዓለም ላይ ስለሚሆን የመጨረሻ ፍርድና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ኢሳይያስ ያየው ራእይ

ኢሳይያስ በእነዚህ አራት ምዕራፎች ውስጥ የዓለም ፍጻሜ ሁኔታ ስለ ፍርድ ቀንና ስለ ሁሉ ነገር መታደስ፣ ስለ ሙታን ትንሣኤም ይናገራል፡፡ /26፥19/ እግዚአብሔር የሚመሰገንባቸው አራት መዝሙሮች ወይም ቅኔዎች በዚህ ራእይ ውስጥ ይገኛሉ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. 25፥1-5
2. 25፥9-12
3. 26፥1-19
4. 27፥2-6

ከእነዚህ መካከል በ26፥1-19 ያለው መዝሙር ተለይቶ አዲየስ በመባል ከታወቁት 15 መዝሙራት ጋር ሆኖ ይዘመራል፡፡

በእኛም ቤተ ክርስቲያን 15ቱ ነቢያት ከሚባሉት አንዱ ይህ የኢሳይያስ መዝሙር ነው፡፡ ይህም ከመዝሙረ ዳዊት ቀጥሎ ተጠርዞ ይገኛል፡፡

መ. ምዕራፍ 28፥1-35፥10 ከእስራኤል ውድቀት በኋላ ይሁዳን የሚመለከቱ ትንቢቶች

ይህ ክፍል ብዙ ጊዜ ስለ ጽዮን ስለሚናገረ “የጽዮን መጽሐፍ” የሚል ስያሜ አለው። ለምሳሌ ምዕ 30፥19፣ 31፥5፣ 33፥20፣ ምዕ 35 ደግሞ በመሢሑ ጊዜ የሚፈጸመውን ነገር ያስረዳል። በተጨማሪም ይህ ክፍል ካለፈው የራእይ ክፍል ጋር ይመሳሰላል ምክንያቱም ስድስት የወዬታ ቃል ይገኙበታል። እነዚህም ቀጥሎ ያሉ ናቸው።

1. 28፥1
2. 19፥1
3. 19፥15
4. 30፥1
5. 31፥1
6. 33፥1

ሠ. ተጨማሪ የታሪክ ክፍል፡- ምዕራፍ 36፥1-39፡8

ይህ ክፍል የሚከተሉት ታሪኮች ይዞአል። ይሁዳ በሰናክሬም መወረርዋ /ምዕ 36/ የንጉሡ ሕዝቅያስ መልእክት ወደ ኢሳይያስ /37፥1-5/ ኢሳይያስ ለሕዝቅያበስ /የላከው/ የመለሰው የማጽናኛ ቃል። /37፥35/ የአሦር ሠራዊት በመልአክ እግዚአብሔር መደምሰስ /37፥36-38/ የሕዝቅያስ እስከ ሞት ድረስ መታመምና በተአምር መዳን 15 ዓመት ተጨማሪ ዕድሜ ማግኘት /38፥1-8/ ሕዝቅያስ በተፈወሰ ጊዜ ለእግዚአብሔር የቀረበው ምሥጋና /38፥22/። ከባቢሎን የተላኩ መልእክተኞች የሕዝቅያስን ቤተ መዛግብት ማየታቸው /39፥1-2/ ነቢዩ ኢሳይያስ የይሁዳን ሕዝብ ወደ ባቢሎን መማረክ ማሳወቅ በዚህ ክፍል ተተርከዋል። ይህ ታሪክ በ2 ነገ ከምዕ 18-20 ስለ ተተረከ ይህንም መመልከት ያስፈልጋል።

ረ. ምዕራፍ 40፥1-66፥24

የማጽናናት ትንቢቶች ይህ ክፍል 40-55 በባቢሎን በጼዋቄ የሚኖሩ አይሁድን የሚያጽናና ወደ ሀገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ የሚያደርጉትን ዝግጅት የሚያሳይ የትንቢት ክፍል ነው።

የሚከተሉት ጥቅሶች ይህን ሀሳብ ይገልጣሉ። 43፥14፣ 46፥1፣ 48፥14-20 የባቢሎን መንግሥት በፈራሳዊው ቂሮስ እንደሚወድቅ፣ እግዚአብሔርም በቂሮስ አማካኝነት ሕዝቡን ከጼዋቄ፡- እንደሚመለስ በ45፥1፣ 44፥28 ላይ በግልጥ ተነግሮአል። በጦርነት ጊዜ የተደመሰሱ ከተሞች በሚጠት ጊዜ ተመላልሰው የሚታነፁ መሆናቸውን ቀጥሎ ያሉት ጥቀሶች ያስረዳሉ። 44፥26፣ 49፥14-21፣ 52፥8-9

በዚህ ክፍል ልዩ አመለካከት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለ /ዓበጽ/ ገብር ፍቁር የሚናገሩት ንባባት ናቸው። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. 42፥1-9 ሐ. 50፥4-9

ለ. 49፥1-7 መ. 52፥12-53፥12 አንዳንድ ሊቃውንት እነዚህ ጥቅሶች በሌሎች ምዕራፋት ስለ ግብር ከሚናገሩት ጥቅሶች ተለይተው መታየት እንደሌለባቸው ይገምታሉ፡፡ ነገር ግን እንደ ብዙዎች ሊቃውንት እምነት እነዚህ ንባባት /ነገራት/ ግብር በዚሁ በካልእ ኢሳይያስ ስለ ግብር ከተነገሩት ጥቅሶች ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ 41፥8-10 እና በምዕ 42፥19 ላይ የሚገኘው ግብር /ዓቤጽ/ ጠቅላላ እስራኤልን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተመለከትናቸው አራቱ ጥቅሶች ውስጥ የተነገረው ግብር ፍቁር ለሕዝበ አይሁድ ታላቅ ሥራ የሚሠራ አንድ የተለየ ግለሰብ ክርስቶስ መሆኑን እንረዳለን፡፡ /49፥5-6/ ተመልከት፡፡ እርሱም ስለሌሎች ብዙ ጸዋትወ መከራ የሚቀበል ጽድቅና ውሃቤ ሰላም እንደሆነ ተነግሮታል /ምዕ 53/ የአይሁድ ሊቃውንት፡- ይህ ፀዋሬ ሕማም ግብር ሀ/ ዘሩባቤል፣ ለ/ የአኳን /ኢኮንያን/ ሐ/ ሙሴ ነው በማለት ተርጉመዋል፡፡ ኤርምያስ ወይም ቄሮስ ነው በማለትም የተረጐሙ አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብ/ኪዳን ሊቃውንትም ግብር ፍቁር የተባለ ለጊዜው ዘሩባቤ ወይም ቄሮስ ፍጻሜው ግን ክርስቶስ እንደሆነ ይተረጉማሉ፡፡ ነገር ግን ከአይሁድ ሊቃውንት መካከል “ግብር ፍቁርን ለመሚሐ ሰጥቶ የተረኅመ እስካሁን የለም፡፡

ከጥንት ጀምሮ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ግብር ፍቁር መሚሐ እንደሆነ ተናግረዋል፣ ጽፈዋልም፡፡ እነርሱንም በመከተል የክርስትና እምነት አቢዮችና ሊቃውንት ሁሉ ይህ ሀሳብ ይቀበላሉ፡፡ እኛም ይህንኑ እንከተላለን፡፡ /እላይ ከሐዲስ ጋር የተቆራኘትን የኢሳይያስ ጥቅሶችን ተመልከት/

3ኛ <u>ኢሳይያስ</u>

2. ምዕራፍ 56፥1-66 2 በእነዚህ ምዕራፎች ያሉ ታሪኮች በጸዋዌ ሀገር ሳይሆን በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ሕዝብ የተነገሩ ናቸው፡፡

1. ምዕ 56፥1-8 እግዚአብሔር ጽድቁንና አድኅኖቱን ሳይወሰንና ሳያዳላ በምልዓት እንደሚሰጥ ያስረዳል፡፡ ግን ኃጢአተኛ ትውልድ ለዚህ ጽድቅና አድኅኖት የተገባ አይደለም፡፡ ቊ 9፥12፡፡
2. ምዕ 57፥1-2 ጻድቅ ሰው በሚመጣው ክፉ ነገር ሁሉ እንደሚድን ቊ 3-9 ኃጢአተኞች ደግሞ በጣዖታዊነታቸውና በአመንዘራዊነታቸው እንደሚወቀሱ፣ ቊ 10-13 እንደገና በኃጢአታቸው ስለሚገፉበት እንደሚጠፉ ይገልጣል፡፡ ነገር ግን ንስሐ ለሚገቡ ሁሉ ድኅነት ይሆንላቸዋል ቊ 13 ለ-21፡፡ ቊጥር 21 በእስራኤል ዘንድ እንኳ ቢሆን

ለኢተንሣሐያን በረከት ጽሂ እንደማይኖራቸው ያስረዳል፣ ተስፋ የተሰጠ ለእውነተኛ ምእመን እስራኤል ነው እንጂ ለማያምን አይደለምና።

3. ምዕራፍ 58፥1-7 እስራኤል በግብዝነት የሚያደርጉትን ጾምና አምልኮት እግዚአብሔር እንደነቀፈ፣ ቍ 8፥14 ትክክለኛውን ጾምና ለባልንጀራቸው ሊያደርጉት የሚገባውን ምግባር እውነተኛውንም የሰንበት አከባበር እንዲከተሉ የተሰጠውን ምክር ያብራራል።
4. ምዕራፍ 59፥1-2 ኃጢአት በእስራኤልና በእግዚአብሔር መካከል እንደ መጋረጃ ሆኖ መለየቱን ይናገራል። ቍ 3-15 እንደ መጋረጃ ሰውን ከእግዚአብሔር የለየውን የኃጢአት አይነት ይዘረዘራል። ቍ 16፥21 እግዚአብሔር ራሱ እውነተኛውን ምእመን እስራኤል በታዳጊው /መሢሑ/ እንደ ሚያምን ይገልጣል።
5. ምዕራፍ 60፥1 ለምእመን እስራኤል የሚሆነውን መንፈሳዊ ለውጥ በብርሃን መስሎ ያብራራል። ቍ 2-14 በዓለም ላይ ያሉ በጨለማ የሚኖሩ አሕዛብ ወደ ጽዮን ይመጣሉ፣ ጽዮን በታላቅ ክብር ለዘለዓለም ትከብራለች ቍ 15፥22 ይህም በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ታላቅ ክብር ያመለክታል።
6. ምዕራፍ 61 ቍ 1-3 የመሢሑን መልእክት ይዘዋል። ቍ 4-11 በመሢሑ የሚሰጡ ዓበይት በረከቶች ተዘርዝረዋል።
7. ምዕራፍ 62፥1 ፍጹም ጽድቅና ድኅነት እስከሚሆን ድረስ የመሢሑ መልእክት አያቋርጥም። ቍ 2፥12 ሕዝብ እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ዘንድ ይታወቃል። ቅዱስ ሕዝብም ይባላሉ። ዓለም ሁሉ ጽዮንን ይፈልጋል። ጽዮንም የተፈለገች ያልተተወች ትባላለች።
8. ምዕራፍ 63 በዚህም ምዕራፍ የመሢሑ መልእክት ይቀጥላል። ቍ 1-6 መሢሑ አሕዛብን ይበቀላል። ቍ 7-14 ሕዝቡ ምን እንኳ ታማኝነትን ባያሳዩም እግዚአብሔር ለእነርሱ ታማኝና መሐሪ ነው። ቍጥር 15-19 እግዚአብሔር ለእነርሱ ታማኝና መሐሪ ነው። ቍጥር 15-19 እግዚአብሔር ርኅራኄን እንዲያደርግላቸው እስራኤል ይማልዳሉ።
9. ምዕራፍ 64፥1-12 ከምዕራፍ 63፥15-19 የተያያዘ ነው። ልመና፣ ኑዛዜና ተማሕጽኖ አለበት በተለይ ሕዝቡን ያሳዝናቸው የጽዮን ምድረ በዳ መሆን የቤተ መቅደስ መቃጠልና የከተማው መፍረስ እንደሆነ ከቍጥር 11-12 ላይ ተወስቶአል።
10. ምዕራፍ 65፥1 አሕዛብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን ይጠራሉ። ቍ 2-7 አይሁድ በኃጢአታቸው ምክንያት ይናቃሉ። ቍ 8፥10 የተመረጡት ትሩፋትን ግን በክብር

ይኖራሉ፡፡ ቁ 11-16 የማያምን እስራኤል ያፍራል፡፡ እውነተኞች አግብርተ እግዚአብሔር ግን ከልብ ደስታ የተነሣ ይዘምራሉ፡፡ ቁ 17-25 አዲስ ሰማይና የአዲስ ምድር በረከቶች ተነግረዋል፡፡

11. ምዕራፍ 66 በብሉይና በሐዲስ ሥርዓቶች መካከል ስላለው ለውጥ ያብራራል፡፡ ቁ 1-2 እግዚአብሔር በምድራዊ መቅደስ ሳይሆን በትሑታን ልብ ያድራል ቁ 3-6 እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ የሚሄድ ሰዎች መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስፈያፊ ነው፡፡ ቁ 7-14 የጽዮን የሚሰጡ በረከቶች ተነግረዋል፡፡ ቁጥር 15-24 ከእስራኤል ወገን ዓመፀኞች እንደሚጠፉ የሚያምኑ አሕዛብና ትሩፋን ግን ጸንተው እንደሚኖሩ ይገልጣል፡፡

ኢሳይያስ በሚጠት ጊዜ ስለታደሰችው ኢየሩሳሌም የተናገረው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንና ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ይመለከታል፡፡ ይህንም ዮሐንስ በራእዩ እንደተጠቀመበት የሚከተሉትን ጥቅሶች እናነጻድር

ኢሳይያስ	ራእየ ዮሐንስ
54፥11-12	21፥15-21
60፥3	21፥24
60፥11	21፥25-26
60፥19-20	21፥23፣ 22፥5
66፥22-23	21፥1
66፥22-23	21፥5

ማጠቃለያ

- .

የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ የሙከራ ጥያቄዎች

1.